# CHOKIE JOURNAL OF LAW

**Vol. 1 Issue 2** **December 2024**

## የምርምር ጽሁፎች

## ARTICLES


የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ ፍሬ ነገሮች እና የህግ ተጠያቂነት በኢትዮጵያ

**ወልደዮሐንስ ወልደሰማያት ወልደመድህን……………………………..……………………….....1**

Investor to State Dispute Resolution in Ethiopia: An Assessment of the Practice During Political Instability

**Aragew Tsegaye Tadesse……..……………………………………………………..………32**

በኢኮኖሚና በገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እና የሕጋዊ ገንዘብ እንቅስቃሴ ገደብ ወንጀል፡ የህግ አተገባበር ዳሰሳ በአማራ ክልል

**አለምነህ ሹመቴ ጌቴ…………………………………...………………………………......66**

በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ በአማራ ክልል

**ዳኘነት ይግዛው ዘለቀ……………………………………......……………………………........106**


## የህግ ዳሰሳ

## LEGISLATIVE REVIEW


የንግድ-ነክ እርቅ ስነ-ስርዓት በኢትዮጵያ፡ የአዋጅ ቁጥር 1237/2013 ዳሰሳ

**ምህረቱ ይዘንጋው ድንቁ ……………………………………………………………….…128**



በደብረ ማርቆስ ዩንቨርሲቲ ህግ ት/ቤት በዓመት ሁለት ጊዜ የሚታተም የህግ መጽሄት

Published Bi-annually by Law School, Debre Markos University

በ፳፻፲፭ ዓ.ም ተመሰረተ

Established in 2023

# CHOKIE JOURNAL OF LAW

**Volume 1 Issue 2** **December 2024**


## Advisors

**Adem Kassie Abebe** (LL.D. Senior Advisor in Constitution and Peace Building at the International Institute for Democracy and Electoral Assistance (IDEA); Adjunct Professor, Debre Markos University)

**Ayalew Abate** (PhD, former Vice Attorney General, Amhara National Regional State)

**Wouter Vandenhole** (PhD, Prof. of Law, University of Antwerp Faculty of Law)

**Yongmei Chen** (PhD, Prof. of Law, School of International Law, Southwest University of Political Science and Law)

## Editorial Members for this Issue

**Anteneh Geremew** (LL.B, LL.M., Assistant Prof.) Editor-in-chief

**Haile Andargie** (LL.B, LL.M., PhD) Associate Editor

**Biruk Abiyu** (LL.B, LL.M.)

**Mekonnen Nigussie** (LL.B, LL.M., Assistant Prof.)

**Zelalem Teferra** (LL.B, LL.M., PhD)

## Reviewers of Articles for this Issue

**Bebizuh Mulugeta Menkir:** LL.B., LL.M., LL.M. (Senior National Consultant for the Criminal Justice Project, Federal Supreme Court of Ethiopia)

**Biniam Shiferaw Ayalew:** LL.B., LL.M. (Anti-Money Laundering/CFT Consultant, Tana Copenhagen)

**Dejen Alamirew Moges:** LL.B., LL.M. (Assistant Prof., Debre Markos University)

**Hailemariam Belay Fenta:** LL.B., LL.M. (Lecturer in Law, University of Gondar)

**Mekuriaw Alemenew Yilma**: LL.B., LL.M. (Retired Assistant Prof., Debre Markos University; Attorney and Consultant at Law)

**Silesh Walelign Kebede:** LL.B, LL.M. (PhD Candidate, at Wuhan University, China)

**Woldetinsae Fentie Assegu:** LL.B., LL.M. (Assistant Prof., Debre Markos University, PhD Candidate, at Addis Ababa University)

**Zemenu Tarekegn Yimenu:** LL.B., MA, LL.M., LL.M. (Attorney and Consultant at Law)

# CHOKIE JOURNAL OF LAW

**Vol. 1 Issue 2** **December 2024**

## የምርምር ጽሁፎች

## ARTICLES

**የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ ፍሬ ነገሮች እና የህግ ተጠያቂነት በኢትዮጵያ**
**ወልደዮሐንስ ወልደሰማያት ወልደመድህን**…………..……………..……………………......1

Investor to State Dispute Resolution in Ethiopia: An Assessment of the Practice During Political Instability
Aragew Tsegaye Tadesse…….………………………………………………..……...…32

**በኢኮኖሚና በገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እና የሕጋዊ ገንዝብ እንቅስቃሴ ገደብ ወንጀል፡ የህግ አተገባበር ዳሰሳ በአማራ ክልል**
**አለምነህ ሹመቴ ጌቴ**……………………………….……………………………….…......66

**በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ በአማራ ክልል**
**ዳኝነት ይግዛው ዘለቀ**…………………......………………...……………………………......106

## የህግ ዳሰሳ

## LEGISLATIVE REVIEW

**የንግድ-ነክ እርቅ ስነ-ስርዓት በኢትዮጵያ፡ የአዋጅ ቁጥር 1237/2013 ዳሰሳ**
**ምህረቱ ይዘንጋው ድንቁ** ………………………………………………………...…128

***Chokie Journal of Law Author's Guidelines***........................................................................141

**Disclaimer**: Statements of facts and opinions are made on the responsibility of the authors alone and do not represent the views of the editors and Debre Markos University. Neither Debre Markos University nor the editors make any representation, express or implied, in respect of the accuracy of the material in this journal and cannot accept any legal responsibility or liability for any errors or omissions that may be made.

# የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ ፍሬ ነገሮች እና የህግ ተጠያቂነት በኢትዮጵያ

**ወልደዮሐንስ ወልደሰማያት ወልደመድህን***

**Abstract**

This paper investigates the fundamental legal elements and extent of the application of the crime of breach of trust within Ethiopia's criminal legislations. It is based on an examination of Ethiopian criminal laws, books, legal analyses, judicial rulings, and instructions issued by the chief prosecutor, as well as conducting some interviews. This paper found that there are varying interpretations among legal professionals concerning the legal components that define the crime of breach of trust, and it recommends that the provisions of the Criminal Code and the Corruption Crimes proclamation should be amended.

**Key Words:** Criminal Code, Breach of Trust, Corruptions Crime

**አህፅሮተ-ፅሁፍ**

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ዕምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ መሰረታዊ ፍሬ ነገሮችንና የተፈፃሚነት አድማስ የሚዳሰሱበት ነዉ ሲሆን ዕምነት ማጉደል ወንጀልን የሚመለከቱ የኢትዮጵያ ወንጀል ህጎችን ፣መጽሐፍትን፣ የህግ ማብራሪያዎችን፣ የፍርድ ቤት ዉሳኔዎችን እና በበላይ ዓቃቢ ህግ የተሰጡ መሪ ትዕዛዞችን በማንበብ እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተሰራ ነዉ። ዕምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ ፍሬ ነገሮችን በተመለከተ በህግ ባለሙያዎች ዘንድ የአተረጓጎም ልዩነቶች ያሉ መሆኑ በዚህ ጥናት የተረጋገጠ ሲሆን ድርጊቱን የሚመለከቱት የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች እና የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ማሻሻያ እንደሚያስፈልጋቸዉ ምክር ሃሳብ ተሰጥቷል።

**ቁልፍ ቃላት፡** የወንጀል ህግ ፣ ዕምነት ማጉደል፣ የሙስና ወንጀል

* ፀሐፊዉ በ 2007 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ህግ ትምህት ቤት የመጀመሪያ ድግሪዉን በህግ ያገኘ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በአብክመ ሰ/ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ በዓቃቢ ህግነት እየሰራ ይገኛል። ለማንኛዉም አስተያየትዎ ፀሐፊዉን በኢሜል gawmmysix@gmail.com ወይም 0921563755/0967302628 ማግኜት ይችላሉ።

## 1. መግቢያ

የእምነት ማጉደል ወንጀል በንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሚደነግገዉ በኢፌዲሪ ወንጀል ህግ ስድስተኛ መጽሐፍ በምዕራፍ ሁለት ስር በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በተለይ በሚደነግገዉ በክፍል አንድ ስር የሚገኝ ነው፡፡ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ድንጋጌዎች በወንጀል ህጉ አንቀጽ 675 ስር ተደንግገዉ የሚገኙ ሲሆን የወንጀሉን ከባድ ሁኔታ የሚደነግገዉ ደግሞ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 (1) እና (2) ስር የተመለከተዉ ነዉ፡፡ ከወንጀል ህጉ በተጨማሪ ከባድ ዕምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁም ድንጋጌ ይዞ የመጣዉ በ 2007 ዓ.ም የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡ ይህ አዋጅ በወንጀል ህጉ ከተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ዉስጥ በአፈፃፀም ወቅት የተስተዋሉ ግልፅነት የሚጎድላቸዉን ድንጋጌዎች ግልፅ በማድረግና በማሻሻል የሙስና ወንጀሎች ራሱን በቻለ አዋጅ እንዲደነገጉ ለማድረግ በማሰብ እንደወጣ በአዋጁ መግቢያ ላይ ተቀምጧል፡፡[1] በሙስና ወንጀሎች አዋጅ እንዲካተቱ ከተደረጉ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች አንዱ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 (1) ስር ተደንግጎ የነበረዉ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ነዉ፡፡

ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚደነግገዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 በከፊል ተሽሮ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 ስር እንዲካተት ሲደረግ በተሻረዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 እና እሱን በተካዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 መካከል መሰረታዊ ልዩነቶች መኖራቸዉ የሙስና ወንጀል የሆኑትን የእምነት ማጉደል ወንጀሎች እና በመደበኛዉ የወንጀል ህግ የሚሸፈኑትን የእምነት ማጉደል ወንጀሎች በመለዬት በኩል በህግ ባለሙያዎች ዘንድ የአተረጓጎም ልዩነቶችን ተስተዉለዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 ላይ በተደነገገዉ ከባድ የዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል እና በአንቀጽ 15(1) (ለ) ላይ በተደነገገዉ በስራ ተግባር ላይ የሚፈፀም የመዉሰድ እና መሰወር ወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተም እንዲሁ በህግ ባለሙያዎች ዘንድ የአተረጓጎም ልዩነቶች አሉ፡፡[2]

ጽሁፉ በሶስት ክፍሎች የተዋቀረ ሲሆን የመጀመሪያዉ ክፍል የዕምነት ማጉደል ወንጀል መሰረታዊ ባህሪያት እና ወንጀሉን የሚያቋቁሙ የህግ ፍሬ ነገሮች የሚዳሰሱበት ሲሆን የወንጀሉን ባህርይና ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮችን በሚገባ ለመረዳት ይረዳን ዘንድ የወንጀል ህጉ ከመዉጣቱ በፊት ስለ ዕምነት ማጉደል ወንጀል የሚደነግጉ ሌሎች የአገራችን የወንጀል ህግጋት

---

[1] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሙስና ወንጀሎች አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 881/2007፣ መግቢያ የመጀመሪያዉ ፓራግራፍ

[2] የኢፌዲሪ ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ፣ የአተረጓጎም ልዩነት ያለባቸዉ የወንጀል ድንጋጌዎች ላይ ወጥነት ያለዉ ትርጉም ለማምጣት እንዲቻል የተዘጋጀ የህግ ማብራሪያ ሰነድ (2013) 62

ጭምር ይዳሰሱበታል፡፡ በክፍል ሁለት ደግሞ በወንጀል ህጉ የተደነገገዉ ዕምነት ማጉደል ወንጀል በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ከተደነገገዉ ከባድ ዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ፤ በስራ ተግባር ላይ ከሚፈፀም የመዉሰድና መሰወር የሙስና ወንጀል እንዲሁም ከአታላይነት ወንጀል ማቋቋሚያ ድንጋጌዎች አንፃር የተፈፃሚነቱ አድማስ የሚዳሰሱበት ነዉ፡፡ የመጨረሻዉ ክፍል በሆነዉ ክፍል ሶስት ደግሞ የዕምነት ማጉደል ወንጀል ጉዳዮችን አይቶ የመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን ስላለዉ ፍርድ ቤት የሚዳሰስበት ነዉ፡፡

## 2. የእምነት ማጉደል ወንጀል መሰረታዊ ባህሪያት

በአገራችን ታማኝነት ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጠዉ ማህበረሰባዊ ዕሴት ነዉ፡፡ በማህበረሰባችን ዉስጥ በእምነት የተሰጣቸዉን የሌላ ሰዉ ንብረት ከራሳቸዉ ንብረት በበለጠ ጠብቀዉ እና ተንከባክበዉ በጊዜዉ ለባለቤቱ የሚመልሱ አለያም ለታለመለት ዓላማ የሚያዉሉ በርካታ አደራ ጠባቂ የሆኑ ግለሰቦች እንዳሉ ሁሉ ለአንድ ለተወሰነ ተግባር የተሰጣቸዉ ጥሬ ገንዘብ ወይም ሌላ ዋጋ የሚያወጣ ነገር ወስደዉ በዛዉ የዉሃ ሽታ ሆነዉ ከባለቤቱ የሚሰወሩም አለያም አደራ በላ ሆነዉ የሚቀሩም ይኖራሉ፡፡

*"የአንባሰል ማር ቆራጭ ይወርዳል በገመድ*

*አደራ ቢሰጡት ይበላል ወይ ዘመድ፡፡"*

የሚለዉ የህዝብ ግጥም አደራ በማህበረሰባችን ዉስጥ የሚሰጠዉን ቦታ እና ከአደራ አስቀማጩ የሚጠበቀዉን ግዴታ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡በክርስትና አስተምሮም "የቄሳርን ለቄሳር የእግዚያብሄርን ለእግዚያብሄር አስረክቡ አላቸዉ ፡፡ በእነሱም ተደነቁ፡፡" የሚል በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ከቁጥር 17 ላይ እናገኛለን፡፡ በአገራችን በባህልም ሆነ በሃይማኖት አስተምሮ ዕምነትን አጉድሎ መገኘት ወይም አደራ መብላት የተወገዘ ተግባር ነዉ፡፡

ዕምነት ማጉደል የሚያስከትለዉን የወንጀል ሃላፊነት በተመለከተ በአገራችን የወንጀል ህግ ራሱን ችሎ ከወጣበት ከ 1923 ዓ. ም ጀምሮ በየጊዜዉ በወጡት የወንጀል ህግጋት ድርጊቱ እንደዬ አፈፃፀሙ ሁኔታ የአመታት እስራትን የሚያስቀጣ ከባድ የወንጀል ድርጊት ሆኖ ተደንግጎ እናገኜዋለን፡፡

በ1923 ዓ.ም በወጣዉ የወንጀለኞች መቅጫ ህግ የእምነት ማጉደል ወንጀል በሁለት የተለያዩ ምዕራፎች ላይ ተደንግጎ እናገኘዋለን ፡፡ የመጀመሪያዉ በመንግስት ሰራተኞችና በመንግስት መስሪያ ቤቶች ስለሚሰራ ወንጀል በሚደነግገዉ 10ኛዉ ምዕራፍ አንቀጽ 229 ላይ የተደነገገዉ

ሲሆን ለመጠበቅ የተቀበለዉን ማናቸዉም የመንግስት ዕቃ ሳያስፈቅድ ለራሱ የወሰደ ወይም እጅ አዛዉሮ ያስወሰደ ከስድስት ወር እስከ 2 አመት እስራት እና ከ 20 ብር እስከ 50 ብር የገንዘብ መቀጮ እንደሚያስቀጣ የሚደነግገዉ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ደግሞ በገንዘብ ላይ ስለሚሰራ ወንጀል በሚገነግገዉ ምዕራፍ በአንቀጽ 454 ስር የተደነገገዉ ሲሆን በእምነት በባዶ ወረቀት ላይ ፊርማዉንና ማህተሙን አድርጎ ሲሰጠዉ በፈረመዉ ሰዉ ላይ በሰዉነቱ ወይም በገንዘቡ ጉዳት የሚያመጣበትን ቃል በሐሰት የፃፈ በሚል የተቀመጠዉ ነዉ፡፡ እነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች የዕምነት ማጉደል ወንጀል በመንግስት ንብረት ላይ ሲፈፀም እና በግለሰብ ንብረት ላይ ሲፈፀም  የሚያስከትለዉን የወንጀል ሃላፊነት ለያይተዉ የሚያስቀምጡ ሆነዉ እናገኛቸዋለን፡፡

በ1949 ዓ.ም የወጣዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ከ 1923 "ቱ" የወንጀለኞች መቅጫ ደንብ በተሻለ መንገድ የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ ፍሬ ነገሮችን በዝርዝር አስቀምጦ እናገኘዋለን፡፡[3] የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ ፍሬ ነገሮችን በግልፅ ደንግጎ ከማስቀመጥ ባለፈ የወንጀሉን ከባድ ሁኔታ የሚደነግጉ ማክበጃ ምክንያቶችም ለመጀመሪያ ጊዜ የተካተቱት በዚሁ ህግ ነዉ፡፡[4] በ 1966 ዓ.ም የተካሄደዉን አጠቃላይ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ተከትሎ ወደ ስልጣን የመጣዉ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት ደርግ በጊዜዉ በስራ ላይ የነበረዉን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በከፊል ያሻሻለ የተሻሻለዉ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ እየተባለ የሚጠራ ህግ አዉጥቶ በስራ ላይ አዉሏል፡፡[5]

የተሻሻለዉ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በምዕራፍ 2 ላይ ታማኝነትን በማጓደልና በመንግስት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ ስለሚሰሩ ወንጀሎች በሚለዉ ርዕስ ስር ዕምነት ስለማጉደል ወንጀል ፣የማይገባ ጥቅም ስለማግኘትና ያላግባብ ስለማጥፋት የሚደነገጉ አንቀፆችን ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ የተደነገገዉ የእምነት ማጉደል ወንጀል ማቋቋሚያ ህጋዊ ፍሬ ነገር በመንግስት፣በህዝባዊ ድርጅቶች ወይም በህብረት ስራ ማህበራት ንብረቶች ላይ የሚፈፀሙ የእምነት ማጉደል ወንጀልን ብቻ የሚመለከት ነዉ፡፡ ይህ አዋጅ የወጣበት አንዱ ምክንያት የመንግስትና ህዝባዊ ድርጅት ንብረቶች ላይ የሚፈፀሙ ህገወጥ ተግባራትን ጨርሶ ለማጥፋት በመሆኑ[6] በግለሰብ ንብረቶች ላይ የሚፈፀሙ መሰል የእምነት ማጉደል ተግባራትን እንዲደነግግ አይጠበቅም፡፡ ይሄ አዋጅ የ 1949 ኙን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሙሉ በሙሉ

---

[3] *የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ* ፣ አዋጅ ቁጥር 158/1949፣ አንቀጽ 641

[4] *የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ* ፣ አዋጅ ቁጥር 158/1949፣አንቀጽ 642

[5] *የተሻሻለዉ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ፣* አዋጅ ቁጥር 214/1974

[6] *የተሻሻለዉ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ፣* አዋጅ ቁጥር 214/1974፣ የአዋጁን መግቢያ ፓራግራፍ 3 ላይ ይመልከቱ

ያልሻረ በመሆኑ በግለሰብ ንብረት ላይ የሚፈፀም የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚመለከተዉን አንቀጽ ጨምሮ በአዋጁ ባልተሸፈኑት በሌሎች ጉዳዮች ላይ የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ ድንጋጌዎች ጎን ለጎን ተግባራዊ ሲሆኑ ቆይተዋል።

በ1996 ዓ. ም የኢ.ፌ.ዴ. ሪ የወንጀል ህግ በልዩ ልዩ አዋጆች ተበታትኖ የነበረዉን የወንጀል ህግ በአንድ አጠቃሎ (ኮምፐርሄንሲቭ ሆኖ) እንዲወጣ ሲደረግ ጎን ለጎን ሲተገበሩ የነበሩት የ 1949 "ኙ" የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ እና የተሸሻለዉ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሁለቱም ተሽረዋል። የኢ.ፌ.ዴ. ሪ የወንጀል ህግ ልክ እንደ 1949 "ኙ" የወንጀል ህግ ሁሉ የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ ፍሬ ነገሮችን በአንቀጽ 675 ላይ ከደነገገ በኋላ ወንጀሉን የሚያከብዱ ፍሬ ነገሮችን ደግሞ በተከታዩ አንቀጽ (አንቀጽ 676) ላይ አስቀምጧል። የድንጋጌዎች አቀማመጥ ለዉጥ እና የቅጣት ከፍ ዝቅ ማለት ካልሆነ በቀር የእምነት ማጉደል ወንጀልን በመደንገግ ረገድ በኢ.ፌ.ዴ. ሪ የወንጀል ህግ እና በወንጀለኛ መቅጫ ህጉ መካከል መሰረታዊ ልዩነት አይታይም።

የተሻሻለዉ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ የ1949 "ኙን" የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አሻሽሎ በመንግስት፣በህዝባዊ ድርጅቶች እና በህብረት ስራ ማህበራት ንብረቶች ላይ የሚፈፀሙ የእምነት ማጉደል ወንጀሎችን ለብቻቸዉ እንደደነገገዉ ሁሉ የሙስና ወንጀሎችን ለብቻቸዉ የሚደነግገዉ ህግ (የሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/2007) ከዋናዉ የወንጀል ህግ ተነጥሎ እንዲወጣ ከተደረገ በኋላ የዕምነት ማጉደል ወንጀል እንደገና በሁለት እንዲከፈል ሆኗል። አንደኛዉ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 675 እና 676//2/ ላይ የተመለከተዉ ሲሆን ሌላኛዉ ደግሞ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 ስር ያለዉ ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀልን የሚመለከተዉ ነዉ።

## 3. የእምነት ማጉደል ወንጀል በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ህግ

የእምነት ማጉደል ወንጀል በንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሚደነግገዉ የወንጀል ህጉ ስድስተኛ መጽሐፍ በምዕራፍ ሁለት ስር በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በተለይ በሚደነግገዉ በክፍል አንድ ስር የሚገኝ ነው።

በኢ.ፌ.ድ. ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በግልፅ እንደተቀመጠዉ አንድ ድርጊት ዕምነት ማጉደል ነዉ ተብሎ በወንጀል የሚያስጠይቀዉ ማንም ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ ፣የሌላ ሰዉ የሆነዉንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠዉን ዋጋ ያለዉን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ፣ ወይም ለሌላ ሰዉ ያደረገ ፣የወሰደ፣ያስወሰደ፣ የሰወረ

ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህንን የመሳሰለዉን ማናቸዉም አድራጎት የፈፀመ እንደሆነ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት የዕምነት ማጉደል ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት ሶስት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች በአንድ ላይ ተሟልተዉ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም፡-1ኛ. ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ማሰብ፣ 2ኛ. ንብረቱ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠ መሆን እና 3ኛ. ነገሩ ዋጋ ያለዉ ወይም ጥሬ ገንዘብ መሆን የሚሉት ናቸዉ፡፡እነዚህን ሶስት መሰረታዊ የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ፍሬ ነገሮች ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፡፡

## 3.1. ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ማሰብ

የእምነት ማጉደል ወንጀል በንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሚደነግገዉ የወንጀል ህጉ ስድስተኛ መጽሐፍ በምዕራፍ ሁለት ስር በተንቀሳቃሽ ንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በተለይ በሚደነግገዉ በክፍል አንድ ስር የሚገኝ መሆኑን ከላይ ተመልክተናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስር የሚፈፀሙ የወንጀል ተግባራትን በተመለከተ ወንጀል አድራጊዉ ለራሱ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ሰዉ ህገ ወጥ የሆነ ጥቅም ለማስገኘት አስቦ የፈፀመዉ ድርጊት ወንጀል መሆኑ በህግ በተደነገገ ጊዜ ድርጊቱ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት የተፈፀመ ነዉ ተብሎ ይገመታል፡፡[7] ድርጊቱ የእምነት ማጉደል ወንጀል በሆነ ጊዜ ደግሞ ተከሳሹ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠዉን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃዉ ያለበትን ሁኔታ ለማሳዬት ወይም ለተገቢዉ አገልግሎት የዋለ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ያልተገባ ጥቅም ለማዋል ሃሳብ እንዳለዉ ግምት ይወሰዳል፡፡[8]

አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለዉ ወንጀሉን የሚቋቋሙት ህጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተማልተዉ ሲገኙ ብቻ እንደሆነ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 23/2/ በግልጽ ይደነግጋል፡፡ አንድ ተከሳሽ ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የጥፍተኝነት ፍርድ የሚሰጥበት ከሳሹ አካል ( ዓቃቢ ህግ) እነዚህ ሶስት ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተዉ የተገኙ መሆኑን ማስረዳት ሲችል ነዉ፡፡ በዕምነት ማጉደል ወንጀል ላይ ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ህጋዊ እና ግዙፋዊ ፍሬ ነገሮች ተሟልተዉ ከተገኙ ወንጀሉ የተፈፀመበትን ሞራላዊ ሁኔታ (ድርጊቱ የተፈፀመዉ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ እንደሆነ) ህጉ በራሱ ግምት የሚወስድበት ስለሆነ ከሳሹ አካል ይህንን ማስረዳት አይጠበቅበትም፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜ ድርጊቱ የተፈፀመዉ

[7] *የኢፌዴሪ ወንጀል ህግ፣* አዋጅ ቁጥር 414/1996 ፣አንቀጽ 663 (1)

[8] *የኢፌዴሪ ወንጀል ህግ፣* አዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 675 (3)

*ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ እንዳልሆነ የማስረዳት ሃላፊነት ከከሳሽ ወደ ተከሳሽ ይዞራል ማለት ነዉ፡፡.*

*እዚህ ላይ ሳይነሳ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ በወንጀል ህጉ አንቀጽ* 675 *ንዑስ ቁጥር* 3 *ላይ ያለዉ "ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠዉን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃዉ ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢዉ አገልግሎት ያዋለዉ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሃሳብ እንዳለዉ ይቆጠራል፡፡" የሚለዉ አገላለፅ ነዉ፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ዉስጥ "ተከሳሹ ሲጠየቅ" የሚለዉ ሃረግ ተከሳሹ መቼ እና ማን ሲጠይቀዉ ነዉ ንብረቱ ያለበትን ሁኔታ ማስረዳት የሚጠበቅበት የሚል ጥያቄን የሚያስነሳ ነዉ፡፡*

*ተከሳሹ (ተጠርጣሪዉ) ስለ ንብረቱ ሁኔታ በግል ተበዳይ፣በፖሊስ ወይም በፍርድ ቤት ሊጠየቅ የሚችልበት አጋጣሚ በመኖሩ ወንጀሉ የሚቋቋመዉ ከየትኛዉ ጥያቄ በኋላ እንደሆነ ግርታን የሚፈጥር ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት በፓሊስ ጣቢያ ሲጠየቅ በቂ ምክንያት ሳያቀርብ ቀርቶ ክስ ከተመሰረተ በኋላ በፍርድ ቤት የእምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ ንብረቱን ለባለቤቱ መልሻለሁ ወይም ለተባለዉ ተግባር አዉያለሁ የሚል መለስ ቢሰጥ እና ይሄዉ ቢረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን በነፃ ሊያሰናብተዉ ይገባል የሚል ክርክር በህግ ባለሙያዎች በኩል ይነሳል፡፡ ለምሳሌ በአመልካች የፍትህ ሚኒስቴር የህዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዓቃቢ ህግ እና በተጠሪ ወ/ሮ ብርቄ ጎዳና መካከል በነበረዉ የከባድ ዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ክርክር ተጠሪ የህዳሴ ቴሌኮም የሽያጭ ሰራተኛ ሆና በምትሰራበት ጊዜ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሷ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት አስባ ጠቅላላ ዋጋቸዉ ብር* 2,077,090 *የሆኑ የማህበሩ የሞባይል ካርድ እና ኢቪዲ ካርድ ምርቶችን ሸጣ ገንዘቡን ገቢ ለማድረግ ከተረከበች በኋላ ሸጣ ገቢ ያደረገችዉ ብር* 2,013,370 *ሲሆን ቀሪዉን ብር* 64200 *ለራሷ ጥቅም ያዋለች በመሆኑ ተጠሪ ከባድ ዕማነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ፈፅማለች በሚል ዓቃቢ ህግ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቧል፡፡*

*ተከሳሽ /ተጠሪ/ የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምኩም ብላ በመካድ ክርክር ያቀረበች በመሆኑ ዐቃቢ ህግ የሰዉና የሰነድ ማስረጃዎችን አስቀርቦ አሰምቷል፡፡ በፍርድ ቤት ቀርበዉ የተሰሙት የዓቃቢ ህግ ምስክሮች በተለይም የማህበሩ ስራ አስኪያጅ የሆኑት የዓቃቢ ህግ* 2ኛ *ምስክር ጎደለ የተባለዉን ገንዘብ ተጠሪ ቀርባ ሙሉ "በሙሉ መመለሷን" ያስረዳ ሲሆን ተጠሪ ገንዘቡን ያጎደለች ስለመሆኑ የሚያረጋግጠዉ የኦዲት ሪፖርትም ለፍርድ ቤቱ ቀርቧል፡፡ መዝገቡን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ የፌደራሉ ከፋተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽ/ተጠሪ/ የኦዲት ሪፖርቱ ሲደርሳት እና መከሰሷን ስታዉቅ ወደ ግል ተበዳይ በመሄድ ያለባትን ገንዘብ ገቢ ስለማድረጓ*

በራሱ በዓቃቢ ህግ ምስክር የተረጋገጠ በመሆኑ “ገንዘቡ ገቢ የሆነዉ ከክስ በፊት ወይም በኋላ መሆኑ በቅድመ ሁኔታነት እንዲታይ ህጉ ያላዘዘ ስለሆነ” ተከሳሽ መከላከል ሳያስፈልጋት ከክሱ በነፃ እንድትሰናበት ሲል ወስኗል፡፡ ዐቃቢ ህግ ይህንን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተዉ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪዋ ያጎደለችዉን ገንዘብ ለግል ተበዳይ የመለሰችዉ መከሰሷን ካወቀች በኋላ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህ ደግሞ ተጠሪ በድርጊቱ መፀፀቷን የሚያሳይ ከሚሆን በቀር የተከሰሰችበትን የወንጀል ድርጊት አልፈፀመችም የሚያስብል አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉን ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነዉ በማለት ሽሯል፡፡[9]

ከላይ ከተመለከተዉ ዉሳኔ መረዳት የሚቻለዉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 675 ንዑስ ቁጥር 3 እና በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 (3) (ለ) ላይ ያለዉ “ተከሳሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠዉን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃዉ ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢዉ አገልግሎት ያዋለዉ መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሃሳብ እንዳለዉ ይቆጠራል፡፡” የሚለዉ አገላለፅ ተከሳሹ ንብረቱን መመለስ ወይም ለተገቢዉ አገልግሎት መዋሉን ማስረዳት ያለበት የወንጀል ክስ ሂደት ከመጀመሩ በፊት እንጅ በወንጀል የሚያስጠይቅ ክስ ከቀረበ በኋላ ንብረቱን መመለስ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስቀር እንዳልሆነ ነዉ፡፡

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ሌላዉ ነገር ለእምነት ማጉደል ወንጀል መቋቋም መሰረታዊ የሆነዉ “ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና የማግኘት ሃሳብ” እጅግ አነስተኛ ዋጋ ወይም ግምት ባላቸዉ ንብረቶች ላይም ተፈፃሚ መሆን አለበት ወይ የሚለዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ የእምነት ማጉደል ወንጀል በሌላ ሰዉ ንብረትና የኢኮኖሚ መብት ወይም በገንዘብ ሊተመኑ በሚችሉ መብቶች ላይ ከሚፈፀሙ ወንጀሎች ዉስጥ የሚመደብ ወንጀል መሆኑን ከላይ ተመልክተናል፡፡ በሌላ ሰዉ የንብረትና የኢኮኖሚ መብት ወይም በገንዘብ ሊተመኑ በሚችሉ መብቶች ላይ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ በደንብ እልፊት የሚያስቀጣ ካልሆነ በቀር በዚሁ ምዕራፍ ስር በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት እንደሚቀጣ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 662/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ለእምነት ማጉደል ወንጀል መቋቋም መሰረታዊ የሆነዉ “ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና የማግኘት ሃሳብ” ትርጉም የሚሰጠዉ በንብረት መብት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን

---

[9] *የፍትህ ሚኒስቴር የሃዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ዓቃቢ ህግ እና ተጠሪ ወ/ሮ ብርቄ ጎዳና (2016) የኢትዮጵያ* ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 242958 ፣*የኢትዮጵያ* ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ (*ያልታተመ*)

አተረጓጎም መርህ በሚያስቀምጠዉ ድንጋጌ አግባብ መሆን እንዳለበት የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ያምናል፡፡

## 3.2. ንብረቱ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠ መሆን

የእምነት ማጉደል ወንጀልን ከሚያቋቁሙት ሀጋዊ ፍሬ ነገሮች መካከል ብዙ ጊዜ የክርክር ምክንያት ሲሆን የሚታዬዉ ይሄዉ "ንብረቱ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠዉን" የሚለዉ ሃረግ ነዉ፡፡ "ለአንድ ለተወነሰ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠዉን" በሚለዉ ሃረግ ዉስጥ በወይም የተያያዙ ሁለት ራሳቸዉን የቻሉ ወንጀሉን የሚያቋቁሙ የህግ ፍሬ ነገሮች አሉ፡፡ አንደኛዉ አደራ ሲሆን ሌላዉ ደግሞ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት እንዲዉል የተሰጠ ንብረትን የሚመለከት ነዉ፡፡

### (ሀ) አደራ

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያሳተመዉ የአማርኛ መዝገበ ቃላት "አደራ" የሚለዉን ቃል እንደ፡ አድርጉልኝ፣ጠብቁልኝ፣ አስቀምጡልኝ...የመሳሰሉት ቃላት የሚያስተላልፉትን መልዕክት በተመለከተ የሚነገር የጠበቀ ተማፅኖ፣ልመና፣ማሳሰቢያ... ቃል ሲል ይተረጉመዋል፡፡[10] በ1952 ዓ.ም የወጣዉ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የፍትሐ ብሄር ህግ በአንቀጽ 2779 ላይ አደራ ማለት አደራ ተቀባይ የተባለዉ አደራ አስቀማጭ የተባለዉን የሌላ ሰዉ ዕቃ ተቀብሎ በአደራ ጠባቂነት እንዲያስቀምጥለት የሚገባበት የዉል ግዴታ ሲል ትርጉም ሰጥቶት እናገኛለን፡፡

ከላይ ከተጠቀሰዉ የፍትሐብሄር ህግ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለዉ አደራ መሰረቱ ዉል ነዉ፡፡ይሁን እንጅ ከሌሎች ዉሎች በተለዬ መንገድ በአደራ የተሰጠዉን ዋጋ ያለዉን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ያደረገ ፣የወሰደ ፣ያስወሰደ ፣የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ አገልግሎት ያዋለ አደራ ተቀባይ ከፍትሐብሄር ሃላፊነት በተጨማሪ በእምነት ማጉደል ወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን ከላይ በመግቢያችን ላይ በተጠቀሱ ህግጋት ላይ ተመልክተናል፡፡

አደራ ልክ እንደ ብድር ዉል፣መያዣ ዉል፣ ኪራይ ዉል፣ሽያጭ ዉል፣የቅጥር ዉል እና መሰል የፍትሐብሄር ግንኙነቶች ሁሉ መሰረቱ ዉል ቢሆንም በአደራ የተቀበሉትን ነገር ለአደራ አስቀማጩ አለመመለስ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በእምነት

[10] አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ *አማርኛ መዝገበ ቃላት (አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ 1993)*

ማጉደል ወንጀል ሊያስጠይቅ የሚችል ተግባር እንደሆነ ከድንጋጌዉ ይዘት መረዳት የሚቻል ነዉ፡፡ ይህን በተመለከተ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካች ተፈሪ ሚናሞ እና በተጠሪ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዓቃቢ ህግ መካከል በነበረዉ የእምነት ማጉደል ወንጀል ክርክር በአደራ የተቀበሉትን ገንዘብ ለአደራ አስቀማጩ አለመመለስ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 675 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በእምነት ማጉደል ወንጀል ሊያስጠይቅ የሚችል ተግባር መሆኑን በአንፃሩ በብድር ዉል የተወሰደ ገንዘብን በዉሉ መሰረት ለመመሰስ ፈቃደኛ አለመሆን የወንጀል ሃላፊነትን ሊያቋቁም አይችልም ሲል አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበት እናገኛለን፡፡[11]

በአደራ የተቀበሉትን ዋጋ ያለዉ ነገር ወይም ገንዘብ ለአደራ አስቀማጩ ካለመመስ ጋር ተያይዞ ሌላዉ የሚነሳዉ ነገር በዉክልና ስልጣን የተረከቡትን ነገር ለወካይ ለመመለስ ፈቃደኛ ያለመሆን ጉዳይ ነዉ፡፡ በዉክልና ስልጣን አማካኝነት ንብረቱ እጁ የገባ ተወካይ በእጁ የገባዉን ንብረት ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኜት ወይም ለማስገኘት አስቦ የወሰደ እንደሆነ ድርጊቱ የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ ፍሬ ነገሮች በሚገኙበት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 675 ንዑስ ቁጥር 1 ስር የሚሸፈን መሆን አለመሆኑ ጉዳይ አከራካሪ ሲሆን ይታያል፡፡ ለምሳሌ በአመልካች ፋሲል በላይነህ እና በተጠሪ የፌደራል ዓቃቢ ህግ መካከል በነበረዉ የወንጀል ጉዳይ ክርክር የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተከታዩን ሃተታ አስቀምጦ በአመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን የጥፍተኝነት ዉሳኔ አፅንቷል፡፡

> አንድ ወኪል በዉክልና ስልጣኑ የወሰደዉን ንብረት ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆነ በወንጀል ህጉ 676/2/ ድንጋጌ የሚጠየቅ ስለመሆኑ ተጠቃሹ ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ ስለሆነም **በዉክልና ስልጣኑ መሰረት አደራ የተቀበለ ተዋዋይ ወገን** እምነት አጉድሏል ተብሎ በወንጀል የሚጠየቅ ስለመሆኑ ስለእምነት ማጉደል የሚደነግጉት የወንጀል ህግ ድንጋጌዎችም ያሳያሉ፡፡በመሆኑም በወንጀል ህግ አንቀጽ 676 (2) መሰረት ወንጀል ነዉ ተብሎ የተጠቀሰዉ የወኪሉ ድርጊት በወንጀል የሚያስጠይቅ መሆኑን ከወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2) እና ተጠቃሹ የወንጀል ህግ አንቀጽ 676(2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ በግልፅ መገንዘብ የምንችለዉ ጉዳይ ነዉ፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች ለጉዳዩ በወንጀል ጥፍተኛ የተባለዉ የፍትሐብሄር ይዘት ብቻ ባለዉ ጉዳይ ነዉ ለማለት ስላልተቻለ የበታች ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ የወንጀል ህግ አንቀጽ 23(2) እና 676(2) ድንጋጌዎች ያገናዘበ ሆኖ

[11] *ተፈሪ ሚናሞ እና የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ዓቃቢ ህግ* (2006) የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 89276፣ (2006)15 ፣ የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ 395

በመገኘቱ ዉሳኔዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በስር ፍርድ ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ አፅንቷል፡፡[12]

የወንጀል ህግ አንቀጽ 676(2) በአንቀጽ 675 ስር የተደነገገዉ የእምነት ማጉደል ወንጀል ከባድ ሁኔታ ነዉ፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 676 (1) እና (2) የተመለከተዉ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል በአንቀጽ 675 (1) ላይ የተመለከተዉን የእምነት ማጉደል ወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር የተከተለ እንደሆነ ከድንጋጌዎች አቀማመጥ መረዳት የሚቻል ነዉ፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 675(1) በአደራ የተረከቡትን ንብረት ለአደራ አስቀማጩ አለመመለስ የእምነት ማጉደል ወንጀል እንደሚያቋቁም ሲደነግግ በዉክልና ስልጣን የተረከቡትን ንብረት ለወካይ አለመመለስን ግን የድንጋጌዉ ማቋቋሚያ አላደረገዉም፡፡ ከላይ በተጠቀሰዉ ዉሳኔ ላይ በዉክልና ስልጣኑ መሰረት በአደራ የተቀበለዉን የሚል ቃል ሰፍሮ እናገኛለን፡፡ ይህ አገላለፅ የዉክልና ስልጣን የአደራ ዉልን ያቋቁማል ወይ? የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነዉ፡፡

በእርግጥ የወንጀል ህግ አንቀጽ 676(2) (ሀ) የእምነት ማጉደል ወንጀሉን የፈፀመዉ ወኪል የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከብዶ እንደሚወሰን አስቀምጧል፡፡ አንድ ወኪል በዉክልና ስልጣኑ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት የሚዉል የወኪል አድራጊዉን ንብረት ሊቀበል ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ የወካይ ንብረት በተወካይ እጅ የገባበት አግባብ ምንጩ የዉክልና ስልጣን እንጅ የአደራ ዉል አይደለም፡፡ የአደራ ዉልና የዉክልና ስልጣን በፍትሐብሄር ህጉም ቢሆን በሁለት የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች ስር ያሉ የተለያዩ ጉዳዮች እንጅ አንድና ተመሳሳይ አይደሉም፡፡ ከላይ በተገለፀዉ ጉዳይ ሰበር ሰሚ ችሎቱ "በዉክልና ስልጣኑ መሰረት አደራ የተቀበለ ተዋዋይ ወገን" የሚል አገላለጽ በመጠቀሙ የዉክልና ስልጣን የአደራ ዉል ያቋቁማል የሚል አረዳድ እንዲኖር የሚያደርግ ነዉ፡፡ ከዚህ ይልቅ በዉክልና ስልጣኑ መሰረት ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት እንዲያዉል እጁ የገባን የወካይ ንብረት ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነ ተወካይ እምነት አጉድሏል ተብሎ በወንጀል ህግ አንቀጽ 676 (2) መሰረት እንዲጠየቅ ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

## (ለ) ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት የተሰጠ መሆን

እምነት ማጉደል ወንጀልን ከሚያቋቁሙት የህግ ፍሬ ነገሮች ዉስጥ "…ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት የተሰጠዉን… "የሚለዉ ፍሬ ነገር ብዙዉን ጊዜ የክርክር ምክንያት ሲሆን ይታያል፡፡ የዚህ ጉዳይ የክርክር ምንጭ የሚነሳዉ በዉል ግንኙነት በተዋዋይ ወገኖች እጅ የሚገባ ንብረት አልያም ጥሬ ገንዘብ ለአንድ ለተወሰነ አገልግለሎት የተሰጠ አድርጎ ከማሰብ

[12] *ፋሲል በላይነህ እና የፌደራል ዓቃቢ ህግ* (2004) የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 67408 ፣ (2005)13 የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ 350

ነዉ። ለምሳሌ በአመልካች ፅጋቡ ወላይ ገብሩ እና የተግራይ ክልል ዓቃቢ ህግ መካከል በነበረዉ ክርክር አመልካች ከመቐለ ወደ ሃዉዜን ሲሚንቶ እንዲያጉዋጉዝ በተሰጠዉ ሃላፊነት መሰረት ሲሚንቶዉን አጓጉዞ በጊዜዉ ማስረከብ ሲገባዉ ሲሚንቶዉን ሽጦ ለግል ጥቅሙ በማዋሉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 675(1) 'ን' በመተላለፍ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅሟል በሚል ክስ ቀርቦበት እናገኛለን። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ የክልተ በለሳ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ጉዳዩ የፍትሐ ብሄር እንጅ የወንጀል ሃላፊነት አያስከትልም በማለት ተከሳሽን በነፃ አሰናብቷል። ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አፅንቷል።ጉዳዩ በሰበር የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ሰበር ሰሚ ችሎት ተከሳሽ ሲሚንቶዉን በዉሉ መሰረት ያላስረከበ መሆኑ ተረጋግጧል የሚል ምክንያት ተከሳሽ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 675(1) ስር ጥፍተኛ አድርጎታል።

ጉዳዩ በሰበር የቀረበለት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት "አመልካች በገባዉ የእቃ ማጓጓዝ ዉል መሰረት ሲሚንቶዉን በሙሉ ጥንቃቄ በማጓጓዝ በተወሰነዉ ጊዜና ስፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታዉን አለመወጣቱ አመልካችን በፍትሐብሄር ተጠያቂ ከመሆን አልፎ በወንጀል ህግ አንቀጽ 675 (1) የተመለከተዉን በመተላለፍ በእምነት ማጉደል ወንጀል የሚያስጠይቃቸዉ ነዉ ወይ?" የሚል ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን መርምሯል።

የወንጀል ህግ አንቀጽ 675 ይዘት አንድ ሰዉ አንድን ንብረት ለአንድ አገልግሎት ለማዋል በኃላፊነት ተረክቦት ንብረቱን ለተባለዉ አገልግሎት ሳያዉል ሲቀር በእምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቅ መሆኑን የሚመለከት እንጅ በማጓጓዝ ዉል መሰረት የሚገባዉን ጥንቃቄ አድርጎ ዕቃዉን በማጓጓዝና በተወሰነዉ ጊዜና ስፍራ አድርሶ ለተቀባዩ የማስረከብ ግዴታዉን ያልተወጣ አጓዥ በእምነት ማጉደል ወንጀል እንዲጠየቅ የድንጋጌዉ ይዘትና መንፈስ አያሳይም በማለት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሰበትን ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነዉ ሲል ሰበር ሰሚ ችሎቱ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል።[13]

በሌላ መዝገብ በአመልካች ብሩክ ሚካዔል እና በተጠሪ የፌደራል ዓቃቢህግ መካከል በነበረ ክርክር ተከሳሽ በባለንብረቱ ፈቃድ ጠግኖ ለመመለስ ዕቃ ከወሰደ በኋላ ንብረቶቹን ሳይመልስ በመቅረቱ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 675(1) በመተላለፍ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅሟል በሚል በፌደራሉ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ክስ ይመሰርታል። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ የፌደራሉ የመጀመሪያ ፍርድ ቤት እና በይግባኝ የተመለከተዉ ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ተከሳሽን በተከሰሰበት የእምነት ማጉደል ወንጀል ጥፍተኛ ነዉ ሲሉ ዉሳኔ ሰጥተዋል።

---

[13] *ፅጋቡ ወላይ እና የትግራይ ክልል ዓቃቢ ህግ* (2006) የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 98647፣ (2007) 16 የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ 260

ጉዳዩ በሰበር የቀረበለት የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዉሉ መሰረት ግዴታዉን ያልተወጣ ተዋዋይ ወገን በዉሉ አግባብ በፍትሐብሄር ከሚጠየቅ በቀር ድርጊቱ የወንጀል ሃላፊነትን አያስከትልም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር አመልካችን በነፃ አሰናብቷል፡፡[14]

በሌላ መዝገብ በአመልካች ያሲን አህመድ መሐመድ እና በፌደራል ዓቃቢ ህግ መካከል በነበረዉ ክርክር አመልካች ብር 10000 (አስር ሽህ ብር) የሚያወጣ ቆርቆሮ ገዝቼ አመጣለሁ በሚል ከግል ተበዳይ ገንዘብ ከወሰደ በኂላ ቆርቆሮዉንም ሆነ ገንዘቡን ለግል ተበዳይ ስላልመለሰ የወንጀል ህግ አንቀጽ 675 (1) የተመለከተዉን በመተላለፍ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅሟል በሚል ክስ የቀረበበት ሲሆን ጉዳዩን በየደረጃዉ የተመለከቱት ፍርድ ቤቶችም ተከሳሽን በተከሰሰበት የእምነት ማጉደል ወንጀል ክስ ጥፍተኛ ነዉ ሲሉ ዉሳኔ ሰጥተዋል፡፡

ጉዳዩን በሰበር የተመለከተዉ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት "አመልካች የግል ተበዳይ ለቆርቆሮ መግዣ በማለት የሰጠዉን ገንዘብ ወስዶ አስቀርቶታል፡፡በገንዘቡ ቆርቆሮዉን አልገዛበትም ወይም ገንዘቡን ለግል ተበዳይ አልመለሰለትም ፡፡ ተከሳሽ ገንዘቡን እስካልመለሰ ወይም ለተባለዉ አገልግሎት ስለማዋሉ አስካላስረዳ ድረስ በወንጀል ህግ አንቀጽ 675(1) የተመለከተዉን ወንጀል ፈፅሟል በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ አፅንቷል፡፡"[15] ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የፍርድ ቤት ዉሳኔዎች የምንረዳዉ አንድ ወሳኝ ነጥብ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት እንዲያዉል በዉል ግዴታ ዋጋ ያለዉን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ ከሌላ ሰዉ የተቀበለ ሰዉ ተጠያቂነቱ በዛዉ የዉል ግዴታዉን ባቋቋመዉ የፍትሐብሄር ህግ የተወሰነ መሆኑን ነዉ፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባዉ ጉዳይ የዉል ግዴታዉ የተፈጠረዉ በጽሁፍ በተረጋገጠ ሰነድ አለያም በቃል መሆኑ የጉዳዩን ባህርይ በመበየን ረገድ ጠቀሜታዉ እምብዛም መሆኑን ነዉ፡፡

## 3.3. ነገሩ ዋጋ ያለዉ ወይም ጥሬ ገንዘብ መሆን

የእምነት ማጉደል ወንጀልን ከሚያቋቁሙት ህጋዊ ፍሬ ነገሮች ዉስጥ "ዋጋ ያለዉን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ" የሚለዉ ፍሬ ነገር በተግባር እምብዛም የክርክር ምክንያት ሲሆን አይታይም፡፡ የኢ.ፌ.ዴ. ሪ ወንጀል ህግ ከቀደምቶቹ የወንጀል ህግጋት ለየት ባለ መንገድ "ነገር (thing) ለሚለዉ ቃል "ዋጋ ያለዉ" የሚል ገላጭ አስገብቶ ዋጋ ያለዉ ነገር ይላል፡፡ የ1949

---

[14] *ብሩክ ሚካኤል እና የፌደራል ዓቃቢ ህግ (2003)* የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 65054፣ (2004)12 የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ 261

[15] *ያሲን አህመድ መሐመድ እና የፌደራል ዓቃቢ ህግ* (2003) ፣የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 64813 ፣ (2004)12 የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ 215

"ኙ" የወንጀል ህግ "ነገር" (*Property)* የሚል ቃል ብቻ የሚጠቀም የነበረ ሲሆን የተሻሻለዉ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ደግሞ ንብረት (*Property)* የሚል ቃል ይጠቀም ነበር፡፡ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 ከወንጀል ህጉ ተመሳሳይ የሆነ ቃል ይጠቀማል፡፡

በንብረት ህግ "*goods, chattles, property, thing*" የሚሉ ቃላት የራሳቸዉ የሆነ ትርጉም ያላቸዉና አንዱ ከሌላኛዉ የሚለዩ ናቸዉ፡፡ የእምነት ማጉደል ወንጀል ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኜት በማሰብ የሌላ ሰዉ የሆነዉን ዋጋ ያለዉን ነገር መዉሰድ ፣ማስወሰድ፣መሰወር እና መሰል ተግባራትን የሚመለከት በመሆኑ "ዋጋ ያለዉ ነገር" የሚለዉ አገላለፅ ንብረት (*Property)* ለማለት እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

## 3.4. ከባድ እና ቀላል የእምነት ማጉደል ወንጀል

የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙት መሰረታዊ ህጋዊ ፍሬ ነገሮች ከላይ የተመለከትናቸዉ ሲሆኑ የዕምነት ማጉደል ወንጀል በፈፃሚዉ ማንነት ወይም ወንጀሉ የተፈፀመበትን ንብረት እየታዬ ከባድ ወይም ቀላል ተብሎ ሊፈረጅ ይችላል፡፡

የእምነት ማጉደል ወንጀሉን የፈፀመዉን ሰዉ ማንነት መሰረት አድርጎ በከባድነት ከተቀመጠዉ የእምነት ማጉደል ወንጀል አንዱ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 (1) ላይ የተመለከተዉ የመንግስት ባለስልጣን ወይም ሹም ወይም የህዝብ ባለአደራ ወይም ተመራጭ የሚፈፅመዉ የእምነት ማጉደል ወንጀል ነዉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) እና (ሐ) ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ ወንጁሉን ከባድ ለማለት የተጠቀመዉ መመዘኛ የፈፃሚዎቹን ማንነት መሰረት አድርጎ ነዉ፡፡ ሞግዚት፣ንብረት ጠባቂ፣ ሂሳብ አጣሪ ፣የህግ ወይም የገንዘብ አማካሪ ፣ወኪል፣ጠበቃ፣ የንብረት አስተዳዳሪ ወይም በተሰጠዉ ሃላፊነት ወይም ስራ ንብረቱ በእጁ የገባ ሰዉ፣ስለ ገንዘብ መሰብሰብ ለህዝብ ጥሪ የሚያደርግ ሰዉ ሆኖ ለራሱ ወይም ለአንድ የንግድ ማህበር ወይም ለባንክ ወይም ለሌላ ድርጅት ጥቅም ሲል ገንዘብ ወይም ዋጋ ያላቸዉን ነገሮች የሚሰበስብ ሰዉ የሚፈፅመዉ የእምነት ማጉደል ወንጀል ከባድ በመባል ተፈርጇል፡፡

በሌላ በኩል የእምነት ማጉደል ወንጀሉ የተፈፀመበትን ንብረት መሰረት በማድረግ ከባድ ተብሎ የተፈረጀዉ የእምነት ማጉደል ወንጀል በወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 ንዑስ ቁጥር 1 ላይ በመጀመሪያዉ እና ሁለተኛዉ መስመር ላይ የተቀመጠዉ መመዘኛ ነዉ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ፈፃሚዉ ማንም ይሁን ማን ወንጀሉ የተፈጸመዉ በመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ንብረት ላይ የሆነ እንደሆነ ድርጊቱ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁም ይሆናል፡፡

## 4. የእምነት ማጉደል ወንጀል በሙስና ወንጀሎች አዋጅ

የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 881/2007 ከመዉጣቱ በፊት የሙስና ወንጀሎች አጠቃላይ ወንጀልን በሚደነግገዉ በ1996 ዓ.ም በወጣዉ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሚካራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ ዉስጥ ተካትተዉ ይገኙ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ የሙስና ወንጀሎች በፈጣን ሁኔታ የመቀያየር ባህሪ ስላላቸዉ አጠቃላይ ወንጀሎችን በሚደነግገዉ የወንጀል ህግ (ኮድ) ዉስጥ እንዲካተቱ ከማድረግ ይልቅ ራሱን በቻል አዋጅ እንዲደነገጉ ማድረግ ተመራጭ ሆኖ በመገኘቱ የሙስና ወንጀሎች ራሱን በቻለ አዋጅ ለብቻቸዉ ተደንግገዉ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡[16]

ቀደም አጠቃላይ ወንጀሎችን በሚደነግገዉ የኢ.ፌ.ዲ. ሪ የወንጀል ህግ ዉስጥ ተካትተዉ የነበሩ እና የሙስና ወንጀል ባህርይ ያላቸዉ ድንጋጌዎች በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ዉስጥ እንዲካተቱ ሲደረግ በወንጀል ህጉ ላይ የነበሩት ተመሳሳይ ድንጋጌዎች እንዳንዶቹ ሙሉ በሙሉ ተሽረዋል ( *Repealed Provisions)* ሌሎቹ ደግሞ ይዘታቸዉ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ እንከተሸፈነ ድረስ ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ተደርጓል (*Inapplicable Provisions*)፡፡[17] በአዋጁ ሙሉ በሙሉ ከተሻሩ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ዉስጥ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀሎችን የሚደነግገዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 ንዑስ አንቀጽ 1 ይገኝበታል፡፡

በተሻረዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የነበረዉ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር እና እሱን በተካዉ በሙስና ወንጀሎቸ አዋጁ አንቀጽ 31 ላይ በተቀመጠዉ ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ጋር መሰረታዊ ልዩነት የሚታይበት ነዉ፡፡ ለንፅፅር ይረዳ ዘንድ ሁለቱን አንቀጾች ከዚህ እንደሚከተለዉ እናስቀምጣቸዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ. ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 676 ንዑስ አንቀጽ 1 እንዲህ ይነበባል፡-

---

[16] *የኢፌዲሪ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ፣* አዋጅ ቁጥር 881/2007 *መግቢያዉን ይመልከቱ*

[17] ሙሉ ለሙሉ የተሻሩት ድንጋጌዎች በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 35 ላይ የተዘረዘሩት ሲሆኑ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 379፤381፣ከ 402-419፣ ከ 427-431፣468 እና 676(1) ናቸዉ፡፡ በአንፃሩ በሙስና ወንጀሎች አዋጁ በተሸፈኑ ገዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም ተብለዉ የተዘረዘሩት የወንጀል ህጉ አንቀፆች የወንጀል ህጉ አንቀጽ 696 እና ሃላፊነትን አላግባብ መገልገልን፣ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ማግኘትን ወይም ማስገኘትን እና በሌላ ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ማድረስን ለመቅጣት የተደነገጉ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ናቸዉ፡፡

> *'…ወንጀሉ የተፈፀመዉ ፣ **በመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ንብረት ላይ ከሆነ** ወይም ወንጀሉን የፈፀመዉ የመንግስት ባለስልጣን ወይም ሹም ፣የህዝብ ባለአደራ ወይም ተመራጭ እንደሆነ…'፣* (ሰረዝ የተጨመረ)

የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1 በአንፃሩ እንዲህ ይነበባል፡

> *ማንኛዉም የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኜት በማሰብ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት የሆነዉንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠዉን ዋጋ ያለዉን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ፣ወይም ለሌላ ሰዉ ያደረገ ፣የወሰደ፣ያሰወሰደ፣የሰወረ፣ወይም ለራሱ ወይም ለልላ ሰዉ አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለዉን ማናቸዉንም አድራጎት የፈፀመ እንደሆነ ፣*

በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 መሰረት ከባድ የዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት አምስት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች በአንድ ላይ ተሟልተዉ መገኜት ይኖርባቸዋል፡፡እነሱም፡-

*ሀ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ መሆን*

*ለ/ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኜት ወይም ለማስገኜት ማሰብ*

*ሐ/ ንብረቱ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት መሆን*

*መ/ ንብረቱ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠዉ ከሆነ*

*ሠ/ ንብረቱ ዋጋ ያለዉ ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ ከሆነ*

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31 መሰረት አንድ ሰዉ በከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ሊጠየቅ የሚችለዉ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ሆኖ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለልላ ሰዉ ለማስገኜት በማሰብ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት የሆነዉንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠዉን ዋጋ ያለዉን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ፣ወይም ለሌላ ሰዉ ያደረገ ፣የወሰደ፣ያሰወሰደ፣የሰወረ፣ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለዉን ማናቸዉንም አድራጎት የፈፀመ እንደሆነ ነዉ፡፡ ከተሻረዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676/1/ በተለዬ መልኩ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ የንብረቱ ባለቤት

መንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት መሆኑ ብቻዉን የወንጀሉ ማቋቋሚያ አላደርገዉም፡፡ ይልቁንም የድርጊቱ ፈፃሚዎች የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ መሆን እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡

# 5. በወንጀል ህጉ ዕምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ ፍሬ ነገሮች ተፈፃሚነት አድማስ

## 5.1. በወንጀል ህጉ ዕምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ ፍሬ ነገሮች በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ከባድ ዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀልን ከሚያቋቁሙት ፍሬ ነገሮች አንፃር

ከዚህ በላይ እንደተመለከተዉ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚደነግገዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676/1/ በሙስና ወንጀሎች አዋጁ የተሻረ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ይህን ድንጋጌ የሻረዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ በአንቀጽ 31 ላይ ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀልን የሚያቋቁሙ ከላይ በክፍል አንድ ላይ የተመለከትናቸዉን አምስት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮችን አስቀምጧል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰዉ በተሻረዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676/1/ ላይ የነበረዉ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀልን የሚያቋቁመዉ ድንጋጌ ንብረቱ የመንግስት ወይም ህዝባዊ መሆንን እንጅ የድርጊቱ ፈፃሚ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅቱ ሰራተኛ መሆንን የወንጀል ድርጊቱ ፍሬ ነገር ማቋቋሚያ የሚያደርግ አልነበረም፡፡ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ከወጣበት አላማና ከሙስና ወንጀሎች መሰረታዊ ባህሪ አንፃር አጠቃላይ ወንጀሎችን ከሚደነግገዉ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች የተለዩ የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር ማካተቱ የሚጠበቅ ነዉ፡፡ ያምሆኖ ከሙስና ወንጀሎች ባህርይ የተለዩ ይዘት ጭምር አካቶ የነበረዉን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676/1/ በመሻር በምትኩ የሙስና ወንጀሎችን ብቻ በሚደነግገዉ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ በአንቀጽ 31 ላይ እንዲካተት ሲደረግ በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል የይዘት ልዩነት በመኖሩ የሙስና ወንጀል የሚያቋቁመዉን ከባድ የእምነት ማጉደል እና በመደበኛዉ የወንጀል ህግ በከባድ የእምነት ማጉደል ሊያስጠይቁ የሚችሉ የወንጀል ድረጊቶችን በመለዩት ረገድ በህግ ባለሙያዎች መካከል የአረዳድ ልዩነቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

ከላይ እንደተመለከተዉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 /1/ ላይ የድርጊቱ ፈፃሚ ማንነት ከግምት ዉስጥ ሳይገባ በመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ንብረቶች ላይ የእምነት ማጉደል ወንጀል የተፈፀመ እንደሆነ ድርጊቱ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀልን ያቋ　　　ቁም ነበር፡፡

በአንፃሩ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 31 ላይ የተቀመጠዉ የከባድ ዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር የድርጊቱ ፈፃሚ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ መሆንን የሚጠይቅ ነዉ፡፡ የመንግስት ሰራተኛ እና የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የሚሉት ሃረጋት በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ላይ እንደ ቅደም ተከተላቸዉ ተከታዩ ትርጉም ተሰጥቷቸዉ እናገኛለን፡-

> *የመንግስት ሰራተኛ ማለት በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት ዉስጥ ተቀጥሮ፣ተሹሞ፣ተመድቦ ወይም በህዝብ ተመርጦ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ሥራን የሚያከናዉን ማንኛዉም ሰዉ ሲሆን የስራ አመራር ቦርድ አባልን ይጨምራል፡፡*[18]

> *የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ማለት በህዝባዊ ድርጅት ዉስጥ ተቀጥሮ ፣ ተመድቦ ወይም በአባላት ተመርጦ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የሚሰራ ሰራተኛ ሲሆን የድርጅቱን መሪ ፣የዳሬክተሮች ቦርድ አባልን፣የአክሲዮን ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት የሚያደራጅ ሰዉን ወይም ኮሚቴን ያካትታል፡፡*[19]

*የመንግስት ሰራተኛ እና የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ከሚሉት ሃረጋት በተጨማሪ በሙስና* ወንጀሎች አዋጅ ሌላዉ ትርጉም ተሰጥቶበት የምናገኘዉ የመንግስት መስሪያ ቤት እና ህዝባዊ ድርጅት የሚለዉ ነዉ፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 በተሰጠዉ ትርጓሜ መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤት ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደር እና የፌደራል ወይም የክልል መንግስት ስራዎች የሚከናወኑበት ማናኛዉም መስሪያ ቤት ነዉ፡፡ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ ደግሞ ህዝባዊ ድርጅት ለሚለዉ ቃል የተሰጠዉ ትርጉም 'አግባብ ከአባላት ወይም ከህዝብ የተሰበሰበ ወይም ለህዝባዊ አገልግሎት ታስቦ የተሰበሰበ ገንዘብ ፣ንብረት ወይም ሌላ ሃብትን የሚያስተዳድር አካልንና አግባብነት ያለዉ ኩባንያን[20] የሚያካትት የግል ዘርፍ ነዉ' የሚል ነዉ፡፡

---

[18] *የኢፌዲሪ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ፣* አዋጅ ቁጥር 881/2007 ፣ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2

[19] *የኢፌዲሪ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ፣* አዋጅ ቁጥር 881/2007 ፣አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 5

[20] አግባብነት ያለዉ ኩባንያ ማለት በህዝባዊ ድርጅት የተቋቋመ ሃላፊነቱ የተወሰነ ኩባንያ ሲሆን እንደህ አይነት ኩባንያ ከሌሎች ጋር ከሌሎች ጋር የሚያቋቁመዉን የሽርክና ማህበር እንደሚያጠቃልል በሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/2007 አንቀጽ 2 (6) ላይ ተደንግጓል፡፡ አግባብነት ያለዉ ኩባንያ የሚለዉ አገላለፅ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርን (PLC) የሚመለከት መሆን አለመሆኑ በህግ ባለሙያዎች ዘንድ አከራካሪ ጉዳይ ሆኖ የቆየ ሲሆን በቅርቡ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 203654 ሐምሌ 30 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት ኃላ/የተ/የግ/ማህበር የገንዘብ ምንጩ ከአባላት በተሰበበሰበ አክሲዮን በመሆኑ በድርጅቱ ላይ የእምነት ማጉደል ወንጀል ሲፈፀም ጉዳዩ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ መታየት እንዳለበት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በሌላ በኩል የአብክመ የተሻሻለዉ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 237/2008 በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ 'የመንግስት መስሪያ ቤት ማለት በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በጀት የሚተዳደርና የክልሉ መንግስት ስራዎች የሚከናወኑበት ማናቸዉም መስሪያ ቤት ሲሆን የገጠር ቀበሌ አስተዳደሮችን አይጨምረም።'[21] የሚል ትርጉም እናገኛለን።

በአማራ ክልል የመንግስት አስተዳደር እርከን በክልል፣በወረዳዎች እና በቀበሌዎች የተዋቀረ እንደሆነ የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል። ቀበሌዎች በክልሉ የአስተዳደር እርከን የታችኛዉ መዋቅር ላይ የሚገኙ የመንግስት ተቋማት ሲሆኑ የቀበሌ ምክር ቤት፣ የቀበሌ አስተዳደር ም/ቤትና የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የሚባሉ አበይት አካላት እንደሚኖራቸዉ በዚሁ ህገ መንግስት አንቀጽ 96 (2) ስር ተቀምጧል።

ከላይ እንደተመለከትነዉ እነዚህ በታችኛዉ የክልሉ መንግስት አስተዳደደር ተቋም ስር የሚገኙ የገጠር አስተዳደር ቀበሌዎች ለሙስና ወንጀል ዓላማ ሲባል እንደ መንግስት መስሪያ ቤት አልተቆጠሩም። የክልሉ ህገ መንግስት "የታችኛዉ የመንግስት አስተዳደር እርከን" በማለት የሚጠራቸዉን የገጠር ቀበሌ መስተዳድር አካላት የክልሉ የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ የመንግስት መስሪያ ቤት በሚለዉ ትርጉም ስር እንዳይጠቃለሉ ያደረገበት ምክንያት (*Rational*) ምንድነዉ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። የአብክመ ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ መስሪያ ቤት የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳሬክቶሬት ለሰ/ጎንደር ዞን ዓቃቢ ህግ መምሪያ በሰጠዉ መሪ ትዕዛዝ ላይ የቀበሌ መስተዳድር አካላት በልዩ ሁኔታ ከአዋጁ ዉጭ የሆኑበትን ምክንያት ሰራተኞቹ በአብዛኛዉ ያልተማሩ እና አርሶ አደሮች በመሆናቸዉ በተሰጣቸዉ ሃላፊነት በመንግስትና ህዝብ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ አይደለም በማለት እና የክልሉ ፀረ-ሙስና ኮሚሽንም ተደራሽ አይሆንም ከሚል መነሻነት ሊሆን እንደሚችል ግምቱን አስቀምጧል።[22]

ከላይ የተመለከተዉን የመንግስት መስሪያ ቤት እና የመንግስት ሰራተኛ ትርጉም ይዘን የሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 ላይ የተደነገገዉን ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ስንመለከተዉ የወንጀሉ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ

[21] *የአብክመ የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ* ፣ አዋጅ ቁጥር 237/2008፣ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1
[22] የአብክመ ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ መስሪያ ቤት የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳሬክቶሬት፣ ሙ/ወ/ጉ 64/2013፣ ቀን 07/08/2013 ዓ.ም

ላልሆኑ ሰዎች እና ለገጠር ቀበሌ መስተዳደር አካላት ተፈፃሚ የሚሆንበት ዕድል እንደሌለ መገንዘብ የሚቻል ነዉ፡፡

የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅ ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ አዋጅ የተሻሩት የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ተግባራዊ ስለማይሆኑ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ያልሆነ ሰዉ በመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ንብረት ላይ የእምነት ማጉደል ወንጀል ሲፈፅም ተጠያቂ ሊሆን የሚችልበት የህግ ድንጋጌ አለ ወይ? የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ሆኗል፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 676/1/ ላይ በተቀመጠዉ አግባብ ተጠያቂ እንዳይሆኑ ይህ ድንጋጌ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 35 መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 መሰረት በከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ይጠየቃሉ እንዳይባል ግለሰቦቹ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ስላልሆኑ የድንጋጌዉን ማቋቋሚያ ፍሬ ነገር እንደማያሟሉ ከላይ በዝርዝር ተመልክተነዋል፡፡

የእምነት ማጉደል ወንጀሉ የተፈፀመዉ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ንብረት ላይ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ፈፃሚዎቹ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆኑም በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ የሚል ክርክር የሚያነሱ የህግ ባለሙያዎች አሉ፡፡ የዚህ ክርክር መነሻ በመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ንብረት ላይ የሚፈፀም የእምነት ማጉደል ወንጀል ሁሉ የሙስና ወንጀልን ያቋቁማል ከሚል አረዳድ የመነጨ ነዉ፡፡የሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 "ን" በዚህ መንገድ የሚተርጉሙ ሰዎች ከባድ የእምነት ማጉደል የሚለዉን የድንጋጌዉን አርዕስት ብቻ ተመልክተዉ ካልሆነ በቀር ከላይ የተጠቀሰዉ ዝርዝር የድንጋጌዉ ማቋቋሚያ ይህን የክርክር መስመር የሚደግፍ አይደለም፡፡ በዚህ ድንጋጌ አግባብ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ያልሆነ ሰዉ በከባድ ዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚችለዉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 33 መሰረት በልዩ ወንጀል ተካፋይ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነዉ፡፡

የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት የሆነ ንብረቱ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ ሊሰጥ የሚችለዉ ለራሱ ለተቋሙ ሰራተኞች ስለሚሆን በዚህ አጋጣሚ ዕምነት አጉድለዉ ከተገኙ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 መሰረት በከባድ እምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ተጠያቂ ስለሚደረጉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 (1) ላይ በተመለከተዉ ዓይነት የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ያልሆኑ ሰዎችን ሁሉ ማካተት አስፈላጊ አይሆንም የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል፡፡ ይህ የመከራከሪያ ሃሳብ መሬት ላይ ያለዉን ሃቅ ያላገናዘበ እንደሆነ የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ያምናል፡፡ ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲዉሉ በማሰብ መንግስት በርካታ ንብረቶችን የመንግስት ሰራተኛ ላልሆኑ ግለሰቦች የሚሰጥበት አጋጣሚ ሰፊ

ነዉ፡፡ ለምሳሌ የአካባቢያቸዉን ሰላምና ፀጥታ እንዲያስከብሩ የጦር መሳሪያ ከመንግስት የሚሰጣቸዉ ግለሰቦች አሉ፡፡እነዚህ ግለሰቦች ለፀጥታ ስራ ከመንግስት የተሰጣቸዉን የጦር መሳሪያ በመሸጥ ለግል ጥቅማቸዉ አዉለዉ በተገኙ ጊዜ ተጠያቂ ሊሆኑበት የሚገባዉን የወንጀል ህግ ድንጋጌ በመለየት ረገድ በህግ ባለሙያዎች ዘንድ ሰፊ የሆነ ልዩነት የሚታይበት ነዉ፡፡ ለምሳሌ በአብክመ ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ የሰሜን ጎንደር ዞን ዓቃቢ ህግ መምሪያ በስሩ ለሚገኙ ሁሉም የወረዳ ዓቃቢ ህግ ጽ/ቤቶች ባስተላለፈዉ መመሪያ በቀበሌ መዋቅር አካላት የሚፈፀሙ ሙስና ነክ ወንጀሎችን በተመለከተ ያለዉ አሰራር ከቦታ ቦታ የሚለያይ መሆኑን ጠቅሶ ወጥ የሆነ የህግ ትርጉም እስከሚሰጥ ድረስ የመንግስት የጦር መሳሪያ የታጠቁ ግለሰቦች የቀበሌ አመራሮች ወይም ሚሊሻዎች የጦር መሳሪያዉን ለመንግስት ካልመለሱ ወይም ከወሰዱ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 703 መሰረት በሌላ ሰዉ ጥቅም የስራ አመራር ላይ ከባድ ጉዳት ማድረስ በሚል ክስ እንዲመሰርትባቸዉ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡[23]

በአ.ብ.ክ.መ ሰሜን ሸ/ዋ ዞን ዓቃቢ ህግ መምሪያ ሥር በሚገኙ የወረዳ ዓቃቢ ህግ ጽ/ቤቶች መካከልም ከላይ እንደተመለከትነዉ እንደ ሰሜን ጎንደሩ ሁሉ የቀበሌ አመራሮቸ እና ሚሊሽዎች ከመንግስት ለፀጥታ ስራ የተረከቡትን የጦር መሳሪያ እንዲመልሱ በተጠየቁ ጊዜ ለመመለስ ፈቃደኛ ሆነዉ ባልተገኙ ግለሰቦች ላይ ክስ የሚመሰረትበት የህግ ድንጋጌ ከወረዳ ወረዳ የተለያዬ መሆኑን የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ተመልክቷል፡፡[24] ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዚህ በአብክመ በሰሜን ሸዋ ዞን እንዲህ አይነት የወንጀል ድርጊቶች ተፈፅመዉ በተገኙ ጊዜ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 ን በመጥቀስ በከባድ ዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል በከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሰ የመመስረት አሰራር ይታያል፡፡ ለምሳሌ በከሳሽ የሰሜን ሸዋ ዞን ዓቃቢ ህግ እና በተከሳሽ ተክሉ ገበየሁ እሸቴ መካከል በነበረዉ ክርክር ተከሳሽ የአካባቢዉን ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር ከሞጃና ወደራ ሚሊሻ ጽ/ቤ አንድ ሱኪ ጠመንጃ ከመሰል አስር ጥይቶች ጋር ወጪ አድርጎ ከወሰደ በኋላ የጦር መሳሪያዉን ይዞ እንዲቀርብ በተጠየቀ ጊዜ መሳሪያዉን ማቅረብ ያልቻለ በመሆኑ ዓቃቢ ህግ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1 ን ጠቅሶ በተከሳሽ ላይ ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ክስ አቅርቦ እናገኛለን፡፡ የክስ ቻርጁ የቀረበለት የአብክመ ሰ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሹ

---

[23] በአብክመ ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ የሰሜን ጎንደር ዞን ዓቃቢ ህግ መምሪያ ፣ ሰ/ጎ/ዞ/ዐ/መም 160/2013፣ ቀን 25/03/2013 ዓ.ም

[24] ለምሳሌ የ 2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ አመት በሰ/ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ ስር የሚገኙ የወረዳ ፍትህ ጽ/ቤቶች ሪፖርት በቀረበበት ጊዜ ጉዳዩ ተነስቶ የነበረ ሲሆን የቀበሌ አመራሮች እና ሚሊሽዎች ከመንግስት ለፀጥታ ስራ የተረከቡትን የጦር መሳሪያ እንዲመልሱ በተጠየቁ ጊዜ ለመመለስ ፈቃደኛ ሆነዉ ባልተገኙ ግለሰቦች ላይ አንዳንድ ፍትህ ጽ/ቤት (ለምሳሌ ሃገረማርያም ከሰም ወረዳ ፍትህ ጽ/ቤት) የወንጀል ህጉን አንቀጽ 676 (2) (ሀ) በመጥቀስ ለወረዳ ፍርድ ቤት ክስ ሲያቀርቡ ሌሎቹ ደግሞ (ለምሳሌ ሞጃና ወደራ ወረዳ እና ደብረብረሃን ፍትህ ጽ/ቤቶች) ድርጊቱ ከባድ ዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀልን ያቋቁማል በማለት ለፍትህ መምሪያዉ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ስራ ሂድት የምርመራ መዝገቡን ይልካሉ፡፡

የአካባቢዉን ሰላምና ፀጥታ ለማስከበር በክሱ ላይ የተጠቀሰዉን የጦር መሳሪያ ከመንግስት የተረከበ መሆኑ በሰዉና በሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል በማለት ተከሳሽ በተከሰሰበት ከባድ የዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ጥፋተኛ ነዉ ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡[25] በዚህ መዝገብ ላይ በዓቃቢ ህግ በኩል በማስረጃ የተረጋገጠዉ ፍሬ ነገር ተከሳሽ ንብረትነቱ የመንግስት የሆነ የጦር መሳሪያ ለፀጥታ ስራ እንዲያዉል የተረከበ መሆኑ እንጅ ተከሳሹ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ ይልቁንም ፍርድ ቤቱ በተከሳሽ ላይ የተወነሰነዉን የእስር ቅጣት ለማገድ እንደ ምክንያት ከወሰዳቸዉ ፍሬ ነገሮች ዉስጥ "ተከሳሹ ቤተሰባቸዉን የሚያስተዳድሩት በግብርና ስራ መሆኑ የእስር ቅጣቱ ቢፈፀም ቤተሰባቸዉ ለችግር የሚዳርግ መሆኑ" የሚለዉ አገላለጽ ተከሳሽ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነዉ፡፡

አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙ ህጋዊ፣ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ እንደሆነ ከወንጀል ህጉ አንቀፅ 23(2) ላይ በግልፅ የተደነገገ ሲሆን በህግ ላይ ከተደነገጉት ወንጀሎች ጋር ይመሳሰላል በማለት ወንጀልነቱ በግልፅ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት ፍርድ ቤት እንደወንጀል ሊቆጥረዉ እንደማይችል በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 ይደነግጋል፡፡ አንድ ተከሳሽ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 31 ላይ በተመለከተዉ አግባብ ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው የወንጀሉ ሟቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ውስጥ የወንጀል ድርጊቱ ፈፃሚ የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ሲሆንና የወንጀል ድርጊቱ የተፈፀመበት ንብረት የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ንብረት ሆኖ ሲገኝ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡ የዚህ ድንጋጌን አፈፃፀም አሁን ባለው የፍ/ቤቶች አሰራርን ስንመለከት ግን የመንግሰት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ያልሆነ ሰዉ ጭምር የመንግስት ንብረት የሆነ የጦር መሳሪያ ለፀጥታ ስራ እንዲገለገልበት በሚመለከተው የመንግስት አካል ከተሰጠው በኋላ የተረከበውን የጦር መሳሪያ እንዲመልስ ሲጠየቅ ካልመለሰ ዓቃቢህግ በዚሁ ግለሰብ ላይ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 ተጠቅሶ ክስ የሚመሰረትበት

---

[25] *ተክሉ ገበየሁ እሸቴ እና የአብክመ ሰ/ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ ዓቃቢ ህግ* (2015)፣ በአብክመ የሰ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት 0249317፣ ፡፡ በተመሳሳይ በወ/መ/ቁ 0249030 በከሳሽ የአብክመ ሰ/ሸዋ ዞን ፍትህ መምሪያ ዓቃቢ ህግ እና በተከሳሽ አቶ ማሙዬ መንግስቴ መካከል በነበረዉ የወንጀል ክርክር ተከሳሽ ለፀጥታ ሥራ ከደብረብረሃን ከተማ ሚሊሻ ጽ/ቤት የተሰጠዉን አንድ ኤስ ኬ ኤስ የጦር መሳሪያ ለመንግስት እንዲመልስ በተጠየቀ ጊዜ የጦር መሳሪያዉን ሊያቀርብ ባለመቻሉ በዓቃቢ ህግ በኩል የሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/2007 አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1 ተጠቅሶ ክስ የቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተከሳሽን በተከሰሰበት ከባድ የዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ጥፋተኛ ነዉ ሲል ፍርድ ሰጥቶ እናገኛለን፡፡

እና ፍ/ቤቶችም የዓቃቢ.ህግ ክስን ተቀብለዉ በዚሁ አግባብ ውሳኔ እየሰጡ እንደሆነ ከላይ በተጠቀሰዉ መዝገብ ተመልክተናል፡፡

የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባልሆኑ ሰዎች ላይ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 (1) ወይም (2) ተጠቅሶ ክስ በቀረበ ጊዜ የድንጋጌውን ተገቢነት በተመለከተ በግራቀኙ ተከራካሪ ወገኖች በኩል የሚቀርብ ክርክር ባለመኖሩ ፍርድ ቤቱም እንደ ዓቃቢ.ህግ ክስ አቀራረብ ዉሳኔዎችን እየሰጠ እንደሆነ በአብክመ ሰ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል ዳኘነት ለረጅም ጊዜ ያገለገሉት አቶ ወንዲፍራዉ ጋሻዉ ለዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ነግረዉታል፡፡[26] ይህን እንጅ የቀረበዉ የክስ ቻርጅ ዝርዝር ሁኔታ እና የተጠቀሰዉ የህግ ድንጋጌ ተከሳሹን የሚያሳስትና በዚህም የፍትህ ስርዓቱን የሚያጓድል ሆኖ በተገኘ ጊዜ ፍርድ ቤቶች በራሳቸዉ አነሳሽነት ወይም ከተከራካሪ ወገኖች በአንደኛዉ አመልካችነት ክሱ እንዲሻሻል ትዕዛዝ መስጠት ያለባቸዉ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ ፍርድ ቤቶች በተከራካሪ ወገኖች ክርክር አልቀረበም በሚል ምክንያት በክስ ቻርጁ ላይ የተጠቀሰዉን ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ፍርድና ዉሳኔ መስጠት የለባቸዉም፡፡

በሌላ በኩል የአብክመ ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ መስሪያ ቤት የሙስና ጉዳዮች ዳሬክቶሬት ለሰሜን ጎንደር ዞን ዓቃቢ ህግ መምሪያ በሰጠዉ መሪ ትዕዛዝ የቀበሌ አመራሮች እና ሚሊሻዎች ለፀጥታ ሥራ የታጠቁትን የጦር መሳሪያ ለመመለስ ፈቃደኛ ባልሆኑ ጊዜ የሙስና ወንጀሎች አዋጅም ሆነ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 703 ተጠቅሶ ክስ መቅረቡ ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሶ ይልቁንም ለጉዳዩ አግባብነት ያለዉ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 (2) (ሀ) ላይ የተመለከተዉ ከባድ የዕምነት ማጉደል ወንጀል እንደሆነ ገልጿል፡፡[27] ይህ መሪ ትዕዛዝ ከተሰጠ በኂላም ቢሆን ያለዉ አሰራር ወጥ እንዳልሆነ የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ ተመልክቷል፡፡

በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 2 (2) ለመንግስት ሰራተኛ ከተሰጠዉ ትርጉም አንፃር የቀበሌ አመራሮችም ሆኑ ሚሊሻዎች የመንግስት ሰራተኞች ናቸዉ ሊባሉ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ይልቁንም እነዚህ ግለሰቦች የግል ሥራቸዉን እያከናወኑ በዛዉ የአካባቢያቸዉን ሰላምና ፀጥታ እንዲያስከብሩ ንብረትነቱ የመንግስት የሆነ የጦር መሳሪያ የተረከቡ ናቸዉ፡፡ የጦር መሳሪያዉ ለግለሰቦቹ የተሰጠዉ አካባቢያቸዉን ሰላምና ፀጥታ እንዲያስከብሩ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ ይህ ንብረት ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት (ለፀጥታ ስራ) ግለሰቦቹ እጅ እንደገባ

[26] በአብክመ ሰ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ከሆኑት አቶ ወንዲፍራዉ ጋሻዉ ኮከብ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ (ደብረብርሃን፣መጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም)

[27] የአብክመ ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ መስሪያ ቤት የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳሬክቶሬት፣ ሙ/ወ/ጉ 64/2013፣ ቀን 07/08/2013 ዓ.ም

የሚያከራክር አይደለም፡፡ እዚህ ላይ አከራካሪዉ ነጥብ ያለዉ ግለሰቦቹ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ካለመሆናቸዉ ጋር የተያያዘ ነዉ፡፡

ከላይ የተሰጠዉ ምሳሌ ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 (1) አንፃር ታይቶ ቢሆን ኖሮ ወንጀሉ የተፈፀመዉ በመንግስት ንብረት ላይ በመሆኑ የድርጊቱ ፈፃሚዎች በከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል የሚጠየቁበት የህግ አግባብ ነበር፡፡ በአሁኑ ሰዓት ይህ ንዑስ አንቀጽ ሙሉ በሙሉ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ የተሻረ በመሆኑ በግለሰቦቹ ላይ ይህን አንቀጽ በመጥስ ክስ መመስረት የሚቻል አይሆንም፡፡

ከላይ እንደተመለከትነዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 በወንጀል ህጉ አንቀጽ 675 የተፈፀመዉን የእምነት ማጉደል ወንጀል የሚከብድበትን ሁኔታ የሚደነግግ ነዉ፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 /1/ እና /2/ መሰረታዊ ማቋቋሚያ ነጥቦች በወንጀል ህጉ አንቀጽ 675 ሥር የተመለከቱት የእምነት ማጉደል ወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች ስለመሆናቸዉ የሁለቱ ድንጋጌዎች ይዘትና አቀማመጥ ያስገነዝባል፡፡[28] የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676/1/ እና /2/ የአንቀጽ 675 ከባድ ሁኔታ መሆኑ ከታመነ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 /1 / መሻር የድርጊቱን ከባድ ሁኔታ ያስቀር ይሆናል እንጅ የድርጊቱ ፈፃሚዎች በአንቀጽ 675 መሰረት ተጠያቂ መሆናቸዉን የሚያስቀር አይሆንም፡፡ ይህ አተረጓጎም በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ንብረት ላይ የእምነት ማጉደል ወንጀል የፈፀሙ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ያልሆኑ ሰዎች በአንቀጽ 675 መሰረት ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ የሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሰናል፡፡በሌላ በኩል እነዚህ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ያልሆኑ ግለሰቦች በመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ንብረት ላይ የፈፀሙት ድርጊት በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 ስር የማይሸፈን ቢሆንም በወንጀል ህጉ አንቀጽ 676/2/ ስር የተመለከቱትን ማክበጃ ምክንያቶች የሚያሟላ የሆነ እንደሆነ የወንጀል ህግ አንቀጽ 676/2/ ድንጋጌዎች ያልተሸሩ በመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ስር ባለዉ አግባብ በከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 5.2. የዕምነት ማጉደል ወንጀል እና በሥራ ተግባር ላይ ከሚፈፀም የመዉሰድና የመሰወር ወንጀል አንፃር ሲታይ

---

[28] *የደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት ዓቃቢ ህግ እና ወ/ሮ ፀሐይ መጫሎ* (2007) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 92826፣ (2008)17 የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ 158

ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀልን የሚደነግገዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 ከባድ የዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀልን የሚያቋቁሙ አምስት መሰረታዊ የህግ ፍሬ ነገሮችን የያዘ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ከእነዚህ የህግ ፍሬ ነገር ማቋቋሚያ አንዱ በአደራ የተሰጠዉን ዋጋ ያለዉ ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ የሚለዉ ነዉ፡፡ይህ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የሆነዉ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኜት በማሰብ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት የሆነዉንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠዉን ዋጋ ያለዉን ነገር ወይም ጥሬ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ ፣ወይም ለሌላ ሰዉ ያደረገ ፣የወሰደ፣ያሰወሰደ፣የሰወረ፣ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ አገልግሎት ያዋለ ወይም ይህን የመሳሰለዉን ማናቸዉንም አድራጎት የፈፀመ እንደሆነ ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀልን እንደሚያቋቁም ይደነግጋል፡፡

በዚህ ድንጋጌ ላይ "ማንኛዉም የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት የሆነዉንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠዉን" የሚለዉ አገላለፅ ግልፅነት የጎደለዉ ነዉ፡፡ ይህ ድንጋጌ የበለጠ አደናጋሪ የሚሆነዉ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 15 (1) ለ ሥር ከተቀመጠዉ በስራ ተግባር የሚፈፀም የመዉሰድና የመሰወር ወንጀልን ከሚደነግገዉ አንቀጽ ጋር ተቀራራቢ ይዘት ያለዉ በመሆኑ ነዉ፡፡

ከባድ የዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀልን የሚደነግገዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/2007 አንቀጽ 31 (1) ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀልን እንደሚከተለዉ ይደነግጋል፡-

> *ማንኛዉም የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኜት በማሰብ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት የሆነዉንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠዉን ዋጋ ያለዉን ነገር ወይም ጥሬ ገነዘብ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ያደረገ…*[29] *(ሰረዝ የተጨመረ)*

በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 15 (1) (ለ) ሥር በስራ ተግባር ላይ የሚፈፀም የመዉሰድና የመሰወር ወንጀል ማለት ደግሞ የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ በማንኛዉም የስራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸዉን ወይም የሚጠብቃቸዉን፣ዕቃዎችን፣ሰነዶችን፣ባለዋጋ ነገሮችን፣ጥሬ ገንዘቦችን፣ተንቀሳቃሽ ወይም አላቂዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ ነዉ በማለት ትርጉም ሰጥቶታል፡፡

[29] የኢፌዴሪ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 881/2007፣ አንቀጽ 31 ንዑስ አንቀጽ 1

በሥራ ተግባር ላይ የሚፈፀም የመዉሰድና የመሰወር ወንጀል በወንጀል ህጉ አራተኛ መጽሐፍ በርዕስ ሶስት ስር በአንቀጽ 413 ላይ ተደንግጎ የነበረዉ ሲሆን ከባድ የዕምነት ማጉደል ወንጀል ግን በንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በሚደነግገዉ በወንጀል ህጉ ስድስተኛ መጽሐፍ አንቀጽ 676 ሥር የነበረ ነዉ፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 413 ከቀድሞዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 422 ጋር ተቀራራቢነት ያለዉ መሆኑ በወንጀል ህጉ ሃተታ ዘምክንያት ላይ ተገልፆ ይገኛል፡፡[30]

የቀድሞዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 422 በስራ ተግባር ላይ ስለሚፈፀም የመዉሰድና የመስረቅ ወንጀል የሚል አርዕስት ነበረዉ፡፡ በተሻሻለዉ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 13 ላይ እምነት ስለማጉደል፣የማይገባ ጥቅም ስለማግኘትና ያለአግባብ ስለማጥፍት በሚል ርዕስ ስር ከወንጀለኛ መቅጫ ህጉ አንቀጽ 422 እና ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 413 ጋር በይዘቱ ተቀራራቢ የሆነ ድንጋጌ እናገኛለን፡፡ ከተሻሻለዉ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ዉጭ ባሉት ሌሎቹ የወንጀል ህጎች ላይ የእምነት ማጉደል ወንጀል በስራ ተግባር ላይ ከሚፈፀም የመዉሰድና የመሰወር ድርጊት ተነጥሎ ራሱን በቻለ አንቀጽ ነዉ የተቀመጠዉ፡፡በተመሳሳይ የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ የወጣዉ አዋጅም በስራ ተግባር የሚፈፀም የመዉሰድና የመሰወር ወንጀልን በአንቀጽ 15 ስር ሲደነግግ ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀልን በአንቀጽ 31 ላይ ደንግጎ እናገኛለን፡፡

በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 15 (1) (ለ) እና አንቀጽ 31 መካከል በግልፅ የሚታዬዉ አንድ መሰረታዊ የሆነ ልዩነት ከባድ ዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል እንዲቋቋም የተወሰደዉ ንብረት ወይም ጥሬ ገንዘብ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት መሆን ሲገባዉ በስራ ተግባር የሚፈፀም የመዉሰድና የመሰወር ወንጀል ግን በግለሰቦች ንብረት ላይ ጭምር ሊፈፀም መቻሉ ነዉ፡፡በዚህም መሰረት የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ የሆነ ሰዉ በግለሰብ ንብረት ላይ የሚፈፅመዉ በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመዉሰድና የመሰወር ድርጊት በሙስና ወንጀልን የሚያቋቁም ሲሆን በግለሰብ ንብረቶች ላይ የሚፈፀም የዕምነት ማጉደል ወንጀል ግን በሙስና ወንጀሎች አዋጅ የሚሸፈን አይሆንም፡፡

### 5.3. የዕምነት ማጉደል ወንጀል ከአታላይነት ወንጀል የሚለይባቸዉ ህጋዊ ፍሬ ነገሮች

[30] *የኢፌዴሪ ወንጀል ህግ፣* አዋጅ ቁጥር 414/1996 ፣ ሃተታ ዘምክንያት

የማታለልም ሆነ የእምነት ማጉደል ወንጀሎች በኢፌዴሪ ወንጀል ህግ በመጽሃፍ ስድስት ውስጥ በንብረት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ።የአታላይነት ወንጀል በ 1949 ዓ.ም በወጣዉ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 656 'ሀ' እና 'ለ' ተብሎ በሁለት አንቀጽ (*Paragraph*) ላይ የነበረ ሲሆን በ 1996 ዓ.ም በወጣዉ የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 692 በአንድ አንቀጽ እንዲጠቃለል ተደርጓል። የአታላይነት ወንጀልን የሚያቋቁሙ ህጋዊ ፍሬ ነገሮችን በተመለከተ በቀድሞዉ የወንጀለኛ መቅጫ እና አሁን በስራ ላይ ባለዉ የወንጀል ህግ መካከል መሰረታዊ ልዩነት አይታይም። የአታላይነት ወንጀልን ከሚደነግገዉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 692 ምንባብ በግልፅ መረዳት እንደሚቻለዉ የአታላይነት ወንጀል ተፈፅሟል ማለት የሚቻለዉ ማንም ሰዉ የማይገባ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባዉን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላዉን ሰዉ የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላዉን ሰዉ አታልሎ የራሱን ወይም የሶስተኛ ወገንን የንብረት ጥቅም የሚጎዳ አድራጎት እንዲፈፀም ያደረገ እንደሆነ ነዉ።

በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 696 ላይ የአታላይነት ወንጀል ከባድ ሁኔታን የሚደነግጉ ንዑሳን አንቀጾች የተዘረዘሩ ሲሆን የሙስና ወንጀሎች አዋጅ 881/2007 ከወጣ በኋላ ግን ይህ የአታላይነት ወንጀል ከባድ ሁኔታን የሚደነግገዉ አንቀጽ ጉዳዩ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ እስከተሸፈነ ድረስ ተፈፃሚነት አይኖረዉም።[31]

ልክ እንደ ስርቆት (አንቀጽ 665) ፣ዉንብድና (አንቀጽ 670) ፣ እና እምነት ማጉደል (አንቀጽ 675) ወንጀሎች ሁሉ የአታላይነት ወንጀልም የሚፈፀመዉ የማይገባ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ እንደሆነ ድንጋጌዉ ይዘት ያስረዳል። ከዚህ በተጨማሪ በድንጋጌዉ መሰረት የአታላይነት ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት አራት መሰረታዊ የህግ ፍሬ ነገሮች በአንድ ላይ ተሟልተዉ መገኘት ይኖርባቸዋል። እነዚህም፡

1. አጥፊዉ ሆን ብሎ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለጽ የሚገባዉን ነገር በመደበቅ ወይም ሌላዉን ሰዉ የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ መግለጽ ይኖርበታል፣
2. ተበዳዩ መታለል ይኖርበታል ወይም በአጥፊዉ የተገለፀለትን አምኖ ሊቀበል ይገባል፣
3. በሀ ሰት የተገለፀለትን ነገር በማመን የፈጸመዉ ተግባር መኖር አለበት፣
4. የግል ተበዳዩ በመታለሉ ሳቢያ የደረሰበት የገንዘብ ጥቅም ሊኖር ይገባል።

[31] *የኢፌዴሪ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ፣* አዋጅ ቁጥር 881/2007፣ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 1 ን ይመልከቱ

የማታለል እና የእምነት ማጉደል ወንጀሎች በወንጀል ህጉ በአንድ መጽሃፍ ውስጥ በንብረት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች ውስጥ ተካተው እንደመገኘታቸዉ ለሁለቱም ድንጋጌዎች የጋራ የሆኑ ማቋቋሚያዎች መኖራቸዉ የሚጠበቅ ነዉ፡፡ ለምሳሌ ብንመለከት ሁለቱም ወንጀሎች የሚፈፀሙት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ ሲሆን የግል ተበዳዩም በንብረቱ ወይም በገንዘቡ ላይ የሚደርስበት ጉዳት ይኖራል፡፡ ሁለቱ ድንጋጌዎች የሚጋሯቸዉ ፍሬ ነገሮች እንዳሉ ሆኖ የእምነት ማጉደል ወንጀል ከማታለል የሚለይበት መሰረታዊ ነገር አለ፡፡

በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሳሽ(ተጠርጣሪ) ንብረቱን እንዲሰጠው ለተበዳዩ የሚናገረው፣አስመስሎ የሚያቀርበዉ ወይም የሚያደርገው ተግባር የለም፡፡በእምነት ማጉደል ወንጀል ንብረቱ ወደ ተከሳሹ እጅ እንዲገባ የሚያደርገዉ በዋናነት የግል ተበዳዩ ሲሆን ይህ ንብረቱ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት እንዲዉል በማሰብ ወይም በአደራ ነው፡፡በአንፃሩ በማታለል ጊዜ የድርጊቱ መነሻ በተከሳሽ (ተጠርጣሪ) በኩል የሚደረጉ ወይም የማይደረጉ አሳሳች የሆኑ ነገሮች ሲሆኑ በግል ተበዳይ ላይ የሚደርሰዉ የንብረት ጉዳትም ይህንኑ አሳሳች የሆነ ነገር ከማመን (ከመታለል) የተነሳ ነዉ፡፡

## 6. የእምነት ማጉደል ወንጀል ጉዳዮች የዳኝነት ሥልጣን

የኢፌዲሪ ህገ መንግስት ፀድቆ በስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ የፍርድ ቤቶችም አወቃቀር በህገ መንግስቱ የተመለከተዉን ፌደራላዊ የመንግስት አወቃቀር ስረዓት በተከተለ መንገድ የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ተብለዉ ተቋቁመዋል፡፡[32] ለረጅም ጊዜ በህግ ባለሙያዎች ዘንድ ትልቅ የመከራከሪያ ነጥብ ሆኖ የዘለቀዉን የክልል ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ምንጭ ከዚህ ጽሁፍ አዉድ ዉጭ በመሆኑ እና እዚህ ላይ ማንሳት ተገቢም ስላልሆነ አልፌዋለሁ፡፡

በሙስና ወንጀሎች አዋጁ አንቀጽ 31 መሰረት ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል የሙስና ወንጀልን የሚያቋቁም ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የተሻሻለዉ የፀረ መስና ልዩ የስረዓትና የማስረጃ ህግ (አዋጅ ቁጥር 434/1997 እንደተሻሻለ) አንቀጽ 7 /1/ ፣/2/ /እና 3 ላይ በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ በዚህ ረገድ የሚነሳ ክርክር አይኖርም፡፡ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል የዳኝነት ስልጣን አከራካሪ የሚሆነዉ ድርጊቱ በሙስና ወንጀሎች አዋጅ የማይሸፈን ሲሆን እና በክልሎች ተፈፅሞ ሲገኝ ነዉ፡፡

---

[32] የኢ.ፌ.ዴ. ሪ ህገ መንግስት፣አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2

በቀድሞዉ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 641 እና 642 ላይ ተደንግጎ የነበረዉ እምነት ማጉደልና ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል በወ/መ/ሥ/ሥ//ህጉ አንደኛ ሰንጠረዥ ላይ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን እንደሆነ ተቀምጦ ነበር ። የህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 17/1967 ሲወጣ በ1954 ዓ.ም የወጣዉን የ/ወ/መ/ሥ/ሥ//ህግ አንደኛ ሰንጠረዥ አሻሽሎታል።በዚህ ህግ ቀድሞ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ሥልጣን ስር የነበሩት እምነት ማጉደልና ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል አዉራጃ ፍርድ ቤት ስልጣን ተደርገዋል። አሁን ባለዉ ፌደራላዊ የመንግስት አወቃቀር አዉራጃ የሚባል አደረጃጀት የሌለ በመሆኑ ቀድሞ ለወረዳ እና ለአዉራጃ ፍርደ ቤት ተሰጥቶ የነበሩ የስረ ነገር ስልጣን ለወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥተዉ ሲሰራበት ቆይቷል።

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ የክልሉን ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሄር የዳኝነት ስልጣን በዝርዝር ሲደነግግ የወንጀል ጉዳዮችን በተመለከተ ግን በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግና በሌሎች አግባብነት ባላቸው የፌደራል ሕጎች መሠረት በክልል መንግሥታት ፍርድ ቤቶች የሥረ-ነገር ሥልጣን ሥር እንደሚወድቁ የተመለከቱ የወንጀል ጉዳዮች የመቀበል እና የመዳኘት የሥረ-ነገር ሥልጣን አላቸው ሲል ይደነግጋል።[33] በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ የሙስና ወንጀል ክሶችን የማዬት የስረ ነገር ሥልጣን የተሰጠዉ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ። ከባድ የዕምነት ማጉደል ወንጀል የሙስና ወንጀልን የሚያቋቁም በሆነ ጊዜ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የሚነሱ የመያዝ ፣የመበርበር፣የቀነ ቀጠሮ፣ በማረፊያ ቤት የማቆየት፣የዋስትና ፣የእግድ፣ እንዲሁም ከምርመራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዩች የሚታዩት ዋናዉን ክስ የማዬት ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት እንደሚሆን ከተሻሻለዉ የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስረዓት እና የማስረጃ ህግ አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 4 ምንባብ መረዳት ይቻላል።[34]

በአንፃሩ በሙስና ወንጀል ሥር የማይጠቃለሉ ከባድ የዕምነት ማጉደል ወንጀል ጉዳዮችን የማዬት ስልጣን የሚወሰነዉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህጉ እና በህግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 17/1967 መሰረት በተቀመጠዉ አግባብ የአዉራጃ ፍርድ ቤት ነዉ ።ነገር ግን አሁን ባለዉ የመንግስት አወቃቀር አዉራጃ የሚባል አደረጃጀት የሌለ በመሆኑ ቀድሞ ለወረዳ እና ለአዉራጃ ፍርደ

---

[33] *የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ* ፣ አዋጅ ቁጥር 281/2014፣አንቀጽ 17 እና 19

[34] የተሻሻለዉን የፀረ ሙስና ልዩ የስነ ስረዓት እና የማስረጃ ህግ አዋጅን ለማሻሻል የወጣዉ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 882/2015 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4 ። ወንጀሉን የማየት ስልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት እንዲታይ መደረጉ የተከሳሹን መብት የሚያጣብብ ወይም ማስረጃ እንዲጠፋ ምክንያት የሚሆን ወይም ተገቢ ላልሆነ ወጪ የሚድርግ መሆኑን አግባብ ያለዉ አካል ካመነበት እንደ ሁኔታዉ በአቅራቢያዉ በሚገኝ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲታይ ሊወሰን እንደሚችል ይደነግጋል።

ቤት ተሰጥቶ የነበሩ የወንጀል ጉዳዮች የስረ ነገር ስልጣን ለወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥተዉ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡

በቅርቡ በፍትህ ሚኒስቴር በተረቀቀዉ የወንጀል ህግ ስነ-ሥረዓት እና የማስረጃ ህግ (ረቂቅ) በወንጀል ህጉ አንቀጽ 675 ላይ የተመለከተዉ የእምነት ማጉደል ወንጀል በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ሲፈፀም ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን ለፌደራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠ ሲሆን ወንጀሉ በክልሎች በተፈፀመ ጊዜ ደግሞ የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ስልጣን እንደሚኖራቸዉ በረቂቁ አባሪ በሆነዉ ሰንጠረዥ ‘ሀ’ ላይ ተቀምጧል፡፡ ድርጊቱ በወንጀል ህጉ 676 ላይ የተመለከተዉ አይነት ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል በሆነ ጊዜ በፌደራልም ሆነ በክልሎች የዳኝነት ስልጣኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እንደሚሆን በዚሁ ሰንጠረዥ ላይ ተመልክቷል፡፡

## 7. ማጠቃለያ

የዕምነት ማጉደል ወንጀል መሰረታዊ ማቋቋሚያ ነጥቦች በኢ.ፌ.ዲ. ሪ ወንጀል ህግ አንቀጽ 675 ሥር የተመለከቱት ሲሆኑ በድንጋጌዉ መሰረት የዕምነት ማጉደል ወንጀል ተፈፅሟል ለማለት ሶስት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች በአንድ ላይ ተሟልተዉ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህም፡-1ኛ. ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ማሰብ፣ 2ኛ. ንብረቱ ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠ መሆን እና 3ኛ. ነገሩ ዋጋ ያለዉ ወይም ጥሬ ገንዘብ መሆን የሚሉት ናቸዉ፡፡

የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 ደግሞ የዕምነት ማጉደል ወንጀል ከባድ ሁኔታን የሚዘረዝር ነዉ፡፡የወንጀል ህጉ አንቀጽ 676 በከፊል በሙስና ወንጀሎች አዋጅ ከተሻረ በኂላ በአንድ በኩል በመደበኛዉ የወንጀል ህግ የሚታዩ ከባድ የዕምነት ማጉደል የወንጀል ድርጊቶች በሌላ በኩል የሙስና ወንጀል የሚያቋቁሙ ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፍሬነገሮች ተፈጥረዋል፡፡ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 676/1/ በመተካት በሙስና ወንጀሎች አዋጅ አንቀጽ 31 ላይ የተደነገገዉ ከባድ የዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል ከላይ ከተዘረዘሩት የዕምነት ማጉደል ወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች በተጨማሪ የድርጊቱ ፈፃሚ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ መሆንን የድንጋጌዉ ማቋቋሚያ የሚያደርግ በመሆኑ የመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ያልሆኑ ሰዎች በመንግስት ንብረት ላይ ለሚፈፅሙት የእምነት ማጉደል ወንጀል ክስ አቀራረብ ተገቢነት ያለዉን ህግ በመለዬት ረገድ በህግ ባለሙያዎች በኩል ልዩነቶች ይስተዋላሉ፡፡

በማለት የሚገልጽ ሲሆን ይህም በግርድፉ በሚተርጎምበት ጊዜ የኢኮኖሚ ወንጀሎች ማለት የሚታይ ግዙፋዊ ሀልዮት ባህሪ የሌላቸው ነገር ግን ከኢኮኖሚ ጥቅም ወይም ሙያዊ የስራ ባህሪያቸው ጋር በተያያዘ የመንግስት ህግጋትና ክልከላዎችን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እንደሆኑና እነርሱም በነጋዴዎችና ሰራተኞቻቸው የሚፈጸሙ እና ሁለተኛው ደግሞ ከአቅርቦት ጋር በተያያዘ በሚፈጸሙ ህገወጥ ድርጊቶች እንደሆኑ ነው[2] ይላል። ይህ ትርጉም ጥቅልና ሌሎችንም ጉዳዮች እንደሚያካትት መረዳት ቢቻልም በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ጭምር እንደያዘና እንደሚያካትታቸው ግን መረዳት ይቻላል።

በኢኮኖሚ ወንጀሎች ላይ የሚያጠናና የታተመ አንድ መጽሄትት እንዳስቀመጠው፡ "'economic crime is a somewhat chaotic conception, that is, on occasion tendencies in both policy and social science to arbitrarily lump together features that are unrelated and inessential, and to bring together diverse issues and phenomena that have little analytical overlaps in both social scientific and policy discourse"[3]

በሚል የኢኮኖሚ ወንጀሎች በባህሪያቸው ውስብስብና የህግ ጉዳይ ብቻ ሳይሆኑ የማህበራዊ ሳይንስና የፖለቲካ ጉዳዮችን የያዙ የተለያዩና የማይገናኙ ግን ደግሞ በመጠኑ ባንድ ላይ ሊታዩና ሊከሰቱ የሚችሉ ክስተቶች እንደሆኑ[4] ያስቀምጣል።

ከዚህ ትርጉምና ወንጀሎች ባህሪ በመነሳት የንግድና የሸማቾች ጥበቃ ሕግጋት፤ ተቋማዊ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው የቢዝነስ ስራዎች ማለትም እንደ ባንክ ስራና የመሳሰሉት፣ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር፤ የታክስና ገቢዎች ጉዳይና የመሳሰሉት በኢኮኖሚ ወንጀሎች ስር ሊታዩ እንደሚችሉና[5] እነዚህን መሰል ጉዳዮች ደግሞ በባህሪያቸው የመንግስትን የገቢ ምንጭ የሚመለከቱ፣ ሀገራዊ ፋይዳ ባላቸው የኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ የፖሊሲና ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚያመለክቱና አስከማስለወጥ ድረስ የሚደርሱ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

በሀገራችን በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የሚባሉት ቀጥተኛ ትርጉም በወንጀል ህጉ ባይሰጥም ከጠቅላላ ቃላትና ከህጉ አገባባዊ ፍች በመነሳት እንደሚከተለው ለመተርጎም ተሞክሯል።

---

[2] *ዝኒ ከማሁ* (ትርጉም በጸሐፊው)

[3] N. Lord and M. Levi, Economic crime, economic criminology, and serious crimes for economic gain: On the conceptual and disciplinary (dis)order of the object of study; Journal of Economic Criminology 1 (2023) 100014, pp 1,7; www.journals.elsevier.com/journal-of-economic-criminology, accessed on 28/12/2024

[4] *ዝኒ ከማሁ* (ትርጉም በጸሐፊው)

[5] *ዝኒ ከማሁ* ገጽ 1፣ 5-7

በመንግስት የኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የሚባሉትን የኢኮኖሚ ወንጀሎች በሚል የሚተረጎምበት ሁኔታ የሚስተዋል በመሆኑ ቃላቶቹ በመዝገበ ቃላት በሚታዩበት ጊዜ ብላክስ ሎው ዲክሽነሪ ሲተርጉመው "economic crime› is a nonphysical crime committed to obtain a financial gain or a professional advantage."[6] በሚል የገንዘብ ጥቅም ለማግኜትና እንደሙያ ስራቸው አድርገው በመያዝ ከሚሰሩት ስራ ጋር በማያያዝ የሚሰራ ወንጀል መሆኑን ይገልጻል፡፡ እንዲሁም ደግሞ በሌላው ትርጉም ክፍል ነገር ግን ተያያዥነት ባለው ጉዳይ ኮሜርሻል ወንጀልን "commercial crime› is a crime that affects commerce"[7] በሚል የቢዝነስ እንቅስቃሴውን የሚጎዳ ድርጊት ሁሉ የንግድ ወንጀል ነው በሚል ከላይ ከተሰጠው ትርጉም ጋር ተቀራራቢ በሚመስል ነገር ግን ከንግድ ጋር በመያዙ መጠነኛ ልዩነት ባለው ሁኔታ ይተረጉመዋል፡፡ ናይሎር የሚባል ጸሐፊ ደግሞ እነዚህ ወንጀሎች ተያያዥና አንዱ ለአንዱ ሊያገለግሉ እንደሚችሉ በመጠቆም "ambiguous but specific umbrella terms [which means commercial crimes are the subsets of economic or whitecollar crimes] often used to refer to commercial crime is "economic crime" and "white-collar crime," both used interchangeably to refer to the former."[8] በሚል በባህሪያቸው ተወራራሽና አንዱ ለአንዱ በተቀያያሪነት ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ያብራራል፡፡

እነዚህ የኢኮኖሚ ወንጀሎችም በባህሪያቸው በሁለት እንደሚከፈሉና ይህም አንደኛው ከመደበኛ ስራቸው ጋር በተያያዘ ግዙፋዊ እያታቸው በጉልህ የማይታይ ነገር ግን በነጋዴዎችና በግልሰቦች የሚፈጸም ወንጀል እንደሆነ እና ሌላኛው ደግሞ ከመንግስት የህግ ክልክላዎችና የስራ ባህሪውና አሰራር ስነ ስርዓቶች በመውጣት የሚፈጸሙ ወንጀሎች እንደሆነ ሲያብራራ፤ ሌላኛው ደግሞ የኢኮኖሚ ወንጀሎች በባህሪያቸው በ 2 እንደሚከፈሉና በአፈጻጸም የተለያዩ አረዳድ እንዳላቸው እንዲሁም ደግሞ በከፊል አንድነት እንዳላቸው በዚህም አግባብ ከመደበኛ ስራቸው ጋር በሚያገኙት አጋጣሚ የሚሰራ መንግስትንና ሀገርን የሚጎዳ በቢዝነስ ዙሪያ የወጡ ደንብና መመሪያዎችን በመጣስ የሚፈጸም ወንጀል እንደሆነና ይህም እንደታክስ ስወራ የመሳሰሉት እንደሆኑ፣ ሌላኛው ደግሞ ሕገወጥ ነገሮችን በሕገወጥ መንገድ ማቅረብን የሚመለከቱ ወንጀሎችን እንደሆነ[9] ያመላክታል፡፡

ወደ ሀገራችን የህግ ማዕቀፍ ስንመጣ የኢኮኖሚ ወንጀል በሚል የተሰጠ ቀጥተኛ ትርጉም የለም፤ የኢኮኖሚ ወንጀል ናቸው በሚል ግን የተዘረዘሩ አሉ፡፡ ጥናቱ የጥሬ ገንዘብ

---

[6] Michele Riccardi and Michael Levi, (n.1)135.
[7] Black's Law Dictionary 425 (9th ed. 2004).
[8] R. Tom Naylor, Towards a General Theory of Profit-Driven Crimes, 43 BRIT. J. CRIMINOLOGY 82 (2003).
[9] Brayan A. Garner, Blacks Law dictionary, USA, Dallas Texsas, 9th edition, 2009, page 427 (ትርጉም በጸሐፊው)

እንቅስቃሴ ገደብ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ወንጀሎችን ምንነት በኢትዮጵያ ማስገንዘብ ጭምር በመሆኑ በአሰራር ደረጃ ምን ምን ጉዳዮች የኢኮኖሚ ወንጀል ተብለው ይታወቀሉ የሚሉትም ተዳሰዋል፡፡ እንዲሁም የወንጀል ህግ እንደሀገር የሚተገበር ቢሆንም የጥናቱ ወሰን አማራ ክልል በመሆኑና መዘግብትም የተዳሰሱትና ችግሮች የተስተዋሉት በሀገሪቱ ህጎችና ደንብና መመሪያ ሲሆን ከክልሉ መዛግብትና ለአሰራርና ለዳይሬክቶች ምደባው የሚያገለግለው ማንዋል[10]ና ሰርኩላሮችም በመጨመር ተዳሰዋል፡፡

በመሆኑም በፌድራል ፍትህ ሚንስትር ከተገቢው ስራ ክፍል ጋር እንደተዋቀረው[11] ሁሉ በክልሉም የኢኮኖሚ ወንጀሎች ዳይሬክቶሬት ስራ ክፍልን በማደረጀት ተግባርና ሀላፊነቱንም ንሐሴ 17/2014 ዓ/ም የአብክመ ፍትህ ቢሮ መስሪያ ቤት አደረጃጀት አሰራር፣ ተግባርና ሀላፊነት ለመወሰን የወጣው ማንዋል[12] በአንቀጽ 12.1.2 ላይ እንዳስቀመጠው ለቢሮው የወንጀል ማስፈጸም ዘርፍ በወል ከተሰጡት ተግባርና ሀላፊነቶች ጋር አያይዞ በዳይሬክቶሬቱ ልዩ ተግበርና ሀላፊነቱ የሚያከናውናቸው ጉዳዮች በሚል የዘረዘራቸው፡- ከንግድ አሰራር ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን፤ ከፍትህ ሚንስትር በውክልና ከተሰጡ የገቢዎችና ጉምሩክ ወንጀሎችን በሚመለከት፤ከሀሰተኛ የገንዘብ ዝውውር ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን፤ ደረቅ (ስንቅ የሌለው) ቼክን የሚመለከቱ ወንጀሎችን (የወ/ህ/ቁ 693)፤ የአራጣ ወንጀልን በሚመለከት (የወ/ህ/ቁ 712)፤ በታወቁ ገንዘቦች፤ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን፤ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ህጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን (አዋጅ ቁጥር 980/2008 እና ተያያዝ ጉዳዮች)፤ ከፀረ-ንግድ ውድድርና ሸማቾች መብት ጥበቃ ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን (አዋጅ ቁጥር 813/2006 እና ተያያዥ ጉዳዮች፤ በግብርና ታክስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

[10] ማንዋሉ በቢሮውና በተለመደው አሰራር በመዋቅሩ ስር ላሉና ለሚመለከታቸው ተገልጋዮች አስገዳጅ ሲሆን አላማው በቢሮው በስሩ ላሉት የስራ ክፍልና መዋቅሮች ስራን ማከፋፈልና መምራት የሚያስችል ሲሆን የአተገባር ልዩነት የተፈጠረባቸውን ጉዳዮችም በጥናትና ልዩ ልዩ አስተያዮቶችን ተከትሎ በቢሮ ሀላፊው፣ በም/ቢሮ ሀላፊው ወይም ደግሞ በዳይሬክተሩ የአሰራር መመሪያ ማውረድም የተለመደ አሰራርና ከመመሪያውና አሰራሩ ወጥቶ መስራትም ተጠያቂነትን የሚያስከትልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚችል አሰራር ነው፡፡ እንደማሳያ በጸረ-ሙስና አዋጁ 881/2007 አንቀጽ 9(1) ሌሎችም ሳይቀር < …በህግ፣ ከተለመደው አሰራር በመውጣት መስራት… ያስቀጣል> የሚሉ ድንጋጌዎችን ልብ ይሏል፡፡

[11] በፌደራል ፍትህ ሚንስትር  የኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳዮች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት ተግባር እና ኃላፊነት፤: http//www. moj.info@moj.gov.et; accessed on 12/25/2014

[12] *የአብክመ ፍትህ ቢሮ መስሪያ ቤት አደረጃጀት አሰራር፣ ተግባርና ሀላፊነት ለመወሰን የወጣው ማንዋል* ፤ አንቀጽ 12.1.2፤ ንሐሴ 17/2014 ዓ/ም በፍትህ ቢሮ ሀላፊ ተፈርሞ የወጣ የአሰራር ማንዋል)፤ ይህ ማንዋል አዲስ ወንጀልን የሚፈጥር ሳይሆን በዓ/ሕግ መካከል ስራን አመጣትኖ ለማከፋፈልና በጉዳዩ የተሻለ ግንዛቤና እውቀት ባላቸው ባለሙያዎች ለማሰራት በህግ ማስፈጸም ዘርፍ ስር ላሉት የወንጀል ዓ/ሕግ ስራ ክፍሎች የስራ ክፍፍልን የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ በህግ ከተደነገጉት የወንጀል ጉዳዮች መካከል የኢኮኖሚ ወንጀሎች ናቸው በሚል እንደመነሻ በስራ ክፍሎች መካከል የስራ ፍሰት ማሳለጫና ምደባ መስጫ ተደርጎ የሚወሰድና  ነው፡፡

በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (Crimes against economic interest of the state)[13] በሚል የሚገልጸው ሲሆን ከሕግ ማዕቀፉ በመነሳት ሲታይ የኢኮኖሚ ወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ወንጀል ድርጊቶች ማለት ከወ/ህ/ቁ አንቀጽ 343-345 የርዕሱ ጠቅላላ ድንጋጌዎችን፣ ከአንቀጽ 346-354 ደግሞ የርዕስ 4 ልዩ ድንጋጌዎችን የሚደነግግ ሲሆን፤ ህጋዊ የገንዘብ ኖቶችን ወይም የዋስትና ሰነዶችን መስራት፣ ወደሀሰት መለወጥ፣ ከሀገር ማስወጣት ወይም ወደሀገር ማስገባትና መሰል ጉዳዮችን በተመለከተ ከአንቀጽ 356 ጀምሮ እስከ አንቀጽ 362 አስቀጪ የሆኑ የወንጀል ድርጊቶች እና የሚያስቀጠቱን የቅጣት መጠን ይደነግጋል፡፡[14] ህጉ ለገንዘቦች ከፍተኛ ጥበቃ ለማድረግ በማሰብ በወንጀል ህጉ ከአንቀጽ 356-359 ለተመለከቱት ገንዘብ ነክ ድርጊት ግኝቶችን አስመልክቶ ማንኛውም ይዞ የተገኘው ሰው ለማዘዋወር ሀሳብ የህግ ግምት እንደሚወሰድበት ጭምር ደንግጓል፡፡[15] ይሄንን ህጋዊ ገንዘብ በቂ ምክንያት ሳይኖረው አልቀበልም ማለት ወይም ሀሰተኛ ገንዘብ በእጁ የገባ ሰው ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ካላሳወቀ በመቀጮ ወይም በማረፊያ ቤት እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል እንደሆነ ስለ ደንብ መተላለፍ በደነገገው የወንጀል ህግ አንቀጽ 778 እና 779 ላይ ይገኛል፡፡

## 2.2. የህጋዊ ጥሬ ገንዘብ ገደብ ወንጀል ፍች፣ ምንነትና የህግ ሽፋን ምልከታ

ህጋዊ የጥሬ ገንዘብ ገደብ ማለት በህግ ከተቀመጠው መጠን በላይ በግለሰብ ደረጃ ማንቀሳቀስን የሚከለክል ሲሆን ይዘቶችን ለመረዳ ቃላቶችን የህግ አወዳዊ ፍች እንደሚከተለው ታይቷል፡፡

‹ህጋዊ ገንዘብ› የሚለው ሲተረጎም "Legal tender" ሲሆን ትርጉሙም “…is a bill of credit in the form of paper, issued by a state and involving the faith of the state, designed to circulate as money in the ordinary uses of business.” በሚል ሳምጭው እንዲከፈል ህግ የሚያስገደድውና በወረቀት መልኩ የተዘጋጀ የ አንድ ሀገር ህጋዊ መገበያያ መሆኑን

[13] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፤* አዋጅ ቁ. 414/1996፣ ርዕስ 4፡፡

[14] የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፤አዋጅ ቁ. 414/1996፣ በአንቀጽ 343-345 ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣ አንቀጽ 346 በወርቅ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ ሀገር ገንዘብ በህገወጥ መንገድ መነገድ፤ በእንቀጽ 347 በከበሩ ማዕድናት ህገወጥ በሆነ መንገድ መነገድ፤ በእንቀጽ 348 በመንግስት ገንዘብ አስተማማኝነት ላይ የሚደረግ የተንኮል ድርጊት፤ በአንቀጽ 353 በአግር ኢኮኖሚና በመንግስት ሞኖፖል ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤ በአንቀጽ 354 የአንቀጽ 353ን ወንጀሎች የሚያከብዱ ሁኔታዎች፤ አንቀጽ 356 የሐሰት ገንዘብን መስራት፤ አንቀጽ 357 ወደሐሰት መለወጥ፤ አንቀጽ 358 ዋጋውን ዝቅ ማድረግ፤ አንቀጽ 359 ወደሀገር ማስገባት፣ ከሀገር ማስወጣት፣ መያዝ፣ ማስቀመጥ፣ና ማቅረብ፤ አንቀጽ 361 ማዘዋወር፤ አንቀጽ 369 የማታለል ሀሳብ ሳይኖረው አስመስሎ መስራት፤ አንቀጽ 370 አንቀጽ 370 በገንዘብ፣ በግዴታ ሰነድ ወይም በዋስትና ሰነድ ወይም በታወቁ ምልክቶች፣ ቴምብሮች ወይም ማህተሞች ላይ አደጋ ማድረስ፣ አንቀጽ 371 ሀሰተኛ ነገሮች ለመስራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችና መስሪያዎች በግልጽ የተዘረዘሩት ሲሆኑ ሌሎቹ የወልና ጠቅላላ ድንጋጌዎች ወይም ደግሞ ማቅለያና ማክበጃ ምክንያቶች ናቸው፡፡

[15] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፤* (ተ.ቁ.13) ፣ አንቀጽ 360

ያመላክታል፡፡[16] በመመሪየው ደግሞ ህጋዊ ገንዘብ (Legal tender) የሚለውን "…*Birr Notes issuied in circulation and commemorative coins minted by National Bank or coused to be prined or minted as the Legal tender which in circulating in the economy"*[17] በሚል ይተረጉመዋል፡፡ *‹ህጋዊ ገንዘብ›የሚለውን* አዋጁ ወደ እንግሊዝኛ ሲተርጉም ደግሞ (Legal tender)[18] በሚል የተረጎመው ሲሆን ቀጥተኛ ዝርዝር ትርጉም ግን በአዋጁ ትርጉም ክፍሉ አልተሰጠውም፡፡ ሆኖም ግን በአዋጁ ህጋዊ ገንዘብ በሚለው አንቀጽ ርዕሱ ስር ከተነሱት ፍሬ ጉዳዮች አንጻር ሲታዩ የገንዘብ መጠን፣ ቅርጽ፣ መደብ የመወሰን፤ የምንዛሬና ቅንስናሽ ሳንቲም ሁኔታ፣ያለገደብ ዝውውር፣ ለመክፈል በቂና ህጋዊ ስለመሆን አለመሆን እንዲሁም ላምጭው እንዲከፈል ህግ ማስገደዱን፤ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባና የሚወጣው ባንኩ ከወሰነው መጠን ውጭ ሊሆን እንደማይቻል፤[19] እንዳጠቃላይ የሚዘዋወር የገንዘብ (ብር) መጠንና የመቆጣጥር ሀላፊነት ተግባርና ሀላፊነት እንዳለበት ጭምር የሚያብራራና የሚደነግግና ጻሀፊውም እንደአስገዳጅ ለወሰድ በሚል የታመነበት ነው፡፡

ሌላው ከጥናቱ ጋር በተያያዘ ትርጉም የሚያሻው ጉዳይ "ጥሬ ገንዘብ (cash)" ሲሆን በአዋጁ እንግሊዘኛውን (ካሽ) (cash) [20] በሚል ሲያስቀምጥ የቃሉ ጥሬ ትርጉም ግን "cash - is Money or its equivalent; Currency or coins, negotiable checks, and balances in bank accounts."[21] የሚል ሲሆን በኢትዮጵያ የህግ ማዕቀፍ በመመሪያው ከተሰጠው ህጋዊ ገንዘብ (Legal tender) ጋር የሚመሳሰልና በተግባርና አጠቃቀም ደግሞ ልዩነት ያላቸው ቢሆንም የህጋዊ ገንዘብና የጥሬ ገንዘብ ልዩነት እና አንድነት የመደበላለቅና የአንዱን ትርጉም ለሌላው የመስጠት ሁኔታ በአዋጁና መመሪያው መካከል ያለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በመነሳት ጥሬ ግንዘብ (ካሽ፣"cash") ቀጥተኛ የሚከፈል ክፍያን የሚያመላክት ሲሆን ጥሬ ገንዘብ የሚለው በህጋዊ ገንዘብ ውሰጥ የሚካተት፤ በይዘቱም ጠቅላላ አስተዳደራዊ ስራውን ጭምር እንዲያከናውን የተሰጠን ተግባርና ሀላፊነት የሚያመላክት መሆኑን ነው፡፡ ህጋዊ ገንዘብ (Legal tender) ከሚከፈል ጥሬ ግንዘብ (cash) ትርጉም ጋር የመቀላቀልና የመመሪያው ጥሬ ገንዘብ ዝውውር ክልከላ ከአዋጁ ጥሬ ገንዘብ ማከማቸት ሀሳብ ጋር የመራራቅ ሁኔታ

---

[16] Brayan A. Garner, (n 9) 188 (ትርጉም በጸሐፊው)

[17] *የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ መመሪያ*፤ መመሪ ያ ቁጥር ሲኤምዲ (CMD) 01/2020 ወይም በፌ/ጠ/ህግ በጸደቀበት ስምና ቁጥሩ "No.288/2020)፤ አንቀጽ 2.4፡፡

[18] *የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ (እንደተሸሻለ) አዋጅ*፤ አዋጅ ቁጥር 591/2000፣ አንቀጽ 18፤ *የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ መመሪያ*፤ መመሪ ያ ቁጥር ሲኤምዲ (CMD) 01/2020 (በፌ/ጠ/ህግ በጸደቀበት ስምና ቁጥሩ "No.288/2020))፣ አንቀጽ 2(3) ፡፡

[19] *የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ (እንደተሸሻለ) አዋጅ*፤ (ተ.ቁ.18)፣ አንቀጽ 18(1፣2፣3፣4፣5 እና 6)

[20] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 2(9(ሀ))፡፡

[21] Brayan A. Garner (n 9) 245፤ *የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ መመሪያ*፤ መመሪ ያ ቁጥር ሲኤምዲ (CMD) 01/2020 ወይም በፌ/ጠ/ህግ በጸደቀበት ስምና ቁጥሩ "No.288/2020)፤፣ አንቀጽ 2(3)፡፡

ስለሚታይበት በትርጉም ከመመሪያው ይልቅ የአዋጁን ጥቅል ሀሳብ ጋር ተያይዞ ትርጉም በተሰጠው አግባብ መረዳት አስፈላጊና ህጋዊ ተቀባይት ያለውም ነው፡፡

እንዲሁም ደግሞ ጥሬ ገንዘብ ማከማቸት "cash hoarding" የሚለው ትርጉም የሚሻ ጉዳይ ሲሆን ይህንንም መመሪያው ሲተረጉም "...it means keeping cash ideal in large amount, outside financial institutions not being used for transactions;"[22] በሚል ማለትም በግርድፍ አማርኛ ትርጉሙ በከፍተኛ መጠን ገንዘብን ወይም የብር ኖትን ከግብይት ስርዓት ውጭ በማድረግ ማስቀመጥ ማስቀመጥ ነው ይላል፡፡

ሌላው የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ከህጋዊ ገንዘብ (የብር_ኖት) ጋር በተያያዘ ሲሆን የጥሬ ገንዘብ ዝውውር ገደብ ከወቅቱ አንጻር አስፈላጊ እንደሆነ የሚከራከሩ ሲኖሩ በሌላ በኩል ለወንጀል ተጋላጭነት ያለው መሆኑ በስፋት እየታየ ስለሆነ አስፈላጊነቱ እየቀነሰ ነው የሚሉም አሉ፡፡ ስለ ህጋዊ የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ገደብን አስመልክቶ አንድ ጸሐፊ ስለሁኔታው ሲገልጽ ጥሬ ገንዘብ ለኢኮኖሚ መሳለጥ አበርክቶው ከፍተኛ ሲሆን ሌሎች አማራጮችን እንደሞባይል ባንኪንግ፣ ቼክ፣ የባንክ መገበያያ ደረሰኝ ክፍያ እና ሌሎች መንገዶች ቢኖሩም ከአደጉ ሀገራት እስከ ታዳጊ ሀገራት የጥሬ ገንዘብ ክፍያን ልማዳዊ የመገበያያ መንገዳቸው አድርገውታል[23] በሚል ይደመድማል፡፡ በኢትዮጵያ ከመንግስት የኢኮኖሚ ጥቅሞች ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ወንጀሎችና በገንዘብ ላይ ህገወጥ ድርጊት ምን እንደሆነና ኢኮኖሚው ወይም ገንዘቦች በምን ሁኔታ መጠበቅ እንዳለባቸው የወንጀል ህጉና የብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጁ ላይ እንዲሁም በግለሰብ ደረጃ ምን ያክል ብር መያዝ እንደሚቻል የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ[24] (እንደተሻሻለ) (ከዚህ በኋላ አዋጅ እየተባለ የሚጠራው) መሰረት የወጣው የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ መመሪያ[25] እና፤ የዚሁ መመሪያ ማሻሻያ የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ ማሻሻያ መመሪያ[26] ይደነግጋል፡፡

በአዋጁ እንደተገለጸው ብሄራዊ ባንክ በተለየ ሁኔታ በፈቀደው አግባብ ካልሆነ በስተቀር በአገራችን ውስጥ የሚደረግ ማናቸውም የገንዘብ ስምምነቶች እና ውሎች በብር እንደተፈጸሙ ይቆጠራል፡፡ ነገር ግን አገራችን ተቀብላ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና በሌላ የአገራችን ህግ ከዚህ በተለየ ሁኔታ ግንኙነቶች በሌላ የገንዘብ ኖት እንዲደረጉ በግልጽ በተደነገገ

---

[22] *የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ ማሻሻያ መመሪያ፣ መመሪያ* ቁጥር CMD02/2021 ወይም በፌደራል ጠ/ህግ በጸደቀበት ስምና ቁጥሩ "Legal Tender Protection Directive No.786/2021፣ አንቀጽ 2(1፣2)

[23] Michele Riccardi and Michael Levi (n 1).

[24] *የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ (እንደተሻሻለ) አዋጅ*፤ (ቁ.18)፣ አንቀጽ 27፡፡

[25] *የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ መመሪያ*፤ (ተ.ቁ.22)፡፡

[26] *ዝኒ ከማሁ*፡፡

ጊዜ ገንዘብ ነክ ውሎች ወይም ግንኙነቶች በአለም አቀፍ ህጉ ወይም በግልፅ በደነገገው ህግ ወይም ብሄራዊ ባንክ ባዘዘው መሰረት በሚፈቀድ የገንዘብ ኖት ሊመዘገብ ይችላል፡፡[27] ህጋዊ ገንዘብን የመወሰን እና የማሳተም ስልጣን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት ብሄራዊ ባንክን የማስተዳደር፣ ገንዘብ ማተም፣ መበደር እና የውጭ ምንዛሬን መቆጣጠር የፌደራል መንግስት ስልጣን እና ሀላፊነት እንደሆነ[28] ተደንጓል፡፡

ለኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት፤ በዋጋ የተረጋጋ የውጭ ምንዛሬ ምጣኔና ጤናማ የፋይናንስ ስርዓት አስፈላጊ በመሆኑና ብሄራዊ ባንክ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ የተመጣጠነ እድገት ተስማሚ የሆኑ ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን ለመከወን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ (እንደተሸሻለ) የወጣ ሲሆን[29] የገንዘብ መደብን፣[30] ህጋዊ ገንዘብን[31] እና መሰል ሌሎች ጉዳዮችን የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ይዟል ፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 26 ላይ ‹ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች፣ ይህን አዋጅ ተከትሎ የወጡ ደንብና መመሪያዎች፣ በመተላለፍ በውጭ ምንዛሬ ግብይት የተሳተፈ፣ ያዘዋወረ፣ የውጭ ምንዛሬ የተቀበለ፣ በውጭ ምንዛሬ የከፈለ፣ የውጭ ምንዛሬ ሲያገኝ ወይም ሊያገኝ እንደሚችል ሲረዳ ያላሰወቀ ወይም የተወ፣ የውጭ ምንዛሬ የማገኘት እድሉን የተወ፣ የውጭ ምንዛሬ ከተፈቀደው መጠን በላይ ይዞ የተገኜ፣ የውጭ ምንዛሬ ኖሮት በወቅቱ ያላሳወቀ፤በብሄራዊ ባንክ ከተወሰነው ወይም ከተፈቀደው መጠን በላይ የኢትዮጵያ ገንዘብ ይዞ ከሀገር የወጣ ወይም ለመውጣት የሞከረ ወይም የገባ ወይም ለመግባት የሞከረ፤ የብሄራዊ ባንክ ሰኖዶቸን ያጠፋ የደበቀ የቀደደ፣ በአዋጁ የተከለከለውን መረጃ በህግ ከተፈቀደላቸው አካላት ውጭ መረጃውን የሰጠ፤ በዚህ አዋጅ መሰረት የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ወንጀል የሰራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ህግ መሰረት ይቀጣል› ይላል፡፡[32] ይህ አዋጅ ‹...በወንጀል ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ስልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም ሲሆን፤ በተደጋጋሚ ሲሆን፤ ያለአግባብ ሀብት ለማካበት ሲሆን ወንጀል የተሰራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር 50,000-100,000 እንደሚቀጣ...› ይደነግጋል፡፡[33] ይህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጹ አስከትሎም ‹ድርጊቱ የተፈጸመው *ከገንዘብ*፣ ከወርቅ፣ ከዋስትና ሰነድ፣ ከእቃ ወይም ከማናቸውም ሌላ ንብረት ጋር የተያያዘ ከሆነ ... ቅጣቱ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል ሀ መሰረት ሊወሰን ከሚችለው ቅጣት የሚያንስ ካልሆነ በስተቀር እስከ ንብረቱ ዋጋ 3

[27] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፤* (ቁ. 13)፣ አንቀጽ 374፡፡
[28] የኢፌድሪ ህገ-መንግስት፣ አዋጅ ቁጥር 01/1995፣ አንቀጽ 51(7)፡፡
[29] *የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ (እንደተሸሻለ) አዋጅ፤* (ቁ.18)፣ አንቀጽ 4፡፡
[30] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 17፡፡
[31] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 18፡፡
[32] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 26(1(*ሀ፣ለ፣ሐ፣መ፣*))፡፡
[33] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 26(2(*ሀ*))፡፡

እጥፍ ድረስ ከፍ ሊደረግ ይችላል› ይላል፡፡[34] እንዲሁም ደግሞ ድርጊቱ የተፈጸመው የህግ ሰውነት ባለው ድርጊት ከሆነ፤ በገቢና ወጭ ንግድና እቃ ጋር በተያያዘ ከሆነ፤ ዋጋቸውን ከፍና ዝቅ በማድረግ የብሄራዊ ባንክን መመሪያዎች በመጣስ የተፈጸመ ከሆነም ቅጣቱ የበለጠ እስከ 25 ዓመት ድረስ ከፍ እንደሚል ይደነግጋል፡፡[35]

ብሄራዊ ባንክ በ በአዋጁ በተሰጠው ደንብና መመሪያ የማውጣ ስልጣን መሰረት [36] ከብዙመመሪያዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን ‹‹የጥሬ ገንዘብ ጥበቃ መመሪያ CMD01/2020[37] የመመሪያ ማሻሻያው CMD02/2021[38] የወጣ ሲሆን፣ ይህ መመሪያ በአንቀጽ 3 ክልከላዎችን፤ በአንቀጽ 4 ደግም ክልከላዎችን የተላለፉ የሚቀጡበቱን የቅጣት ድንጋጌዎች አስቀምጧል፡፡

## 2.3. የኢኮኖሚ ወንጀሎች ጋር በተያያዘ የህገ-መንግስት፣ የወንጀል ስነስርዓት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች ምልከታ

የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ የሆነው ህገ-መንግስት ማንኛውም ዜጋ ወይም ዜጎች የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንዳላቸው፣ ንብረቶቻቼውን በማንኛውም ህጋዊ ሁኔታ ማስተላለፍ እንደሚችል፣ ንብረት ማለትም በህጋዊ መንገድ ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት እንደሆነ ይገላጻል፡፡[39] እንዲሁም ደግሞ የሀገሪቱንና የህዝቦቿን ኢኮኖሚ ሁኔታ ለማሻሻል እንደአንድ የኢኮኖሚ አላማ[40] የተቀመጠ ሲሆን በሌላ በኩል አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመፍጠር መነሻ እንዳለውም[41] በመግቢያው ያትታል፡፡ እንዲሁም ደግሞ የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ህግ ህግ እንዲያወጣባቸው የፌድራል መንግስቱ ስልጣን ስር የሆኑ የንግድ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ፣አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያስችል ፍ/ብሄር ህግም ሲያስፈልግ እንደሚያወጣ[42]፣ የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ የፋይናንስና ገንዘብ ፖሊሲሰዎችና ስትራቴጅዎችን እንደሚያጸድቅ፣ ገንዘብን፣ የብሄራዊ ባንክ አስተዳደርን፣ የውጭ ምንዛሬንና ልውውጥን በተመለከተ ዝርዝር ህግ እንደሚያወጣ[43]

---

[34] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 26(2(ለ))፡፡
[35] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 26(2(ሀ፣ለ፣ሐ)፣ 3፣ 4፣5) ፡፡
[36] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 27፡፡
[37] *የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ መመሪያ*፤ (ቁ.17) ፡፡
[38] *የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ ማሻሻያ መመሪያ፣* (ቁ.22)፣ አንቀጽ 3 እና 4፡፡
[39] የኢፌድሪ ህገመንግስት፣ (ቁ.28)፣ አንቀጽ 40(1፣2) ፡፡
[40] *ዝኒ ከማሁ፣* አንቀጽ 49(2) ፡፡
[41] *ዝኒ ከማሁ*፣ *መግቢያ*፡፡
[42] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 55(4፣5፣6)፡፡
[43] *ዝኒ ከማሁ፡* አንቀጽ 55(10)፡፡

ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም የኢኮኖሚ ጉዳዮች የፌድራል ጉዳዮች እንደሆኑና ህገመንግስታዊ መሰረት ብቻ ሳይሆን ሰፊ ሽፋንም እንዳላቸው መገንዘብ የቻላል፡፡

የወንጀል ስነ-ስርዓት ህግ የወንጀል ጉዳዮች የሚመሩበትን ስነ-ስርዓት የሚወስን ህግ እንደመሆኑ መጠን ዳሰሳ በሚደረግበት ጊዜ ከሌሎች ህጎች የተለየ ሽፋን የሰጠበት ቦታ በልዩ ሁኔታ ተከሳሹ በሌለበት የሚሰማበትን ሁኔታ ከሚወስነው ድንጋጌ በስተቀር በሌሎቹ ድንጋጌዎች ግን ልዩ ሽፋን አልተሰጠውም፡፡ ሆኖም ግን በዚህ በሌለበት ነገሩ እንዲታይ ልዩ ትኩረት በመስጠት በሌሎች ጉዳዮች ድርጊቱ ከ12 ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ጉዳዩ በሌለበት እንደማይሰማ ቢደነግግም[44] በዚህ የኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳይ ግን በልዩ ሁኔታና ትኩረት በመስጠት ድርጊቱ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ከአንቀጽ 354-365 የሚያስቀጡ ድንጋጌዎች ቅጣታቸው በጽኑ እስራት ወይም ከ5000 ብር በላይ የሚያስቀጡ ከሆነ የተከሳሹ ጉዳይ በሌለበት እንደሚታዩ ይደነግጋል፡፡[45] ይህ ድንጋጌ በተሻሻለው የወንጀል ህግ ርዕስ አራት ስር ከወንጀል ህግ አንቀጽ 343-354 የተደነገጉት ከመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች እና በገንዘብ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በግለሰብ እንዲያዝ ከተፈቀደው መጠን በላይ ጥሬ ገንዘብ መያዝ ክልከላንና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የታክስና ጉምሩክ እንዲሁም የበመንግስት ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ማሻሻያ ማስፈጸሚያ ህጎች ላይ የተጠቀሱ ወንጀሎች ጭምር መሆናቸውን መረዳት ይቻላል፡፡[46] በስነስርዓት ህጉ በግልጽ ለተጠቀሱት ወንጀሎች በሌሉበት የሚሰማበት እድል በነባሩ ህግ ከተቀመጠ ሲሻሻል ወይም በሌላ ማስፈጸሚያ አዋጅ የወንጀል ድንጋጌ ሲተካ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ወይ የሚለው አከራካሪጉዳይ ነው፡፡ በአንድ ወገን የወንጀልህግ መርሆዎችን[47] በመጠቀስ በአመሳስሎ (analogy) ትርጉም በተከሳሽ መብት ላይ መክበድ የለበትም የሚል ሲሆን በሌላ ወገን ደግሞ ከመደበኛው የወንጀል ስነ-ስርዓት ህጉ በልዩነት የወጣ እንደመሆኑና ከኢኮኖሚ ወንጀሎች ልዩ ባህሪ አንጻር በሌሉበት ሊሰማ ይገባል የሚል ሀሳብ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ከዚህ በመነሳት በተቃራኒው የሚከራከሩ ያሉ ቢሆንም፤ እንደጸሐፊው እምነት፤ ድርጊቱ የስነ-ስርዓት ህግ በመሆኑና ልዩ ትኩረት የተሰጠው፣ ከመደበኛው ስነ-ስርዓትም ከመጀመሪያው በመውጣት በልዩ ሁኔታ እንዲታዩ የተደነገገ መሆኑን የወንጀሎችን ተፈጥሮአዊ ባህሪ ግምት ውስጥ

---

[44] *የወንጀልኛ መቅጫ ህግ ስነስርዓት* ፣ በልዩ እትም የወጣ ቁጥር 1/1954፣ አንቀጽ 161(2(ሀ))፡፡

[45] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 161(2(ለ))፡፡

[46] የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፤ አዋጅ ቁ. 414/1996፣ በአንቀጽ 343-345 ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣ አንቀጽ 346 በወርቅ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ ሀገር ገንዘብ በህገወጥ መንገድ መነገድ፤ በእንቀጽ 347 በከበሩ ማዕድናት ህገወጥ በሆነ መንገድ መነገድ፤ በእንቀጽ 348 በመንግስት ገንዘብ አስተማማኝንት ላይ የሚደረግ የተንኮል ድርጊት፤ በአንቀጽ 353 በአግር ኢኮኖሚና በመንግስት ሞኖፖል ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤ በአንቀጽ 354 የአንቀጽ 353ን ወንጀሎች የሚያከብዱ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

[47] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ* (ቁ.13)፣ በአንቀጽ 2፡፡

ያስገባ በመሆኑ፣ በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞችና ሌሎችም ኢኮኖሚ ወንጀሎች ሁሉ እንደጉዳዩ ሁኔታ በጽኑ እስራት ወይም ከ5000ብር በላይ ሊያስቀጣ የሚችል ጉዳይ በገጠመ ጊዜ በሌለበት ሊሰማ የሚችልበት የመከራከሪያ ሀሳብ ማቅረብ ይቻላል፣ ፍርድቤትመ ሊቀበል ይገባል የሚል ምልከታ አለው።

ሌላኛው የተግዳሮት ምልከታ ከፍርድቤት የመዳኘት ስልጣን ጋር የተያያዘና በፌድራል ፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ድንጋጌዎች ሲሆን እነሱም፡ ጉዳዩ በፌድራል መንግስቱ የቀረጥና የግብር ገቢዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ከሆኑ፤ ጉዳዩ በፌድራል መንግስት የገንዘብና ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ከሆኑ፣ እና በታወቁ ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች ቴምብሮች ወይም መሳሪያዎች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ከሆኑ ስልጣኑ የፌድራል ፍርድቤቶች እንደሆነ ይደነግጋል።[48] እነዚህ የንዑስ አንቀጹ ድንጋጌዎች ለየትኛው እርከን ፍርድቤት የመዳኘት ስልጣን ተሰጠው የሚለው ደግሞ ለፌድራል ከፍተኛ ፍርድቤት የወንጀል መጀመሪያ ደረጃ የመዳኘት ስልጣን የተሰጠውን በግልጽ ሳይሆን በጠቅላላው በአዋጅ 1234/2013 በአንቀጽ 3 እና 4 የተጠቀሱትና በሌሎች ህጎች ለከፍተኛ ፍርድቤት የተሰጡ ጉዳዮች እና በሌሎች ህጎች ለፌድራል ፍርድቤቶች የተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች በሚል ይደነግጋል።[49] የዚህን ድንጋጌ "ሌሎች ህጎች" የሚለውን የህግ አውጭውን ሀሳብ ፍለጋ በምንሄድበት ጊዜ መደበኛው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ-ስርዓትንና ማሻሻያዎችን የምናገኝ ሲሆን ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው የስነ-ስርዓት ህጉ 1ኛ ሰንጠረዥ[50] እና ማሻሻያው ደንብ ቁጥር 17/1967[51] ናቸው። የወንጀል ስነ-ስርዓት ህጉ በ1ኛ ሰንጠረዥ የስልጣን ደረጃ የወሰነ ሲሆን እነዚህንም ሌሎች ጉዳዮችን ለወረዳና አውራጃ ሲሰጥ በልዩ ሁኔታ፡ አንቀጽ 366 ገንዘብ ስለመስራት፣ አንቀጽ 367 ወደሀሰት ገንዘብ ስለመለወጥ፣ አንቀጽ 368 የገንዘብ ዋጋ ስለመስራት፣ አንቀጽ 369 ገንዘቡን እንዲዘዋወር ስለማድረግ፣ አንቀጽ 370 የሀሰት ገንዘብን ወደሀገር ስለማስገባት ስለማስወጣት በአደራ አስቀማጭነት ስለመያዝና በስጦታ ስለማቅረብ፣ አንቀጽ 371 የመንግስትን ማህተም ወደሀሰተኛነት ስለመለወጥ፣ አንቀጽ 372 ሌሎችን የህዝብ አገልግሎት ያላቸው ማህተሞችን ስለመለወጥ ጉዳዮችን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰጥቷል።[52]

በዚህ የሰንጠረዡ ማሻሻያ ግን በጥቅሉ በሌሎች ህጎች ከ10 ዓመት በላይ የሚያስቀጡት ድንጋጌዎች ለከፍተኛ ፍርድቤት መሆናቸውን ቢገልጽም ቀጥተኛ የፍርድቤት ደረጃ ለውጥ

---

[48] *የፌደራል ፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ;* አዋጅ 1234/2013፣ አንቀጽ 4(11፤ 12 እና 13)

[49] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 12።

[50] *የወንጀልኛ መቅጫ ህግ ስነስርዓት* ፣ በልዩ እትም የወጣ ቁጥር 1/1954፣ 1ኛ ሰንጠረዥ።

[51] *የወንጀልኛ መቅጫ ህግ ስነስርዓት፣ አንደኛ ሰንጠረዥ ማሻሻያ፣* ደንብ ቁጥር 17/1967።

[52] *የወንጀልኛ መቅጫ ህግ ስነስርዓት* ፣ በልዩ እትም የወጣ ቁጥር 1/1954፣ 1ኛ ሰንጠረዥ።

ከተደረገባቸው ዝርዝሮች ውስጥ ግን በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች እና የህጋዊ ገንዘብ (የብር-ኖት) ላይ ግንኙነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ለውጥ አልተደረገበትም ነበር፡፡[53] ስለሆነም በወንጀል ህጉ የተጠቀሱት ከገንዘብ ጋር የተያያዙት በግልጽ በስነስርዓቱ ለከፍተኛ ፍርድቤት ከተሰጡት በስተቀር በፌ/መ/ደ/ፍርድቤት በክልል ውክልና ለክልል ከፍተኛ ፍርድቤት ሲሆን እንደሀሰተኛ ገንዘብ መስራትና ማዘዋወር የመሳሰሉትና በግልጽ ለከፍተኛ ፍርድቤት የተሰጡት በውክልና ለክልል ጠ/ፍርድቤት ናቸው፡፡ እንዲሁም ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26(2-5) የሚሸፈኑ ጉዳዮች ቅጣታቸው ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ በፌድራል ከፍተኛ ፍርድቤት፤ በክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ በውክልና የፌድራልን ከፍተኛ ፍርድቤት ስልጣንን ደርቦ ለያዘው የክልል ጠቅላይ ፍርድቤት የሚሆን ሲሆን ሌሎች መሰልና አግባብነት ያላቸው ህጎች ካሉም በዚሁ አግባብ የሚታዩ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡[54] እንዲሁም ደግሞ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የማይቀርቡት ሌሎች የኢኮኖሚ ወንጀሎች ግን መቅረብ ያለባቸው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትን በውክልና[55] ለያዘው ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድቤት ይሆናል ማት ነው፡፡

## 3. የኢኮኖሚ ወንጀል፤ በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች እና የህጋዊ ገንዘብ (የብር_ኖት) እንቅስቃሴ ገደብን በመተላለፍ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የህግ ማዕቀፍ አተገባበር በአማራ ክልል

### 3.1. የኢኮኖሚ ወንጀል፤ የመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞችን የሚወስን ህግ በመጣስ የሚፈጸሙ ድርጊቶች ወንጀልነት ዳሰሳ

የኢኮኖሚ ወንጀሎች የሚባሉት እንደፌድራልና አማራ ክልል የኢኮኖሚ ዳይሬክቶራት ስራ ክፍፍል ከላይ በርዕስ 2.1 ‹የኢኮኖሚ ወንጀሎች ፍች፣ ምንነትና የህግ ሽፋን› ላይ ተዘርዝረው የተጠቀሱትን እንደሆነ መረዳት ቢቻልም እነዚህ የተዘረዘሩት ግን ለፍትህ ሚንስትርና ፍትህ ቢሮው አሰራር እንጅ በወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች ግን እነዚህ ብቻ ናቸው ሊባል አይችልም፡፡ ምክንያቱም 1ኛ/ የድርጊት ፈጻሚዎች ሀሳብ የገንዘብ ጥቅም ለማግኘትና ይህም ድርጊታቸው ሀገራዊ ወይም ማህበራዊና ህዝባዊ ጉዳትን ሊያስከትል የሚችሉት ሁሉ እንደሀገር ሊያመጡ

---

[53] *ዝኒ ከማሁ፡* አበራ ጋሼ፣ 'በህግ ከተፈቀደው መጠን በላይ የኢትዮጵያን ገንዘብ መያዝ ወንጀል ህጉና በአብክመ ፍትህ ቢሮና መዋቅሮቹ ያለው አተገባበር' [2022]9 አብክመፍባማህምኢ የህግ መጽሄት152፣184-185፡፡

[54] *የኢፌድሪ ህገ መንግስት፣* አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ አንቀጽ 80(2)፤ አበራ ጋሼ፣ 'በህግ ከተፈቀደው መጠን በላይ የኢትዮጵያን ገንዘብ መያዝ ወንጀል ህጉና በአብክመ ፍትህ ቢሮና መዋቅሮቹ ያለው አተገባበር' [2022]9 አብክመፍባማህምኢ የህግ መጽሄት152፣184-185፡፡

[55] *የኢፌድሪ ህገ መንግስት፣* አዋጅ ቁጥር 1/1987፣ አንቀጽ 80(4)፡፡

የሚችሉት ጉዳት ከፍተኛነት አንጻር ሊመዘኑ እንደሚችሉ ሲታይ ሌሎች ድንጋጌዎችና አግባብነት ያላቸውን አዋጆች ሊጨምር እንደሚችል መረዳት ስለሚቻል፤ 2ኛ/ የፍትህ አካላት የስራ አደረጃጀት ዘርፍ ላይ በአግባቡ አለመቀረጹ እንጂ በዚህ ልክ ቢታይ ኖሮ ሌሎችንም ድንጋጌዎች ሊጨምር የሚችል የነበረ መሆኑ፣ እንደማሳያም በአደረጃጀቱ እንደበወንጀል የተገኙን ሀብት ማዘዋወር አዋጅ ቁጥር 780/2005 ባህሪው ከገንዘብ ጋር ሆኖ ለሌላ ዘርፍ ማለትምለመደበኛ ወንጀሎች ዳይሬክቶሬት መሰጠቱ፣ አራጣ የወ/ህቁ 712 እና ደረቅ ቼክ የወ/ህ/ቁ 693ን የኢኮኖሚ ወንጀል ነው ተብሎ ምዕራፍ 3 ጠቅላላ ርዕሱ ‹በንብረት መብቶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች›[56] የሚለው፤ አራጣ ወንጀል በክፍል ስር የሚገኝበት  3 የህሊና ወይም የሰውን ችግር መሰረት በማድረግ የሚፈጸሙ ወንጀሎች[57] የሚለው ስር ሆኖልሎች ግን እጅግ ተቀራራቢ ባህሪ ኖሯቸው ለሌላ ስራ ክፍል መሰጠታቸው፣ እና ርዕስ 2 ‹በንግድና ኢኮኖሚ ጉዳይ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች›[58] የሚሉ ታላቅ ርዕስ ስር የተቀመጡ ሁሉም የኢኮኖሚና ንግድ ጉዳዮች ሆነው ሳለ እነዚህን ድንጋጌዎች ለይቶ ማውጣት እነዚህ መብቶችን ለመጠበቅ የተቀመጡ ድንጋጌዎች ደግሞ እንደደረቅ ቼክና አራጣ ሁሉ ጉዳታቸው ጥቅል እንደሀገርም እንደማህበረሰብም ከፍተኛ በመሆኑ አንዱን ካንዱ ለይቶ ማየት ጥቅል የወንጀል ህጉን የኢኮኖሚ ወንጀል ድንጋጌዎች አላማና ግብ ሊያሳካ የሚችል ነው ለማለት የሚያስብል ስለማይሆን፤ የኢኮኖሚ ወንጀል በሚል ለኢኮኖሚ ወንጀል ዳይሬክቶሬት በሚል የተዘረዘሩለት ሙሉ አለመሆናቸውነና ለወደፊት የኢኮኖሚ ወንጀልና ተያያዥ የሆኑትን ሁሉ በድጋሚ ሊታዩና ሊደራጁ የሚገባ መሆኑን መረዳት የሚቻል ሲሆን እንዳጠቃላይ ግን የኢኮኖሚ ወንጀሎች ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሌሎችንም እንደሚያካትት ነው፡፡

ከወንጀል ህግ ባህሪና አተረጓጎም አንጻር በህግ ጸሀፊያን ዘንድም "Criminal law appears when the court is in doubt as to the application of the rule, or as to the occurrence or existence of a fact, the court should decide as such rule is not applicable, and in favour of the accused., respectivlly" በሚልና ይህም ወደ አማርኛ ባጭሩ ሲተረጎም የህግ ተርጓሚ አካላት ስለጉዳዩ መፈጠርም ሆነ ስለህጉ ተግባራዊነት የሚያጠራጥርና የሚያሻማ ነገር ሲገጥማቸው ለተከሻሽ በሚያዳላ መልኩ መተርጎም እንዳለባቸው[59] ያስቀምጣል፡፡ ከሀገራችንም አንጻር አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ለማለት የወንጀል ህግን መዳሰስ አስፈላጊ ሲሆን የሚመነጨውም ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ መሆን እንዳለበት የወንጀል

---

[56] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፡ አዋጅ ቁ.* 414/1996፣ *አንቀጽ* 691-705፡፡
[57] *ዝኒ ከማሁ*፣ *አንቀጽ* 712-715፡፡
[58] *ዝኒ ከማሁ*፣ *አንቀጽ* 716-724፡፡
[59] Simeneh Kiros (2017), Methods and Manners of Interpretation of Criminal Norm", 11(1), Mizan Law Review, 88-124, 110.

**ህጉ[60] ላይ የሚደነግግ ሲሆን፤ የፌድራል ሰበር ሰሚ ችሎቱም መሰል አስገዳጅ ውሳኔ[61] ሰጥቷል። እንዲሁም ደግሞ የወንጀል ህጉ ስለወንጀል ህግ መርሆዎች በተደነገገው[62] እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰ/ሰሚ ችሎትም በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም[63] አግባብ ህገወጥነቱ በግልጽ ድርጊትና ግድፈት እስካልተፈጸመና አስቀጭነቱም በግልጽ እስካልተወሰነ ድረስ እንደወንጀል ተቆጥሮ መቀጣት እንደሌለበት፤ ይመሳሰላል በሚል በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ እንደማይገባ፤ እና ህጉ አሻሚ ሆኖ በሚተረጎምበት ጊዜ ህጉ ሊደርስበት ያሰበውን ግብ ለማረጋገጥ እንዲቻል ህግ አውጭው ባቀደው ትርጉምና በህጉ መንፈስ መሰረት ሊተረጎም እንደሚገባ አስቀምጧል።**

**የወንጀል ህግ ባህሪ በህግም ሆነ በምሁራን አተያይ ከላይ ያለውን የሚመስል ሲሆን የኢኮኖሚ ወንጀልን በምናይበት ጊዜ ደግሞ የወንጀል 3ቱ ፍሬ ነገሮች ስለመሟላት አለመሟላታቸው እንዲሁም ደግሞ የድርጊት ፈጻሚዎቹ የሀሳብ ክፍል በምሁራን ዘንድ ሲያወዛግብ ይታያል። እንደአንዳድ ጸሐፊዎች ምልከታ** "violations of regulatory crimes [Among issues which makes conomic crime through regulation] should not be dealt with by the criminal law, as they do not possess "criminal essence" such as the requirement of mens rea element"[64]፤ **በሚል በንግድ ዘርፉ የሚፈጸሙ የኢኮኖሚ ወንጀሎች 3ቱን የወንጀል ፍሬ ነገሮች ስለማያሟሉና ድርጊቱም የሚፈጸመው ወንጀል ለመስራት ሳይሆን ለንግድና ለትርፍ በመሆኑ ወንጀል መሆን እንደሌለበት እና ወንጀል ከሆነም ነጻ ገበያን ሊጎዳ እንደሚችል ሀሳብ ያቀርባሉ።**

**በሌላኛው ወገን ያሉ ምልከታዎች እና በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ያሉ ዕሳቤና የሕግ-ድንጋጌ ምልክታዎች ደግሞ የኢኮኖሚ ጉዳይ ክልከላ ድርጊቶችን በመጣስ ወንጀል ማድረግ[65]፤ ተጠያቂ ካለማድረግ የበለጠ ጠቃሚ እንደሆነ ሲገልጽ** "Commercial crimes [i.e one taypes of economic crime] are non-violent crimes committed in business setting in pursuit of economic advantage for oneself or somebody, which affects free market exchange."[66] **ይላል። ይህ ጸሐፊም መሰል ድርጊቶችን ወንጀል ማድረግ የበለጠ የመንግስት ኢኮኖሚ ጥቅም ግጭቶችን ሊቀንስ እንደሚችል ሲያብራራው** "Severity of criminal sanctions designed to deter crimes of

---

[60] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፡* አዋጅ ቁ. 414/1996፣ አንቀጽ 23(2)።
[61] እነ ጀሚላ ሙሀመድ እና የፊ/መ/ደ/ዓ/ህግ፣ የፊ/ጠ/ፍ/ሰ/ሰ/ችሎት መ/ቁ 38161፣ የካቲተ 19/2001 ዓ/ም
[62] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፣* (ቁ.13)፣ አንቀጽ 2(2፣ 3፣ 4)።
[63] የገቢዎችና ጉምሩክ ዓ/ህግ እና እነ አቶ ከበደ ተሰራ፣ የፊ/ጠ/ፍ/ሰ/ሰ/ችሎት መ/ቁ 81178፣ መስከረም 21/2006 ዓ/ም
[64] Andrew Ashworth, Is the Criminal Law a Lost Cause? 116 L. Q. REV. 225 -229 (2000).
[65] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፡* አዋጅ ቁ. 414/1996፣ አንቀጽ 343-354።
[66] Jetu E. Chewaka, The Criminal sanction of Commercial Deceptions in Ethiopia, Haramaya Law Review [Vol. 3:1] 46(52)

commercial deceptions under Criminal Law potentially contribute to the reduction of economic crime"[67] በሚል በሀገር ላይና በኢኮኖሚ ላይ የሚፈፀሙ ድርጊቶችን ከፍ ያለ ቅጣት መጣል ለሀገር ጥቅም ጉልህ ሚና እንዳለውና የኢኮኖሚ ወንጀሎች ውስጥ አንዱ የሆነውን በንግድ ዘርፉ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ ማህበራዊ ጉዳቱን መቀነስ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ ከዚህ ትረጉምና አረዳድ በሚስማማ መልኩ በንግድና ተያያዥ ህጎች የህገወጥ ንግድ ወንጀሎችን[68] እንዲሁም የወንጀል ህጉ በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች አስመልክቶ አስቀጭ እንደሆኑ ይደነግጋል፡፡ ስለሆነም የጽሁፍ አቅራቢው እንደሚስማማበት በህጉ በተቀመጠው አግባብ ባላደጉ ሀገራት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው አዳጊ ስለሆነ ለግለሰቦች ምክንያታዊ ያልሆነ ጫና በመፍጠርና በአቋራጭ ለመክበር ስግብግ ነጋዴወች ኢኮኖሚውን እንዳይጎዱት በህግ መወሰንና ይህነን ተላለፈው ሲገኙም ከአስተዳደራዊና ፍ/ብሄራዊ ተጠያቂነት ባለፈ በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ፋይዳው የጎላ እንደሆነ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ሌላው በጥናቱ እንደጥያቄ በማንሳት ለመመለስ የተሞከረው የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ገደብ ጠቃሚ ነው ወይስ ጎጅ? ብሄራዊ ባንክ የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ መመሪያው የጥሬ ገንዘብ ክፍያ ገደብ ማድረግ የወንጀል ቅጣት ክፍሉ ከጅምሩ ህጋዊ ነው ወይስ አይደለም? በአዋጁ ያልተከለከሉ ነገሮችን መከልከሉ አግባብነት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ነው፡፡ ከላይ በንዑስ ርዕስ 2 ስር በከፊል ስለ ኢኮኖሚ ጉዳዮች ወንጀልነት አከራካራነት እንዳየነው የጥሬ ገንዘብ ክፍያ ገደብ ይኑረው አይኑረው በሚለው ላይም ክርክሮች አሉ፡፡ የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ገደብ መኖር ጠቃሚ እንደሆነ የሚሞግቱ የህግ ምሁራን ሲገልጹ፡

"Cash facilitates the laundering of illicit funds because it is anonymous and cannot normally be traced. It is a bearer negotiable instrument which gives no details either on the origin of the proceeds or on the beneficiary of the exchange; and which makes it harder for law enforcement to follow the audit trail. Thus; they argue that cash restriction regulatory frameworks must issued in mandatory ways."[69]

በሚል በወንጀል የተገኘ ገንዘብን ህጋዊ አድርጎ ማቅረብ ወንጀልን ለመቀነስና የኢኮኖሚ ወንጀል ፈጻሚዎችን ለመያዝ የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴን መገደብ የተሻለና የግዴታ ዋና አማራጭ እንደሆነ ይሞግታሉ፡፡

---

[67] *ዝኒ ከማሁ*፣ 76፡፡
[68] *የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ*፣ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 49፡፡
[69] Michele Riccardi and Michael Levi, (n 2)154፤

በሌላ በኩል ከጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ገደብ ጋር በተያያዘ ሌላ ጸሐፊም ስለሁኔታው ሲገልጽ፡

"Cash is successful in the legal economy.[70] … Despite the increasing use of alternative payment methods, such as credit cards, mobile payments or virtual currencies, banknotes still represent the preferred means of payment in certain sectors (e.g. food or retail), for certain age classes (very young or elderly people) and in certain areas—usually the poorest ones."[71]

በሚል ምንም እንኳን ሌሎች የገንዘብ እንቅስቃሴ አማራጮች ያሉ ቢሆንም የጥሬ ገንዘብ ከፍያ መኖሩ ባደጉ ሀገሮች ጭምር የሀገር ኢኮኖሚን በውጤታማነት ለመምራት በተለይም ለአነስተኛ ግዥዎች፣ ለፍጆታ እቃ መቸርቸሪያ ድርጅቶች እና ለከፊሉ ማህበረሰብ በተለይም ለወጣቶችና በእድሜ ለገፉ ሰዎች የተሻለ ተመራጭ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ እንዲሁም እንደዚህ ጽሁፍ ማብራሪያ ‹እንደውም በገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ ገደብ በተቀመጠ ቁጥር ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝንና ሀገራትን ከግብይትና የቅንጦት ግዥና ፍጆታዎች አንጻር ወደኋላ እንዳይወስድ ያሰጋል›[72] ይላል፡፡ ይህነን ምሁራኑ ሲገልጹም፡

“Cash restriction may modify the nature of illegal markets, increasing bartter, for example, exchanging drugs for firearms or other assets. And this will reshape criminal networks and partnerships. As a result of that, the reduction of cash may lead criminal groups, following new opportunities, to displace from traditional criminal activities to cybercrimes, including ‘old crimes in new bottles.”[73] ይላል፡፡

ይህም ማለት ሲተረጎም የገንዘብ እንቅስቃሴ መገደቡ ህወጥ የገንዘብ ዝውውርን መከላከል ይልቅ ሌላ አዲስና ውስብስብ ወንጀል በመፍጠር ሌላ ስጋት እንዳይሆንና ቀድሞ ወደነበረው የእቃ በእቃ ልውጥ እንዳይወሰደው ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባውም ጭምር ይጠቁማሉ፡፡[74] በሌላ አገላለጽ የህግ ምሁሩ ስሜነህ ኪሮስ “… must be made by the decision of the majority, the lawmaking process must be inclusive, and the law should be reasonable and should not be intrusive.”[75] ማለትም በግርድፉ ሲተረጎም ህግ በብዙሀኑ ውሳኔና ምክረ

70 ዝኒ ከማሁ፣ 153፡፡
71 ዝኒ ከማሁ፡፡
72 ዝኒ ከማሁ፣ (ትርጉም በጸሀፊው)፡፡
73 ዝኒ ከማሁ፣ 155፡፡
74 ዝኒ ከማሁ፣ (ትርጉም በጸሀፊው)፡፡
75 Simeneh Kiros Assefa , Ethiopia’s Criminal Law Evolution from the Perspectives of Major Legal Theories … , MIZAN LAW REVIEW, Vol. 16, No.2[241] December 2022, pp 270

ሀሳብ መውጣት እንዳለበት፣ የማውጣት ሂደቱም ሁሉን አካታች ሊሆን እንደሚገባ የሚወጣው ህግም ምክንያታዊ አሳምኝና የብዙሀኑ ቅቡልነት ሊኖረው እንደሚገባ[76] የሚገልጽ ነው፡፡

ስለሆነም እንደአጥኚው እምነት ወደፊት በርዕስ 3.2 ላይ እንደምንመለከተው ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ገደቡ መኖሩን ቢያምንበትም ከምንም ተነስቶ በ2012 ዓ/ም 1.5 ሚሊዮን ብር ከዚያም አመት ባልሞላጊዜ ውስጥ በ2013 ዓ/ም ለግለሰብ አንድ መቶ ሺ ለህጋዊ ድርጅት ሁለት መቶ ሺ ብር[77] በሚል ገደብ ማስቀመጡ የማህበረሰቡን ንቃተ ህሊናና የትምህርት ደረጃ፣ የባህላዊ ግብይት ልምድ፣ የኤሌክትሮኒክስ አማራጭ ክፍያ እውቀትን፣ የባንክና ሌሎች ፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነትን የማካለ መጠን ነው የሚል እምነት የለውም፡፡

ሌላው ጥያቄ ስለ መመሪያ ማውጣትና የህግ አግባብነት እንዲሁም አሁን ባለው አሰራር የጥሬ ገንዘብ ጥበቃ መመሪያ ሲሆን የተደነገገው የወንጀል ቅጣት በአንድ ወገን እና የመመሪያውን ክልከላ መነሻ በማድረግ በአዋጁ[78] መመሪያን በመጣስ ከተፈጸመ እንደሚስቀጣ ስለተቀመጠበት አግባብነት ነው፡፡ የህግ ምሁራን ሰለህግ አወጣጥና ስለመመሪያዎች የወንጀል ቅጣት አግባብነት ሲገልጹ

"The criminal law is manifestation of the "legal-social control"; it has to be adopted by the elected body representing the public in order to reflect the "social consensus". The executive is not an elected body and cannot represent the social realities of the union; and thus, the administrative agencies power is limited to making administrative offences which are punishable by adminstrative fine."[79]

በሚልና ይህም ሲተረጎም የወንጀል ህግ መገለጫው የማህበረሰብና መንግስት ህግ ውል እንደመሆኑ ሊጸድቅ ሚገባው በማህበረሰቡ በተመረጡ የህግ አውጭ አካላት መሆን እንዳለበት፤ አስጻሚ አካላት ደግሞ የመንግስት ተመራጭ እንጅ የህዝብ ተመራጮች ባለመሆናቸው የማህበረሰቡ ቀጥታኛና እውነተኛ ተመራጮች አለመሆናቸውንና በዚህም ምክንያት የአስፈጻሚ አካላት የሚወጡ መመሪያዎች ከአስተዳደራዊ ቅጣት በዘለለ የወንጀል ቅጣትን ሊወስኑ እንደማይገባ ይገልጻል፡፡[80] እንዲሁም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህግ

---

[76] *ዝኒ ከማሁ* (ትርጉም በጸሀፊው)፡፡

[77] *የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ ማሻሻያ መመሪያ*፣ *መመሪያ* ቁጥር CMD02/2021 ወይም በፌደራል ጠ/ህግ በጸደቀበት ስምና ቁጥሩ "Legal Tender Protection Directive No.786/2021፣ አንቀጽ 2(1)፣ 3.7፡፡

[78] *የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ (እንደተሻሻለ) አዋጅ*፤ አዋጅ ቁጥር 591/2000፣ አንቀጽ 27

[79] Simeneh Kiros & Chernet Wordofa (2017). "Over-criminalization': A Review of Special Penal Legislation and Administrative Penal Provisions in Ethiopia", XXIX(1) Journal of Ethiopian Law, 49-83. (82-83)

[80] *ዝኒ ከማሁ* (ትርጉም በጸሐፊው)፡፡

አወጣጥ ስነ-ስርዓት አዋጅ እንደሚያመለክተው ህግ ማለት በአዋጅ በተደነገገው ስነ-ስርዓት መሰረት በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ጸድቆ በፕሬዝዳንቱ ፊርማ አማካኝነት በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ በስራ ላይ የሚውል ህግ፤ ደንብና *መመሪያ* እደሆነ[81] ሲገልጽ ደንብና *መመሪያን* በነጋሪት ጋዜጣ መታተምን ሲደነግግ *መመሪያን* ግን መታተምንም ሆነ አለመታተምን እንዲሁም በአንድ በተወሰነ ቋንቋ መውጣትን በአስገዳጅነት አላስቀመጠም፡፡ ስለሆነም አስገዳጅነት የለውም ይላል፡፡

በተቃራኒው ደግሞ የፌድራል ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው የሕግ ትርጉም ‹በሕግ አውጪው የመንግስት አካል የሚወጡ ተከታይ ህግ (subsidiary legislations) በተለያዩ ቴክኒካዊና ማህበራዊ ምክንያቶች ዋናውን ህግ ለማስፈጸም የሚያስችል ዝርዝር ህግ ማውጣት ባልተቻለ ጊዜ በዋናው ህግ መሰረት ደንብና *መመሪያ* እንዲያወጡና እንዲያስፈጽሙ ውክልና መስጠት ሀገራችን ኢትዮጵያን ጨምሮ የተለመደ አሰራር[82] እንደሆነና በአስፈጻሚ አካላት የወጡ *መመሪያዎች* በነጋሪት ጋዜጣ ታትመው አለመውጣታቸው ወይም ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ አለመታተማቸው ህጋዊነታቸውን የሚያሳጣ ስላለመሆኑ እና አዋጁን ተከትለው የወጡ *መመሪያዎችን* መጣስ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡[83]

ይህና መሰል ህግና ውሳኔ ግን በህግ ምሁራንና በጸሀፊው ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡፡ አንደ ምክንያት የሚነሳው ደግሞ "Since Federal Cassation is not empowered to affect the content and scope of the law as proclaimed by the lawmaker;[84] its interpretative power is limited to constituting and giving effect to the law and not changing or deviating from the law,[85] as wellas its power is limited to making correct decisions."[86] በሚል የፌደራል ሰበር ውሳኔ የህጉን ይዘትና ወሰን የሚቀይር ሳይሆን ከህግ ወሰን ሳይወጡ ትርጉም መስጠትና ህጉን ውጤታማ እንዲሆን ትርጉም ከመስጠት የዘለለ ባለመሆኑ ከህጉ ወሰን የሚወጡ ከሆነ ከወንጀል ህግ አንጻር የወንጀል ህግ መርሆዎችን ስለሚጥስ አግባብነት እንደሌለው የሚገልጽ ሲሆን ይህን አረዳድ ጸሐፊውም ይስማማል፡፡

---

[81] *የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የህግ አወጣጥ ስነ-ስርዓትአዋጅ፣* አዋጅ ቁጥር 14/88፣ አንቀጽ 2(1)

[82] በአመልካች እነ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተጠሪ ዳንኤል መኮነን፣የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅጽ 10፣ መ/ቁ 43781፣ ሐምሌ 14/2002፡፡

[83] በአመልካች እነ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተጠሪ ዳንኤል መኮነን፣የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅጽ 10፣ መ/ቁ 43781፣ ሐምሌ 14/2002፡፡

[84] Simeheh Kiros (2017), Methods and Manners of Interpretation of Criminal Norm", 11(1), Mizan Law Review, 88-124. Pp 116

[85] *ዝኒ ከማሁ፣* ገጽ 114፡፡

[86] *ዝኒ ከማሁ፣* ገጽ 116 (ትርጉም በጸሀፊው)፡፡

በሌላ በኩል ይህ የሰበር ውሳኔም ሆነ የአዋጆች ውክልና ስልጣን በአዋጁ መሰረት የሚወጡ ህጎችን እንጅ በአዋጁ ያልተከለከለንና ክልከላውም ብሄራዊ ባንክ ባልተሰጠው ስልጣን ላይ የህጉን ጥቅል ውክልና በመውሰድ ከውክልና ስልጣኑ ውጭ በመውጣት ያወጣው መመሪያ ስለሆነ ተግባራዊነት የለውም የሚል መከራከሪያ እንዳለው ከአቶ ስንታየሁ ታከለ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ያስረዳል፡፡[87] ይህ የአቶ ስንታየሁ ሀሳብ ከህግ ምሁሩ ስሜነህ ኪሮስም ጋር የሚስማማ ሲሆን ይዘቱም "criminal law cannot be expanded beyond its scope and that every doubt favours the accused as the rule of lenity principle." በሚል ከሰጠውና የዚህ ትርጉምም የወንጀል ህግ ከዋናው የወንጀል ህግ መርሆና አላማ መውጣት እንደሌለበትና ከወጣም የተጠርጣሪን ነጻ ሆኖ መገመት መብት መርህ መሰረት በማድረግ አሻሚ በሚሆንበት ጊዜ ለተከሳሽ አመዛኝ በሆነ ሁኔታ መተርጎም እንደላበት ከገለጸው ሀሳብ ጋር ይስማማል፡፡[88]

ወደሀገራችን የህግና የአሰራር ማዕቀፍ በምንመጣበት ጊዜ መመሪያው በህግ የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ የተገደበ ሲሆን በህገ መንግስቱም ይሁን በአዋጁ መሰል ገደቦች አልተቀመጡም፡፡ እንዴውም አዋጁ ጥሬ ገንዘብ ያለገደብና ያለምንም ተቃውሞ በሀገሪቱ ገበያ ላይ እንዲቀሳቀስና ግብይት እንዲፈጸምበት ይደነግጋል፡፡[89]

ሆኖም ግን ከዚህ የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ብሄራዊ ባንክ በአዋጁ አንቀጽ 27 በተሰጠው መመሪያ የማውጣት ስልጣን መሰረት መመሪያ CMD 01/2020 እስከ የመመሪያ ማሻሻያው CMD 02/2021 የወጣ ሲሆን በመግቢያው ላይ አላማውንም ብሄራዊ ባንክ በሀገሪቱ ገንዘብ ላይ ህገወጥ የምስል የገጽታና የምልክት አርማዎችን በመጠበቅ የህዝብ አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ፤ ከአለምአቀፍና ከሀገራዊ የገንዘብ መጥፋትና መቀደድ መቃጠልና ሀሰተኛ ብር መራባት ጋር ተገቢውን ጥበቃና ቁጥጥር ለማድረግ፤ ህጋዊ የገንዘብ ግብይትንና ፍሰትን ለመጠበቅ እንደሆነና ጥሬ ገንዘቦች ከታለመላቸው አላማ ውጭ እንዳይውሉ ለመጠበቅ ስለመሆኑ ይገልጻል፡፡[90] ይህ መመሪያ ሌሎች ክልከላዎች እንደተጠበቁ ሆነው ለዚህ ጽሁፉ ማጠንጠኛ የሆነውና የተግዳሮቶች መነሻ የሆነው ጉዳይን ለማንሳት መሆኑን ተከትሎ የወጣውና ለወንጀል ድርጊቱ መቋቋም ህጋዊነት የወሰነው መመሪያ በመግቢያው ላይ አላማውን ህጋዊ የገንዘብ ግብይትንና ፍሰትን ማሳለጥ እንደሆነና ገንዘቦች ከታለመላቸው አላማ ውጭ እንዳይውሉ ለመጠበቅ ስለመሆኑ ከመግለጽ ባሻገር በመመሪያው

---

[87] ስንታየሁ ቸኮል፣ የአብክመ ፍትህ ቢሮ የኢኮኖሚ ወንጀል ዓ/ግ፤ በቀን 12/04/2016 ዓ/ም የተደረገ ቃለ-ምልልስ፡፡

[88] Simeheh Kiros (2017), Methods and Manners of Interpretation of Criminal Norm", 11(1), Mizan Law Review, 88-124. Pp 109 (ትርጉም በጸሀፊው)፡፡

[89] *የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ* (እንደተሸሻለ) አዋጅ 591/2000፣ አንቀጽ 18(3)፡፡

[90] *የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ መመሪያ*፤ (ተ.ቁ 17)፣ መግቢያ፡፡

ከፍተኛ በግል ጥሬ ገንዘብ ይዞ መንቀሳቀሱ እስከ 1.5 ሚሊዮን ብር እንደሆነ[91] ቢገልጽም ይህ መመሪያ አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተሻሻለ ሲሆን በዚሁ መመሪያ ማሻሻያ CMD 02/2021 በአንቀጽ 3.7 በእንግሊዝኛ ቅጅው በግለሰብ መያዝ የሚቻለውን ከፍተኛ መጠንን በማስመልከት በግለሰብ እስከ 100,000 (መቶ ሽ) ብር ለድርጅት እስከ 200,000 (ሁለት መቶ ሺ) ብቻ መያዝ እንደሚቻል የሚደነገግ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 4.5 ላይ ከተፈቀደው መጠን በላይ ይዞ የተገኜ በአዋጁ መሰረት እንደሚወረስበት ቢገልጽም በወንጀል ስለመቀጣት አለመቀጣቱ ግን ያለው ነገር የለም፡፡ ሆኖም ግን ከመመሪያው ሌሎች ድንጋጌዎችና አዋጁ መንፈስ አንጻር በአንቀጽ 26(1(መ)) መሰረት ወደ ወንጀል ህጉ የሚመራውን አማራጭ መጠቀሙንና የመመሪያው ጣምራ ምንባብ በግለሰብ መያዝ ከተፈቀደው መጠን በላይ ይዞ መገኘት ወንጀል እንደሚሆን የደነገገ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

## 3.2. ከብር ኖት (ጥሬ-ገንዘብ) ጋር የተያያዙ ወንጀሎች አተረጓጎም እና አተገባበር

ከኢኮኖሚ ወንጀል ጉዳይ ስራዎች ውስጥ አንዱ ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ማለትም በግለሰብ ደረጃ መያዝ ከሚፈቀደው መጠን በላይ ይዞ መገኘት ወንጀል፣ የጸና የንግድ ፈቃድ ሳይኖር የባንክ ስራ መስራት፤ ህገወጥ የገንዘብ ዝውውር እና ሌሎችም[92] መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ከዚህ ከተፈቀደው መጠን በላይ ገንዘብ ይዞ መገኘት ወንጀል ጋር በተያያዘ በቢሮው ብሎም በተዋረዱ ስር ባሉ ባለሙያዎች የህግ አተረጓጎም ልዩነት ያለ ስለመሆኑ በስራ ካጋጠሙን ልዩ ልዩ መዛግብቶች፤[93] አቶ አበራ ጋሼ ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በህግ መጽሄት ካሳተሙት ጥናታዊ ጽሑፍ[94] እና የፍትህ ቢሮ የወንጀል ጉዳይ ዘርፉ በእነ ምስጋነው አህመድ መዝግብ ጉዳይ ከተሰጠው መመሪያ፤[95] ላይ እንደተቀመጠው በግለሰብ ደረጃ እንዲያዝ ከተፈቀደው መጠን በላይ ጥሬ ገንዘብ ይዞ መገኜት ወንጀሎች ጋር በተያያዘ የወንጀል ድርጊት የፈጸሙ ሰዎች በመመሪያው CMD 01/2020 እና በማሻሻያው CMD 02/2021 መሰረት

---

[91] *የሀጋዊ ገንዘብ ጥበቃ ማሻሻያ መመሪያ፣* (ተ.ቁ. 22)፣ አንቀጽ 3.7፡፡

[92] የአብክመ ፍትህ ቢሮ የኢኮኖሚ ወንጀል ዳይሬክቶራት በቁጥርኢወጉዳ/22/2016 በቀን 28/01/2016 የቀረበ የ2016 በጀት አመት የ3 ወር የስራ ሪፖርት፡፡

[93] ሌሎች ብዙ ጉዳዮች ያሉ ቢሆንም እንደምሳሌ ለማሳያ ያህል በግዛቸው ታደሰ እና ዐ/ህግ መካከል በሰሜን ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ.0201853 ከሚፈቀደው መጠን በላይ 200000 ብር የዞ መገኘት ወንጀል ክስ ቀርቦለት በቀን 20/3/2015 በዋለው ችሎት በተከሰሰበት የመመሪያውንና የወንጀል ህጉን ተላልፏል በሚል ክስ ቢቀጣውም በይግባኝ የቀረበለት የጠ/ፍ/ቤት የወ/መ/ቁ .02-05659 ግን ባንክ በሌለበትና መንግስት ግዴታውን ባልተወጣበት ሁኔታ ወደባንክ ሊያስገባ በመሄድ ላይ ወደ ከተማ እየሄደ እያለ መያዙ የወንጀል ሀሳብ የለውም በሚል በነጻ የለቀቀው ሲሆን ይግባኝ ለሰበር ሰሚ ችሎት በይግባኝ ቀርቦም አያስቀርብም ተብሏል፡፡

[94] አበራ ጋሼ፣ 'በህግ ከተፈቀደው መጠን በላይ የኢትዮጵያን ገንዘብ መያዝ ወንጀል ህጉና በአብክመ ፍትህ ቢሮና መዋቅሮቹ ያለው አተገባበር' [2022]9 አብክመፍባማህምኢ የህግ መጽሄት152፣184-185፤

[95] በቁጥር ፍቢወ/219/16 በቀን 17/03/2016 ዓ/ም የፍትህ ቢሮው የህግ ማስፈጸም ዘርፍ በእነምስጋናው አህመድ(2 ሰዎች) ጉዳይ ላይ ለኢኮኖሚ ወንጀል ዳይሬክቶራት የሰጠው መመሪያ፡፡

የወንጀል ድርጊቱን ተላልፈው የተገኙ ሰዎች የሚጠየቁት መመሪያውን መጥቀስ እንዳለ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 26(2)(ለ) ነው ወይስ በመደበኛው የወንጀል ህግ አንቀጽ 353(1(ረ))[96] እና እንደሁኔታው በከባዱ ሁኔታ በሚያስጠይቀው በአንቀጽ 354 እና እንዲሁም በደንብ መተላለፉ? በሚለውን በተመለከተ በተግባር የሚታየው የአተረጓጎም እና አሰራር ወጥነት ችግር እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

1ኛ/ ከሚቀርበው የክስ ድንጋጌ አንጻር ሲሆን በቢሮው ዳይሬክቶሬትና በተዋረዱ ስር ባሉ ዓ/ህግ የሚቀርቡ ክሶች መመሪያውና የአዋጁ አንቀጽ 26(2(ለ)) ጠቅሶ ማቅረብ[97] የተለመደና ከፊሉ የሚስማማበት የህግ አተረጓጎም ሲሆን ውጤታማነቱም በፍርድቤት ውሳኔ ደንጋጌው ከአዋጁ 26(2(ለ)) ወደ 353(1(ረ)) የመሻሻልና በይግባኝም አለመስተካከል ሁኔታዎች ቢኖሩም ከጥፋተኝንት መመዘኛ አንጻር የተሻለ ነው፡፡[98] ከፊሉ ባለሙያና በተዋረዱ ባሉት ዞኖችና ወረዳዎች ግን እንደሁኔታው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 353(1(ረ)) እና መመሪያው፣ አዋጁና የወንጀል ህጉ አንቀጽ 343 እና 344፣[99] እንዲሁም በወረዳ መመሪያውና 785 ተጠቅሶ ክስ የሚቀርብበት ሁኔታ መኖሩ[100] በይግባኝ ከሚቀርቡት መዛግብቶች መረዳት ስለሚቻል ወጥነት ያለውን አሰራርና የህግ ትርጉም እንዲሰጥበት የጋራ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

2ኛ/ ክሶች ከመቅረባቸው አስቀድሞ ተከሳሾች የሚያቀርቡትን መከራከሪያ ከቃላቸውና ማስረጃዎች በመነሳት በምርመራ ማጥራትና የተከሳሾችን የሀሳብ ክፍልን ማግኜት እንዲሁም ይህነን በማስረጃ የመደገፍ ክፍተት የሚመነጭ ሲሆን ከተጠርጣሪ ወይም ከተከሳሽ ቃል

---

[96] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፤* አዋጅ ቁ. 414/1996፣ አንቀጽ 353(1(ረ)) በሀገር ኢኮኖሚና በመንግስት ሞኖፖል ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በሚል ርዕስ የተቀመጠ ሲሆን በንዑስ አንቀጽ 1 ስር ‹ማንም ሰው ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ወይምበደንብ መተላለፍ ከሚያስቀጡት ውጭ … ‹የመንግስት…የማናቸውም ተቋማት አሰራርና ቁጥጥርን አስመልክቶ የወጡ ድንጋጌዎችን አስቦ የጣሰ… በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል› የሚል ሲሆን መመሪያዎችን አይይዞ በመጥቀስ ክስ ማቅረብ የተለመደ ሲሆን ከዚህ አንጻር የገንዘብ ገደቡን መመሪያ በመጣስ ክስ ሲቀርብበትም ሆነ ፍ/ቤቶች በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 113 ከአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26(2(ለ)) የተከሰሰን ወደዚህ ድንጋጌ የመቀየር ልምዶች እንዳሉ በሌሎች የግርጌ ማስታወሻዎች የተጠቀሱ እንዳሉ ልብ ይሏል፡፡

[97] በከሳሽ ዓ/ህግ እና በተከሳሽ ኪሮስ ተገኜ በቁጥር ኢወጉዳ/110/2015 በቀን 21/09/2015 ዓ/ም በዓ/ህግ ወ/መ/ቁ 15/15 በዞን ፖ/ወ/መ/ቁ05/15፤ በጠ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 02-28869 በቀን 23/9/2015 ዓ/ም የተከፈተ ፋይል፤ በከሳሽ ዓ/ህግ እና በተከሳሽ እነወርቁ ጌትነት በቁጥር ኢወጉዳ/17/2016 በቀን 19/12/2015 ዓ/ም በዓ/ህግ ወ/መ/ቁ 18/15፤ በፖ/ወ/መ/ቁ33/15፤ በጠ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 02-29218 በቀን 29/12/2015 ዓ/ም የተከፈተ ፋይል፡፡

[98] በቁጥር ኢኮወዳ/97/2016 ሰኔ 24/2016 ዓ/ም የአብክመ ፍትህ ቢሮ ዒኮኖሚ ወንጀል ዳይሬክቶሬት ለቢሮው ያቀረበው አመታዊ ሪፖርት ላይ የማስቀጣት አቅም 75% መሆኑን ያሳያል፡፡

[99] በከሳሽ የሰሜን ጎንደር ዞን ፍትህ ዐ/ህግ እና በተከሳሽ ግዛቸው ታደሰ በቁጥር 02/2015 በቀን 27/11/2014 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ለዞኑ ከ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ በወ/መ/ቁ.0201853 የቀረበና ይዘቱም የኢፌዲሪ የወ/ህ/አንቀጽ 343/1/ እና 344(1-2) ፣ የተሻሻለው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.591/2000 አንቀጽ 26/1/መ/ በመተላለፍ የሚል ቅጣት የተላለፈበት በይግባኝ ግን የተሸረና በነጻ የተሰናበተ፡፡

[100] በከሳሽ ዓ/ህግና በተከሳሽ መላክ አስቻለው ደስታ፣ የባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ38949፤ በይግባኝ ባይ ዓ/ህግና በተጠሪ መላክ አስቻለው የባህርዳርና አካባቢዋ ከ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 0417610 በቀን 24/6/15 የተወሰነ፡፡

እንዲሁም መከላከያ ማስረጃዎች እንደሚታየው የዞ የመገኘት ድርጊቱን በከፊል አምነው ድርግቱን የፈጸምኩት ግን ‹‹ገንዘቡን ወደባንክ ላስገባ ስሄድ ነው እንጅ ወንጀል ለመፈጸም አይደለም፣[101] በጋራ ያመረትነውን በጋራ ሽጠን ልንከፋፈል ነው እንጅ ለሌላአላማ አይደለም፣[102] የከብት ነጋዴ በመሆኔ ብዛት ያለው ጥሬ ገንዘብ በመያዝ ለግብይት ልገዛ ስሄድ ነው፣[103] ለቤተ-ክርስቲያን የተሰበሰበውን ብር ወደ ተቋሙ ልናስገባ ነው እንጂ ለሌላ ህገወጥ አላማ አይደለም፤[104] ያመረትሁትን እቃ በጅምላ ወይም በችርቻሮ ሽጨ ባንክ ወዳለበት ወስጄ ላስገባ እንጅ ከግብይት አሰራር ውጭ ለመደበቅ/ለማስቀምጥ አይደለም፣[105] ከአርሶ አደር ሰብል ምርት በለቀማ የምገዛ የእህል ነጋዴ በመሆኔ ልገዛበት ይገፔ እየሄድሁ ወይም ሽጨ የያዝሄትና ለግብይት ልጠቀምበት እንጅ ለመደበቅ ወይም ከግብይት ስርዓት ውጭ ለማድርግ ይዥ አልተገኘሁም እና የመሳሰሉት››[106] የሚሉትን ተጠቅሰው በፖሊስ የምርመራ መዝገብ በተከሳሽነት ቃል እንዲሁም በፍርድቤት በመከላከያነት ቀርበዋል፡፡

ምንም እንኳን የሀሳብ ክፍል ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት የሚለው በወንጀል ህጉ[107] አግባብ የሚታይ ቢሆንም የዚህ መመሪያ ከተፈቀደው መጠን በላይ ገንዘብ ይዞ መገኜት ጉዳይ ወንጀልነት የሚከለክልና ማቋቋሚያም በመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ላይ በግልጽ  ለመጠየቅ የሃሳብ ክፍሉን አለመደንገጉ ወይም ደግሞ እንደሀሰተኛ ገንዘብ ይዞ መገኜት ወንጀል የማዘዋወር ሀሳብ ግምት እንደሚወሰድ[108] እና እንደሙስና ወንጀል ድንግጋጌዎች ከድርጊቱ በመነሳት

---

[101] በከሳሽ ዓ/ህግ እና በተከሳሽ እነምስጋናው አህመድ በቁጥር ኢ.ወጉዳ/6/2016 በቀን 6/04/2016 ዓ/ም በዓ/ህግ ወ/መ/ቁ 9/15 በአንዳቤት ወረዳ ፖ/ወ/መ/ቁ117/15 ለፖሊስ በተከሳሽነት ያስመዘገቡት ቃል፤

[102] በከሳሽ ዓ/ህግ እና በተከሳሽ እነወርቁ ጌትነት በቁጥር ኢ.ወጉዳ/17/2016 በቀን 19/12/2015 ዓ/ም በዓ/ህግ ወ/መ/ቁ 18/15 በፖሊስ በፖ/ወ/መ/ቁ 33/15 ያስመዘገቡት የተከሰሽነት ቃል፡፡

[103] በከሳሽ ባርዳር ከተማ ፖሊስ እና በተከሳሽ አሸናፊ ታከለ በቁጥር ፍ/ቢ/839/መ-17 በቀን 24/08/2015 ዓ/ም 540000 ይዘህ ተገኝተሀል በሚል ክስ ቀርቦበት ክሱ ለትክክለኛ ፍትህ ሲባል ከፍርድ በፊት በቢሮ ሀላፊው የተነሳለት፡፡

[104] ባህርዳር ፖሊስ መምሪያ ከተጠርጣሪ እነዘመነ ካሴ (5 ሰዎች) መካከል 545700 ብር ይዛችሁ ተገኝታችኋል በሚል በፖ/ወ/መ/ቁ 25/15 ለተጣራው ምርመራ በቀ;ህግ መ/ቁ 18/15 በቁጥር ኢ/ወ/ጉ/ዳ/87/2015 በቀን 13/07/2015 ዓ/ም ከሰጡት የተከሰሽነት ቃል ላይ የተወሰደና መዝገቡ ግን በአያስከስስም የተዘጋ፡፡

[105] በከሳሽ ዓ/ህግ እና በተከሳሽ ኪሮስ  በዞን ፖ/ወ/መ/ቁ 05/15፤ በጠ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 02-28869 በቀን 23/9/2015 ዓ/ም የተከፈተ ፋይል፤ በከሳሽ ዓ/ህግ እና በተከሳሽ እነወርቁ ጌትነት  በፖ/ወ/መ/ቁ 33/15፤ በጠ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 02-29218 በቀን 29/12/2015 ዓ/ም የተከፈተ ፋይል፤ በከሳሽ ዓ/ህግ እና በተከሳሽ እነምስጋናው አህመድ  በአንዳቤት ወረዳ ፖ/ወ/መ/ቁ117/15፤ በጠ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 02-29372 በቀን 8/4/2016 ዓ/ም የተከፈተ ፋይል ላይ ተከሳሾች በፖሊስ ምርመራ መዝገብ ላይ የሰጡት የተከሳሽነት ቃል በአጭሩ የተገለጸ፡፡

[106] ሌሎች መዛግብቶች ያሉ ቢሆንም እንደማሳያ በከሳሽ ዓ/ህግና በተከሳሽ እነ ጌታቸው ሞገስ (2 ሰዎች)፣ አብክመ ጠ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 912015፤ በከሳሽ ዓ/ህግና በተከሳሽ መላክ አስቻለው ደስታ፣ የባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ38949፤ ቤግባኝ ባይ ግዛቸው ታደሰ እና መ/ሰጭ ዐ/ህግ መካከል በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጎንደር ምድብ በጠ/ፍ/ቤት የወ/መ/ቁ .02-05659  ከሰጧቸው ውሳኔዎችና ካቀረቧቸው የመከላከያ መልሶች ባንክ በሌለበትና መንግስት ግዴታውን ባልተወጣበት ሁኔታ ወደባንክ ሊያስገባ በመሄድ ላይ ወደ ከተማ እየሄደ እያለ መያዙ የወንጀል ሀሳብ የለውም የሚል መከራከሪያ ቀርቧል፡፡

[107] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፤* (ተ.ቁ.13)፣ አንቀጽ 58፣ 59፡፡

[108] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 360፡፡

*የሀሳብ ክፍል የህግ ግምት አለመውሰዱ*[109] *በምርመራ ሂደት ማጥራቱን የሚያከብድና ለከሳሹ ወገን ክክስ በፊት ለመወሰን የሚያስቸግር እንዲሁም ለክርክር በር የሚከፍት*[110] *ነው። ድንጋጌው ግልጽ ነው ቢባልም ይዘው በመገኘታቸው ብቻ መክሰስና ማስቀጣቱ ግለሰቦች ያፈሩትን ንብረት እንዳይጠቀሙ መከልከል ውጤትን ያስከትላል፤ እንዲሁም ደግሞ ባለን የባንክ ተደራሽነትና ልማዳዊና ኋላቀር የግብይት ስርዓት አንጻር በአብዛኛው የገጠር ቀበሌዎች ባንክ የሌለ ከመሆኑ በላይ አልፎ አልፎ በወረዳ እንኳን ባንክ በሌለበት ሁኔታ፣ ባንክ ቢኖር እንኳን አንዳንዴም አርሶአደርና የገጠር ነጋዴው ማህበረሰባችን የብር ኖትን በከፍተኛ መጠን ይዞ በመሄድ ካልተገበያየ በስተቀር ግብይት ለመፈጸም የሚቸገር ከመሆኑ አንጻር፤ ያላችውን አነስተኛ ጥሪት በወንጀል መውረሱ የግብይት ስርዓቱን የሚጎዳው ስለመሆኑ አያጠያይቅም። እንዲሁም ደግሞ ከ80% አካባቢ ያልተማረ ማህበረሰብ ወይም አርሶ አደር በሆነበት የሀገራችን ክፍል ይህን መመሪያ ማውጣቱ ግብይትን በኤሌክትሮኒክስ ግብይት ከመፈጸም ይልቅ ወደ እቃ በቃ ግብይት* (Bartter system) *ሊወስደው የሚችልበት እድልም ሰፊ ነው።*[111] *ያልተማረው ማህበረሰብ በኤሌክትሮኒክ ግብይት አለማወቅ የተነሳ ለመጭበርበር የመዳረግ እድሉ ከፍተኛ መሆን፤ ብሩን ወደባንክ ለማስገባትና ለማውጣት ብሎም በተሳለጠ ለመገበያየት የባንኮችን መጨናነቅና የአርሶ አደር ግለሰቦችን ከገጠር ወደ ባንክ ያለበት ከተማ መመላለሻ ጊዜና ጉልበት ከማባከን አልፎ አሁን አሁን እየተተገበሩት ያሉ የባንክ አገልግሎት ክፍያና ታክስም ማንኛውም የወቅቱ ባንክ ተጠቃሚ የሚያረጋግጠው ሀቅ በመሆኑ በተለይ ባልተማረውና ለወቅቱ ቴክኖሎግ ቅርብ ላልሆነው ማህበረሰባችን የሚፈጥረው ችግር ቀላል አይደለም። በምርመራ ሂደት አረጋግጦ ለሌላ ወንጀል አላማ ካልሆነና ለመደበቅ አላማ አለመሆኑን አረጋግጦ የክስ አይቀርብም ውሳኔ እንዳይሰጥ ፖሊስ በምርመራ ማጥራት ሂደቱ ይዞ መገኘቱን በማስረጃ ከማረጋገጥ ባለፈ የተጠርጣሪን መከላከያ የሚያሰባስብበትና ማስረጃመ የሚሰበስብበት አሰራር ያልተለመደ ስለሆነ የህጉን ጽንሰ ሀሳብ ተረድቶ ተገቢውን ፍትህ ለማስጠት አዳጋች ያደርገዋል። ስለሆነም እነዚህ የተጠቀሱት ችግሮች ታይተው ከምርመራ፣ ክስና ክርክር እስከ ፍርድ አሰጣጥና የህግ ማሻሻል ጥያቄ ማቅረብ ድረስ አቅጣጫ ሊሰጥበት የሚገባ መሆኑን መረዳት የሚቻል ነው። ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ከላይ በርእስ* 3.1

---

[109] *የሙስና ወንጀሎች አዋጅ፤* አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀጽ 3።

[110] በከሳሽ ዓ/ህግ እና በተከሳሽ እነምስጋናው አህመድ በቁጥር ኢ.ወጉዳ/6/2016 በቀን 6/04/2016 ዓ/ም በዓ/ህግ ወ/መ/ቁ 9/15 በአንዳቤት ወረዳ ፖ/ወ/መ/ቁ117/15፤ በጠ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 02-29372 በቀን 8/4/2016 ዓ/ም የተከፈተ ፋይል፤ በከሳሽ ዓ/ህግና በተከሳሽ እነ ጌታቸው ሞገስ (2 ሰዎች)፣ አብክመ ጠ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 912015፣ በከሳሽ ዓ/ህግና በተከሳሽ እና አለ ጌትነት (03 ሰዎች) የሠ/ጎጃም ፍትህ መምሪያ በቁጥር 062985 በቀን 05/10/2015 ዓ/ም፤ በከሰሽ ክልል ዓ/ህግና በተከሳሽ ጋሹ ደስታ በከአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 02-27995 የቀረበ ክስ፤ ላይ ሁሉም ተከሳሽ (ተጠርጣሪዎች በሚባል መልኩ የሀሳብ ክፍላቸው በመጠቀስ ጥፋተኛ እንዳልሆኑ ክርክር ተነስቶባቸዋል።

[111] Michele Riccardi and Michael Levi, (n 1)155.

እንደተብራራው ጉደዩ የተሻለ ሌላ አማራጭ ካልተፈለገለት በስተቀር ውጤቱ ወደሌላ አዲስ የወንጀል ድርጊት የሚያመራና ግለሰቦችን ወደእቃ በእቃ ልውውጥ ሊያመራ የሚችልበት ሁኔታም ሊፈጠር እንደሚችል ያመላክታል፡፡

3ኛ/ በክልሉ ባሉት የፍርድቤት መዋቅሮችም ሆኑ በፍትህ ቢሮው መዋቅሮች የቀረቡ መዛግብቶችን በምናይበት ጊዜ ከህግ ባለሙያዎች የክርክርና ይግባኝ አተያይ አንጻር የሚመነጭ ሲሆን በቀረቡት መከራከሪያዎች መሰረትም ከፊሉ ተከሳሾች ጥፋተኛ ሲባሉ ከፊሎች ከተፈቀደው መጠን በላይ ገንዘብ ይዞ መገኜት ወንጀል የሀሳብ ክፍሉን አያሟላም እየተባሉ አያስከስስም በሚል በነጻ መለቀቃቸው[112]፤ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 141 መሰረት ወይምተከላክለዋል በሚል[113] በነጻ መለቀቃቸው፤ ጥፋተኝ ከተባሉም ሊጠየቁ የሚገባው መመሪያው ለሁሉም ድንጋጌዎች መጠቀሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 26(2(ለ)) ሳይሆን በአዋጁ 26(1(መ)) እና በወንጀል ህጉ 353(1(ረ)) ነው በሚል ተቀይሮ የሚቀጣበትና በይግባኝም ተመሳሳይ ልዩነቶች እየተከሰቱ ለማሳረም አለመቻሉ፤[114] በመሰል ጉዳይዎች ልዩነት ያለው ውሳኔ በፍትህ ቢሮውና በተዋረዱም ሆነ በፍርድ ቤቶች[115] እንዲሁም በህግ ባለሙያዎች አረዳድ ዘንድ መኖሩ ይስተዋላል፡፡

በፍትህ ቢሮው ባለሙያዎች የአረዳድ ልዩነት ያለ ለመሆኑ እንደማሳያ ለማሳየት ያክል በከሳሽዓ/ህግ እና በተከሳሽ አሸናፊ ታከለ አንተነህ በተጠረጠረበት በህግ ከተፈቀደዉ በላይ ገንዘብ ይዞ መገኘት ወንጀል በወ/መ/ስ/ስ/ህ ቁ 41 መሰረት መሪ ትዕዛዝ የተጠየቀ ሲሆን የጥያቄው ይዘቱም፡-1ኛ/ግማሹ ባለሙያ ተጠርጣሪዉ ለፍየል መግዣ ይዞ ሲሄድ የተያዘና ነጋዴ ስለሆነ ለንግድ ልዉዉጡ ያመች ዘንድ ገንዘቡን ይዞ መገኘቱ የወንጀል ህጉን አንቀጽ 23 አያሟላም የክስ አይቀርብም ዉሳኔ ይሰጥ የሚል፣ 2ኛ/ ግማሹ ባለሙያ ከመጠን በላይ ገንዘብ ይዞ መገኘት ወንጀል በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 መሠረት ጉዳዩ ለክልል ዐ/ህግ ስልጣን ነዉ የሚል፣ እና 3ኛ/ ሌላዉ ባለሙያ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26(1) (መ) መሠረት ወደ ደንብ መተላለፉ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 785

[112] ባህርዳር ፖሊስ መምሪያና ከተጠርጣሪ እነዘመነ ካሴ (ተራ ቁጥር 82)፡፡

[113] ከሳሽ ዓ/ህግ እና በተከሳሽ እንዳለው አድማሱ፤ የአብክመ ጠ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 29584፣ በቀን ሰኔ 25/2016 ዓ/ም በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 149(2) መሰረት ባካባቢው ባንክባለመኖሩ ወደባንክ ሊያስገባ እንጅ በህገወጥ ለማከማቼት አልያዘውም በሚል ተከላክሏል ተብሎ በነጻ የተለቀቀና ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ቀርቦ በክርክር ላይ ያለ፡፡

[114] በከሳሽ የሰሜን ጎንደር ዞን ፍትህ መምሪያ ዐ/ህግ እና በተከሳሽ ግዛቸው ታደሰ በቁጥር 02/2015 በቀን 27/11/2014 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ለዞኑ ከ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ በወ/መ/ቁ.0201853 የቀረበና ይዘቱም የኢፌዲሪ የወ/ህ/አንቀጽ 343/1/ እና 344(1-2) ፣ የተሻሻለው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ.591/2000 አንቀጽ 26/1/መ/ በመተላለፍ የሚል ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ተብሎ ይተቀጣ በይግባኝ ግን የተሸረና በነጻ የተሰናበተ፡፡

[115] አበራ ጋሼ (ተ.ቁ 94)164-165፡፡

ስለሚመራ ወደ ወረዳ ይላክ የሚል በመሆኑ እና ባለሙያዎች በ3 ተከፍለዉ የተለያየ ሀሳብ የቀረበ በመሆኑ ለመወሰን የተቸገሩ መሆኑን በመግለጽ መሪ ትዕዛዝ እንዲሰጣቸው የጠየቁ ሲሆን መመሪያው የሀሳብ ክፍል ስለማያስፈልገውና ስልጣኑም ለክልል በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26(2(ለ)) እና በመመሪያው ሲኤምዲ1/2012 ማሻሻያ ሲኤምዲ 2/2013 አንቀጽ 2(1) መሰረት ክስ እንዲቀርብበት የተወሰነ መሆኑንና ክሱም በዚሁ አግባብ መቅረቡን ያሳያል፡፡ [116]

በፍርድቤት ከቀረቡትና ከተወሰኑት መካከል ሌሎች ብዙ ጉዳዮች ያሉ ቢሆንም እንደምሳሌ ለማሳያ ያህል በግዛቸው ታደሰ እና ዐ/ህግ መካከል በሰሜን ጎንደር ዞን ከ/ፍ/ቤት በወ/መ/ቁ.0201853 ከሚፈቀደው መጠን በላይ 200000 ብር ይዞ መገኘት ወንጀል ክስ ቀርቦለት በቀን 20/3/2015 በዋለው ችሎት በተከሰሰበት የመመሪያውንና የወንጀል ህጉን ተላልፏል በሚል ክስ ቢቀጣውም በይግባኝ የቀረበለት የጉንደር ምድብ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት የወ/መ/ቁ .02-05659 ግን ባንክ በሌለበትና መንግስት ግዴታውን ባልተወጣበት ሁኔታ ወደባንክ ሊያስገባ ወደ ከተማ እየሄደ እያለ መያዙ የወንጀል ድርጊት ሀሳብ የለውም በሚል በነጻ የለቀቀው ሲሆን ይግባኝ ለክልሉና ለፌ/ጠ/ፍርድቤት በሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦም አያስቀርብም ተብሏል፤ እንዲሁም በከሳሽ ዓ/ህግና በተከሳሽ መላክ አስቻለው ደስታ፣ የባህርዳር ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ38949፤ በይግባኝ ባይ ዓ/ህግና በተጠሪ መላክ አስቻለው የባህርዳርና አካባቢዋ ከ/ፍ/ቤት ወ/መ/ቁ 0417610 በቀን 24/6/15 የተወሰነ መዝገብ ላይ 554000 ብር ይዞ ተገኝቷል በሚል በወ/ህ/ቁ 785 እና መመሪያውን በመጥቀስ ክስ ቀርቦ ህጋዊ ነጋዴ በመሆኑና በወቅቱ የህወሃት ወረራ በመሆኑ ለመነገድና ንብረቱን ከዘራፊ ለመከላከል ይዞት ተገኜ እንጅ ህጉን ለመጣስ አይደለም በሚል በወረዳ ተወስኖ ይህነን ለማስቀየር እስከ ሰበር ተጠይቆበት አልተለወጠም፡፡

ይህንን የአተገባበር ልዩነት ለማጥበብም እንደፍትህ ቢሮ ታይቶ የሁሉም አቋም ባይሆንም በአስገዳጅነት ከተፈቀደው መጠን በላይ ገንዘብ ይዞ መገኜት ወንጀል በአዋጁ አንቀጽ 26(2(ለ)) እና በመመሪያው መሰረት ክስ እንዲርብና ክርክሩም እስከ ይግባኝ እንዲታይ የሚል ይዘት ያለው በወንጀል ዘርፍ ም/ቢሮ ሀላፊው በአስገዳጅ ሰርኩላር[117] አስተላልፎል፡፡ ይህ

---

[116] በተከሳሽ ዓ/ህግ እና በተከሳሽ አሸናፊ ታከለ፤ የክልል ዐ/ህግወ/መ/ቁጥር 8/2015፣ የፖሊስ ወ/መ/ቁ 61/2015 ላይ የባህርዳርና አካባቢው ፍትህ መምሪያ በቁጥር 062072 በቀን 11/04/2015 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ትዕዛዝ የተሰጠ መልስ ሲሆን ጉዳዩም በክልሉ ጠ/ፍ./ቤት ክስ ቀርቦበት ሲያከራክር ቆይቶ ለግብይት ይዞ ሲንቀሳቀስ እንጅ ለወንጀል አላማ አይደልም በሚል አመክንዮ በቁጥር ፍ/ቢ/839/መ-17 በቀን 24/08/2015 ዓ/ም ለትክክለኛ ፍትህ ሲባል ከፍርድ በፊት በቢሮ ሀላፊው የተነሳለት፡፡

[117] በቁጥር ፍ/ቢ/ወ/234/16 በቀን 18/03/2016 ዓ/ም ‹የአተገባበር ልዩነት የተፈጠረበትን የወንጀል ጉዳይ ይመለከታል› በሚል ርዕስ በተጻፈ 04 ገጽ ክሱ በመመሪያውና በአዋጁ 26(2(ለ)) መሰረት እንዲሆን በሚል የተላለፈ ሰርኩላር፡፡

ሰርኩላር ወይም የስራ መመሪያወይም መሪ ጥእዛዝ ከበላይ ሀላፊ ወይም ዓ/ህግ ለስራዎች ውጤታማነትና ወጥነት ሲባል አልፎ አልፎ መስጠት በህግም[118] በአሰራርም የተለመደ ሲሆን የስር ባለሙያ የበላዩን ትዕዛዝ እንዲያክብርና እንዲቀበል አስገዳጅነት ያለው ስለመሆኑ ከስነስርዓት ህጉም ሆነ ከተለመደው የበላይ ትኣዛዝ ማለትም ጉዳዮች በይግባኝ ተሸረው እንደሚመጡት አይነት ህጋዊ እስከሆነ ድረስ የመቀበል ግዴታ አለበት፡፡[119] ሆኖም ግን ከላይ የተጠቀሰው ሰርኩላር ባለሙያን የመወሰን ነጻነት የሚጋፋበት ሁኔታ ስለሚኖር፣አስገዳጅነቱም በስሩ ላሉ ዓ/ህግ እንጅ ለፍርድቤትን የማይጨምር በመሆኑ እንደሁኔታው እየታየ ሊተገበር የሚገባና ከዚህ በተቃራኒው መስራት ግን ከአስተዳደራዊ እስከ ወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትልም ይችላል፡፡

ከፍ ሲል ከተገለፀው አሰራር ተቃራኒ የሆነው ሌላኛውን መከራከሪ ሃሳብ ከወንጀል ህግ መርህ፤ ከአዋጁ እና ከመመሪያው አተገባበር አንጻር እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ የወንጀል ህጉ በርዕስ አራት በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን አስመልክቶ ‹‹በህግ መሰረት ስልጣን ባለው አካል በአገር የገንዘብ ወይም የኢኮኖሚ ጥቅም ላይ የሚፈጸም ማናቸውንም ጉዳት ለመቆጣጠር ወይም ለመከላከል በፌድራል ነጋሪት ጋዜጣ ወይም በክልል መንግስታት የህግ ጋዜጣ [ በክልላችን ሁኔታ በዝክረህግ] ላይ የሚወጣን ህግ በመጣስ ወንጀል የተፈጸመ እንደሆነ፤ ቅጣቱ በዚህ የወንጀል ህግ በተመለከቱት መርሆዎች (ከአንቀጽ 343-354) መሰረት እንደሚወሰን[120] የሚገልጽ ሲሆን የዚህ በተዘዋዋሪ ንባብ (*Acontrario* reading) በመሰል ጋዜጣዎች ባልታተመበት ሁኔታ ሊያስጠይቅ እንደማይገባ የደነገገ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡[121] ይህ ባልሆነበት ማለትም በጋዜጣ ባልወጣበት/ባልታተመበት ሁኔታ መመሪያውን የጣሱት በምን ይጠየቁ የሚለውን በወንጀል ህጉ 343(2) ላይ ከ10,000 ባልበለጠ ጉዳይ መጠን እስከሆነ ድረስ በደንብ መተላለፉ

[118] *የወንጀለኛ መቅጫ ስነስዓት ህግ፡* ልዩ እትም 1/1954፣ አንቀጽ 41፡፡
[119] *የአብክመ አስፈጻሚ አካላት እንደገና መቋቋሚያ አዋጅ፣* አዋጅ ቁጥር 280/2014፣ አንቀጽ 28፡፡
[120] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ፣* አዋጅ ቁ. 414/1996፣ አንቀጽ 343(1)፡፡
[121] የወንጀል ሕጉ በርዕስ አራት ስር 2 ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን ምዕራፍ አንድ ጠቅላላ ድንጋጌ በርዕስ 4 ስር ስላሉት ጉዳዮች፤ ምዕራፍ 2 ልዩ ድንጋጌ ከ አንቀጽ 343-354 ያሉት ጉዳዮች የሚመሩበትን የሚያመላክት ሲሆን እንዚህ ጠቅላላ ድንጋጌዎቹ በምእራፍ አንድ (አንቀፅ 343-345) ያሉት በልዩ ህግነት ለተጠቀሱት ከአንቀፅ 345 በኋላ ላሉት ልዩ ድንገጌዎች እንደጠቅላላ ድንጋጌዎች የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ይህ ማለት በወንጀል ህጉ ከአንቀጽ 1-237 ያሉት ጠቅላላ የወንጀል ድንጋጌዎች ለሁሉም የወንጀል ድንጋጌዎች እንደዋና ጠቅላላ ህግ የዚህን ክፍል ርዕስ 4ትን ጨምሮ የሚያገለግሉ ሲሆኑ በርዕስ 4 ምዕራፍ 1 ከአንቀጽ 343-345 ያሉት ጠቅላላ ድንጋጌዎች በርዕስ 4 ስር ለተገለጹት ማለትም በመንግስት ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ብቻ እንደ ልዩ ጠቅላላ ድንጋጌዎች የሚያገለግሉ መሆኑን ከህግ አቀራረጽና ከጠቅላላ የወንጀል ህግ አተረጓጎም መርሆዎች መረዳ ይቻላል፡፡ ይህ ማትም በወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ካሉ መርሆዎች ውስጥ ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ከ 343- 345 ያሉት ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረኑት (በተለይ ቅጣትን የተመለከቱት) እንጅ፣ በለሌሎች ጉዳዮች ላይ የወንጀል ሕጉ ጠቅላላ ክፍል መርሆዎች በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በተመለከተም ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

ሊጠየቁ እንደሚገባ[122] መልስ ስጥቶበት ቢያልፍም ከዚህ መጠን በላይ ለደረሰ ጉዳት ነገር ግን ክልከላው በጋዜጣ ባልታተመበት ሁኔታ ሲሆን ምን ይሁን የሚለውን ግን የሰጠው መልስ የለም፡፡ በሌላ በኩል የሚወጡ ህጎች በጋዜጣ መታተምን እንደግዴታ የሚያስቀምጠው ከላይ በንዑስ ርዕስ 3.1. እንደተዳሰሰው፣ *የፌድራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ* አዋጅ 3/1987 አንቀጽ 2(3) ‹‹*ማናቸውም የፌድራል ወይም የክልል ህግ አውጭ፣ አስፈጻሚና ተርጓሚ አካላት እንዲሁም ማንኛውም ሰው/አካል በፌድራል ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጣን ህግ የመቀበል ግዴታ እንዳለበት*›› *ያስቀምጣል*፡፡ ይህ *ማለት* በጋዜጣ *ካልታተመ* አስገዳጅነት የለውም የሚል *አንድምታ የሚያመላክት* ቢሆነም ይህነን ክፍተት *ለመሙላትና መከራከሪያዎችን ለመዝጋት* የፌድራል ሰበር ሰሚ ችሎቱ *መመሪያዎች* በነጋሪት *ጋዜጣ* አለመውጣታቸው በአዋጁ *መሰረት* እስከወጡ ድረስ ተፈጻሚነታቸው አስገዳጅ አንደሚሆን በሰበር ስልጣኑ አስገዳጅ ትርጉም[123] ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ግን የወንጀል ህጉ የኢኮኖሚ ወንጀሎችን በሚመለከት ለአዋጆች፣ ደንብና *መመሪያዎችም* ቢሆን በፌድራል ነጋሪት ጋዜጣ ወይም በክልል የህግ ጋዜጦች እስካልወጡ ድረስ ተፈጻሚነታቸውን በመገደብ ለክርክር በር በመክፈት አጠያያቂና አሻሚ አድርጎታል፡፡

የጉዳዩ መነሻ የወንጀል ድርጊትነት የሚመነጨው ከወንጀል ህጉ እንዲሁም ከብሄራዊ ባንክ አዋጅ አንቀጽ 26 እና 27 *መሰረት* ሲሆን የአዋጁ እንቀጽ 27 አዋጁን ተከትሎ ደንብና *መመሪያ* የማውጣት ስልጣን *ያለው መሆኑን* ሲደነግግ በአንቀጽ 26 ላይ ደግሞ ‹ስለቅጣት› *ያስቀምጣል*፡፡[124] ቅጣትን በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 26(1(መ)) ላይ እንደተቀመጠው ‹‹ይህን አዋጅ ወይም በአዋጁ *መሰረት* የወጡ ደንቦችን ወይም *መመሪያዎችን* በማናቸውም ሌላ *መንገድ* [ከላይ በዝርዝር ከተገለጹት ውጭ *ያለውን መሆኑ* ነው] የተላለፈ ወይም አተገባበራቸውን *ያሰናከለ* ወንጀል የሰራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በወንጀል ህግ *መሰረት* ይቀጣል›፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት *ያለውና* አዋጁን ተከትሎ የወጣውና ለወንጀል ድርጊቱ መቋቋም ህጋዊነት የወሰነው *መመሪያ* በመግቢያው ላይ አላማውን ህጋዊ የገንዘብ ግብይትንና ፍሰትን ለመጠበቅ እንደሆነና ገንዘቦች ከታለመላቸው አላማ ውጭ እንዳይውሉ ለመጠበቅ ስለመሆኑ ይገልጻል፡፡[125] በዚሁ *መመሪያ ማሻሻያ* በአንቀጽ 3.7 በእንግሊዝኛ ቅጅው በግለሰብ *መያዝ* የሚቻለውን ከፍተኛ መጠን በማስመልከት ‹‹---a person, at one time may hold bank notes up to birr 100,000 and a juridical person up to birr 200,000” **በሚል በግለሰብ እስከመቶ**

---

[122] *የኢፌድሪ የወንጀል ህግ ማሻሻያ ሀተታ ዘምክንያት፣* አንቀጽ 343(1) *ማሻሻያ* አንጻር የተሰጠ *ማብራሪያ*፡፡

[123] በአመልካች እነ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተጠሪ ዳንኤል መኮነን፣የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቅጽ 10፣ መ/ቁ 43781፣ ሐምሌ 14/2002፡፡

[124] *የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ (እንደተሻሻለ)፣* አዋጅ 591/2000፣ አንቀጽ 26 እና 27 ጣምራ ምንባብ፡፡

[125] *የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ መመሪያ*፤ *መመሪያ* ቁጥር ሲኤምዲ (CMD) 01/2020 ወይም በፌ/ጠ/ህግ በጸደቀበት ስምና ቁጥሩ “No.288/2020)፣ *መግቢያ*፡፡

ሽ ብር ብቻ መያዝ እንደሚቻል የሚደነገግ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 4.5 "Any excessive hoarding of bank notes in violation of article 3.7 here in above shall be confiscated in accordance with sub-article 26(1(d)) of proclamation no.591/2000" በሚል ከተፈቀደው መጠን በላይ ይዞ የተገኘ በአዋጁ መሰረት እንደሚወረስበት ቢገልጽም በወንጀል ስለመቀጣት አለመቀጣቱ ግን ያለው ነገር የለም፡፡ ቢሆንም ግን ከመመሪያው ሌሎች ድንጋጌዎችና ከአዋጁ አንቀጽ 26(1)(መ)) አንጻር መመሪያን መጣስን የሚመለከት ጥፋት ወደወንጀል ህጉ የሚመራውን አማራጭ ማስቀመጡን መረዳት ይቻላል፡፡

ይህ መመሪያ ራሱን ችሎ ቅጣት በአንቀጽ 4 ላይ ያስቀመጠ ሲሆን የመመሪያው አንቀጽ 4.4 በተመሳሳይ በመመሪያው አንቀጽ 3.3 ላይ የተቀመጠውን ክልከላ ማለትም ህጋዊ ገንዘቦችን ያለ ባንኩ ፈቃድ ማራባትንም ሆነ ማተምን በወንጀል ህጉና በአዋጁ መሰረት እንደሚያስቀጣ ሲገልጽ በመመሪያው 3.6 ላይ የተቀመጠውን ማለትም ከተፈቀደው መጠን በላይ ይዞ መገኘትን አስቀጭነት በግልጽ ሲደነግግ አንቀጽ 3.7ን ማለትም ከፍኛው የገንዘብ መጠን ገልጾ አስቀጭነቱን በተመለከተ በዝምታ ማለፉ የአዋጁ አንቀጽ 26 እንዲተገበር ፈልጓል ወይም ደግሞ ከአስተዳደራዊ ሀላፊነት የዘለለ ክልከላ ማደረግን አልፈለገም የሚል ትርጉምን የሚያመለክትና በወንጀል ተጠያቂ ለማድረግ አሻሚነትን የሚፈጥር ነው፡፡

ሆኖም ግን የመሻሻሉ ምክንያት ባይገለጽም እንኳን በማሻሻያው CMD02/2021 ወይም No.786/2021 በአንቀጽ 2(1) ላይ ተጨማሪ አንጽ 3.7[126] በማሻሻል በግልሰብ መያዝ የሚቻለው የገንዘብ መጠን በአንድ አመት ልዩነት ከመጀመሪያው መመሪያ የ1,500,000 ብር በግልሰብ ወደ 100,000 ብር በድርጅት ወደ 200,000 ብር ብቻ የተፈቀደ መሆኑን አውርዶ በማሻሻል የሚደነገግ ሲሆን ለዚሁም ከቀድሞው መመሪያ ያልነበረና በተጨማሪ አንቀጽ ከ 4.4 ቀጥሎ በመጨመር አንቀጽ 4.5[127] ላይ ከተፈለገው መጠን በላይ ይዞ መገኘት በወንጀል ህጉ መሰረት አስቀጭነቱን ሳይጠቅስ ገንዘቡ ግን መወረስ ያለበት መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ህጋዊ ሰው (ድርጅት) እስከ ሁለት መቶ ሽ ይፈቀድለት እንጅ ከዚህ ባለፈ ለሌሎች አካላት ገንዘብን የማከማቸትና የመቆጠብ ተፈጥሯዊ ስራቸው ከሆኑት ተቋማት ውጭ የተፈቀደ ነገር ያለ ስለመሆኑ ከመመሪያው ላይ ካለመኖሩም በላይ ለማግኘት የተደረገው ጥረትም በአጥኙው አልተቻለም፡፡

---

[126] *የህጋዊ ገንዘብ ጥበቃ ማሻሻያ መመሪያ፣ መመሪያ* ቁጥር CMD02/2021 ወይም በፌደራል ጠ/ህግ በጸደቀበት ስምና ቁጥሩ "Legal Tendere Protection Directive No.786/2021፣ 2(1)

[127] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 2(2)፡፡

*መመሪያው መጠቀሱ እንደተጠበቀ ሆኖ የአዋጁ ሁለት ድጋጌዎች ማለትም ወደ ወንጀል ህጉ የሚመራው አንቀጽ 26(1(መ)) ተጠቅሶ 353(1ረ)) ወይስ በቀጥታ እስከ 15 ዓመት የሚያስቀጣውን አንቀጽ 26(2(ለ)) የሚለውን ከማየታችን በፊት የወንጀል ህግ የማውጣትን ስልጣን እንመልከት፡፡ የወንጀል ህግ የማውጣት ዋና ተግባር በህገመንግስቱም*[128] *ሆነ ከስሜነህ ኪሮስና ቸርነት ሆርዶፋ*[129] *ሀሳብ ስንነሳ የወንጀል ህግ ማውጣት የህግ አውጭው ምክርቤት ሀላፊነት ስለመሆኑና ለሌላ አካል ተላልፎ ልሰጥ እንደማይገባ ይገልጻሉ፡፡ ምናልባትም ከስልጣንም ሆነ ከአተገባር ጋር በተያያዘ የህግ ግጭት በሚከሰትበት ጊዜ ውጤታማና የህግ ቅቡልነት ያለው አተረጓጎምን መከተል የሚኖርብን ሲሆን ከዚህ አንጻር የህግ ምሁራን* "the provisions of special penal legislations and the penal provisions of administrative legislation may be interpreted in conformity with the principles of the General Part of the Criminal Code."[130] *በሚል ማለትም በግርድፉ ሲተረጎም ልዩ የወንጀል ቅጣት ድንጋጌዎች እና የአስተዳደራዊ ህግ የቅጣት ድንጋጌዎች ሲተረጎሙ ከጠቅላላ የወንጀል ህግ መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ መሆን እንዳለበት*[131] *ይገልጻል፡፡ እንዲሁም ደግሞ ህግ ማውጣት ፍትህንና ፍትሀዊነትን ማስፈን ስለመሆኑና ይህን ያላመከለ ህግ በሚያጋጥማቸው ጊዜ ፍርድቤቶች ሲተረጉሙ ምክንያታዊነትና ፍትሀዊነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ* "Lawmaking is "value Creation for justice and fairness and when the law fails to achieve that, the courts are there "to ensure rationality and justice in the law" through interpretation to achieve justice."[132] *በሚል ያስቀምጣሉ፡፡ እንዲሁም ደግሞ ስለሚተረጎሙበት አግባብ ምሁራን ሲገልጹ*

"Interpretation is the bridge between the text of the law and the fact situation in real life. It is through interpretation and application that the criminal law is 'transformed' into reality and enters into the social consciousness. The effect of interpretation may be deciding the law inapplicable or void."[133]

*በሚል ማለትም አተረጓጎም የፍሬነገርና የህጉ ማገናኛ ድልድዮች እንደሆኑና ህጎችንም ህጋዊየሆኑትን ህጋዊም ሆነ ህገወጥየሆኑትን ህገወጥና ተግባራዊ እንደማይሆኑ ትርጉም*

---

[128] *የኢፌድሪ ህገመንግስት፣* አዋጅ ቁጥር 1/1995፣ አንቀጽ 55(5)፡፡

[129] Simeneh Kiros & Chernet Wordofa (2017). "'Over-criminalization': A Review of Special Penal Legislation and Administrative Penal Provisions in Ethiopia", XXIX(1) Journal of Ethiopian Law, 49-83. [83].

[130] Simeheh Kiros (2017), Methods and Manners of Interpretation of Criminal Norm", 11(1), Mizan Law Review, 88-124. Pp119.

[131] *ዝኒ ከማሁ* (ትርጉም በጸሐፊው)፡፡

[132] Simeheh Kiros (2017), Methods and Manners of Interpretation of Criminal Norm", 11(1), Mizan Law Review, 88-124.pp 121.

[133] *ዝኒ ከማሁ* 112-113፡፡

*በመስጠት እውነተኛውንና ትክክለኛውን ማህበራዊ ተግባቦትን የሚፈጥርና የሚያሸጋግር እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡*[134]

ስለሆነም ከላይ የተቀመጡትን የህግ አወጣትና አተረጓጎም መርሆወችን ይዘን ወደርዕስ ጉዳዩ ስንመጣ መመሪያው መጠቀሱ እንደላ ሆኖ በአዋጁ የትኛው ድንጋጌ ማለትም በከባዱ የአዋጁ ክፍል አንቀጽ 26(2(ለ)) ወይስ መመሪያው በሚለው 26(1(መ)) የሚለውን መከራከሪያ ስንመለከት፡-

1ኛ/ የድርጊቱ አስቀጭነት የሚመነጨው ከዚሁ ከመመሪያው የከፍተኛ ገንዘብ መጠን መደንገግና ክልከላ ጋር ተያይዞ የሚመነጭ መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ በምን አግባብ ይጠየቅ የሚለውን ደግሞ እንዲጠየቅልኝ የፈልግሁት በአዋጁ አንቀጽ 26(1(መ)) ነው በሚል ማስቀመጡ ምንም እንኳን ወንጀል በአዋጁ የሚደነገግ በመሆኑ የመመሪያውን ጥቆማ ዋጋ ቢያሳጠውም የመመሪያ ህግ አውጭውን ሀሳብ ግን ሊጠዩቅበት የፈለገውና መመሪያው ሊያረጋግጠው የፈለገውን ግብ በአዋጁ የተቀመጠውን መሆኑን መረዳት ስለሚቻል በዚሁ አግባብ ማየቱ ከወንጀል ህግ አተረጓጎም መርህ ውጭ ሊያስብል አይችልም፡፡

2ኛ/ መመሪያው ራሱ ከስሙ እንኳን ስንነሳ "Legal tender protection" ወይም ‹ህጋዊ የጥሬ ገንዘብ ጥበቃ› የሚልና የመመሪያውን ድንጋጌ በመተላለፍ ገንዘብ ማከማቸት[135] በአዋጁ አንቀጽ 26(1(መ)) እንዲጠየቅ በሚል በወንጀል መጠየቁን በቀደመው አግባብ የነበረውን ድንጋጌ ይዘት በመተው ሳያሻሽል አወራረሱን በተመለከተ ግን ይወረስ ማለቱ ሲታይ አዋጁ ወደ ወንጀል ህጉ የሚመራበትን አንቀጽ 26(1(መ))ን ከመጥቀስ ይልቅ በቀጥታ በአዋጁ አንቀጽ 26(1(መ)) መሰረት ይጠየቅ ወይም ደግሞ ከገንዘብ ጋር የተያያዘ መመሪያና ገደብ እንደመሆኑ መጠን በቀጥታ የአዋጁን አንቀጽ 26(2(ለ))ን በመጠቀስ በዚሁ አግባብ ይጠየቅ በሚል ያስቀመጥ ነበር የሚል አመክንዮን የሚያመላክትበት ሁኔታ አለ፡፡ ነገር ግን ከዚህ በማለፍ ከገንዘብ ጋር በተያያዘ የሚወስን መመሪያ እንደሆነ እየታወቀ ወደ ወንጀል ህጉ የሚያመራውን የመመሪያም ሆነ የአዋጁን አንቀጽ 26(1(መ)) ክፍል በመተው በተከሳሽ ላይ የበለጠ የሚያከብደውን ማለትም ‹‹ድርጊቱ የተፈጸመው …ገንዘብ.. ጋር የተያያዘ ከሆነ…›› የሚለውን ነጥሎ መጠቀሙ ከተከሳሽ መብትም ሆነ ከወንጀል ህግ ጠቅላላ አተረጓጎም መርህን[136] ከሚደነግገው እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በሰ/መ/ቁ 81178[137] እንዲሁም በሰ/መ/ቁ

---

[134] *ዝኒ ከማሁ* (ትርጉም በጸሐፊው)፡፡
[135] *ዝኒ ከማሁ፣* አንቀጽ 2(3)፡፡
[136] *የኢፌድሪ ወንጀል ህግ፣* አዋጅ ቁጥር 414/1996፣ አንቀጽ 2፡፡
[137] የፌ/ገቢዎች ዓ/ህግ እና እንከበደ ተሰራ (2 ሰዎች)፤ የፌ/ሰ/መ/ቁ 81178፣ በቀን መስከረም 21/2006 ዓ/ም የተወሰነ፡፡

38161[138] በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ክስ ስለድርጊቱና አፈጻጸሙ የሚሰጠው መግለጫ ድርጊቱን ወንጀል ከሚያደርገው ህግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንዳለበትና አሻሚ በሚሆን ጊዜ ለተከሳሹ በሚጠቅም መልኩ መተርጎም እንዳለበት ጭምር ከሰጠው አስገዳጅ ትርጉም የሚያፈነግጥና የሚጋጭ ነው፡፡

3ኛ/ ማንኛውም በብዙ መጠን ጥሬ ገንዘብ ማከማቸት "Any excessive hoarding of bank notes" የሚለው ለምን አላማና በምን ሁኔታ እንዲሁም የሀሳብ ክፍል የሚለው በግልጽ አለመቀመጡ ማንኛውም ሰው በማንኛውም ሁኔታ ይዞ መገኘት ብቻውን በቂ እንደሆነ በመረዳትና በመተረጎም በመመሪያውና በአዋጁ አንቀጽ 26(2(ለ)) መሰረት ክስ እንዲቀርብ በመመሪያና ሰርኩላር ጭምር የታዘዘ ስለሆነ አሁንም በዚሁ አግባብ ክስ እየቀረበ ነው፡፡ ሆኖም ግን በግልሰብ ከሚፈቀደው መጠን በላይ ገንዘብ ይዞ የተገኜ ሁሉ በመመሪያው (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 4.4 እና 4.5 ላይ በአዋጁ አንቀጽ 26(1(መ))ና ተያያዥነት ባላቸው የወንጀል ህጉ ይቀጡ እያለ ወደ አዋጁ አንቀጽ 26(2(ለ))[139] መውሰዱ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 2(3) ላይ የተቀመጠውን ማለትም በወንጀል ህጉ በይመሳሰላል እና ከህግ አውጭው አላማና ግብ በመውጣት መተርጎም እንዳይሆን፤ እንዲሁም ደግሞ የመመሪያውን አለማና መግቢያ ጭምር በተመጋጋቢ ምንባብ በድጋሚ ተገናዝቦ በአዋጁ በተቀመጠው የብሄራዊ ባንክ አለማና ግብ መሰረት ፍትህ ቢሮው ሊሰራበት የፈለገውን አቋም በድጋሚ በግልጽ መመሪያ ቢሰጥበትም በድጋሚ ከተከሳሽ መብትና ከወንጀል ህግ መርህ አንጻር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ይህም በመመሪያውና በአዋጁ አንቀጽ 26(1(መ)) እና በወንጀል ህጉ 353(1(ረ)) ማክበድ ቢያስፈልግ እንኳን 354 መሰረት ክስ እንዲቀርብ፤ ፍርድ ቤቶችም ሊከተሉት የሚገባ የህግ፣ የማስረጃና የፍሬነገር ምዘና አተያይ አመላካች ሁኔታዎች ከላይ በተጠቀሰው አግባብ ሊተረጉሙና ለወደፊት በግልጽ በህግ ማሻሻያ መልስ ሊያገኝ እንደሚገባ ያመላክታል፡፡

4ኛ/ በአዋጁ ይህን አዋጅ በሚቃረን መልኩ የሚወጡ መመሪያዎች ተግባራዊ እንደማይሆንና ተፈጻሚነት እንደሌላቸው አዋጁ ራሱ በአንቀጽ 28[140] ላይ ስለሚገልጽና ክልከላውም ብሄራዊ ባንክ ባልተሰጠው ስልጣን ላይ ያወጣው መመሪያ ስለሆነ ተግባራዊነት የለውም[141] የሚለው መከራከሪያ የመመሪያውን ከወንጀል ፍሬ ነገር ድርጊት ህጋዊነት አንጻር አጠያያቂና የሚያወዛግብ እንደሆነ መግለጹን ከአቶ ስንታየሁ ቸኮል ጋር የተደረገ ቃለምልልስ

---

[138] አመልካች እነጀሚላ መሀመድ እና በተጠሪ የፌ/ዓ/ህግ፤ ፌ/ጠ/ፍ/ሰ/ችሎት ፋ/ቁ 38161፤ በቀን የካቲት 19/2001 ዓ/ም፡፡

[139] *የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ (እንደተሻሻለ)፣* አዋጅ 591/2000፣ አንቀጽ 26፡፡

[140] *ዝኒ ከማሁ፣* አንቀጽ 28(3)፡፡

[141] ስንታየሁ ቸኮል (ተራ ቁጥር 66)፡፡

የሚያስረዳን ሲሆን ይህም ለመሰልጉዳይ በግልጹ አዋጁ የገንዘብ እንቅስቃሴ ገደብ ሊኖር እንደሚችል ያመላከተበት ቦታ የለም፡፡ እንዲሁም መመሪያው የተመዘገበ ቢሆንም ተገቢው ውይይት ከሚመለከተው አካል ጋር ረቂቁ ቀርቦ ውይይት ስለመደረጉ፣ የማብራሪያ ጽሑፍ ስለመኖሩ፣ ተደራሽነቱ አብዛኛውን የኢትዮጲያ ህዝብ ያማከለ ስለመሆኑ[142] ጸሐፊው ባለማግኙቱ የተሟላ አሰተያየት መስጠት ባይቻልም ተደራሽነቱና በመመሪያው ላይ የህዝብ ጥሪ ተደርጎ ውይይት አለመደረጉን ግን ከነበረው ወቅታዊና የድግግሞሽ ማሻሻያ እንዲሁም አጥኝው በተቋሙ ድረገጽ ባለማግኜቱ ተገቢውን አካሄድና የህዝብ እውቅና እንደልተፈጠረበት ጠቅላላ ግምት መውሰድ ይቻላል፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ገደብ ማድረጉ ደግሞ አይደለም ለማንኛውም ሰው ቀርቶ ለህግ ባለሙያም ለገደቡና ተጠያቂነቱ አሻሚ መሆን ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡ ለዚህም መመሪያው ከሚፈለገው መጠን በላይ መያዝን ክልከላ የሚመለከተውን ብቻ በመጠቆም በምን እንደሚቀጣ አሳይቶ እያለ በአዋጁ አንቀጽ 26(2(ለ)) ገንዘብ የሚለውን ነጠላ ጉዳይ ብቻ በመውሰድ ሳይሆን ሌሎችንም ከባባድ ጉዳዮች ማለትም፣ ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀምን፤ በከፍተኛ መጠን ከሀገር ውስጥ ገንዘብ ማስገባትና ማስወጣን፤ በከፍተኛ ሁኔታ ለሀገር አደጋና ስጋ ሊያመጡ የሚችሉ ጉዳዮችን በመጥቀስና ይህም ድርጊት ከገንዘብ ጋር ከተያያዘ ሊጠየቁበት ይገባል በሚል ካስቀመጠው የአዋጁ ከባዱ ክፍል ጋር በማቀራረብ በአዋጁ አንቀጽ 26(2(ለ)) መሰረት እንዲጠየቁ ማደረጉ የወንጀል ህጉንም ሆነ የመመሪያውን መውጣት አላማ ካስቀመጠው የመግቢያው ክፍል ከተቀመጠው ማብራሪያ ባፈነገጠ መልኩ መተርጎም የሚመስል አንድምታን የሚያመላክት በመሆኑ በተዋረዱ ላሉ የህግ ባለሙያዎች የልዩነት ምንጭ ከመሆኑም በላይ በተከሳሽ ላይ ከህግ አውጭውና ከጠቅላላ የወንጀል ህግ መርህ በመውጣት በከባዱ እንዲከሰስ እየተደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡

ሌላው መልስ ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ‹መመሪያው ወደ ወንጀል ህጉ የሚያመራበት አንቀጽ 26(1(መ))[143] ተግባራዊ ይደረግ ከተባለ ቅጣትን አስመልክቶ ‹…በወንጀል ህግ መሰረት ይቀጣል ስለሚል› የትኛውን የወንጀል ድንጋጌ ለማለት ፈልጎ ነው?› በምንልበት ጊዜ አግባብነት ያለቸው ነገር ግን አሻሚ የሆኑት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 785፤343፤344፤ 346፤ 353(1(ረ)) እና 354[144] ሲሆኑ አንቀጽ 343 እና 344 እንዲሁም 785 ድርጊቱን በዋናነት ወንጀል የሚያደርገው አዋጅ 591/2000 ባልወጣበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ይህ አዋጅ ወጥቶ

---

142 *የፌደራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ*፣ አዋጅ ቁጥር 1183/2012፣ መግቢያ፣ አንቀጽ 14፣ 17፡፡

143 *የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ (እንደተሻሻለ)*፣ አዋጅ 591/2000፣ አንቀጽ 26(1(መ)) ‹‹ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ወይም በአዋጁ መሰረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በማናጨውም ሌላ መንገድ የተላለፈ ወይም አተገባበራቸውን ያሰናከለ እንደሆነ ወንጀል የሰራበት ሀብት መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ በመንጀል ህግ መሰረት ይቀጣል››፡፡

144 የኢፌድሪ ወንጀል ህግ፣ አዋጅ ቁጥር 414/1996፣ አንቀጽ 343፣344፣346፣ 353(1(ረ))፣ 354፡፡

እያለና ይህነንና ተከትለው የሚወጡ መመሪያዎችን መተላለፍ ወንጀል እንደሆነ በደነገገበት ሁኔታ ተፈጻሚነታቸው አጠያያቂ ነው የሚል አቋምን መያዝ ይቻላል፡፡ አዋጁ በአንቀጽ 28(2) ላይ እንደደነገገው ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ህግ፤ ደንብና መመሪያ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት እንደሌለው ያስረዳል፡፡ በሌላ በኩል እነዚህ ድንጋጌዎች የገንዘብ ጉዳት መጠኑ ከ10,000 ብር ካነሰና ክልከላው በነጋሪት ጋዜጣ ወይም በክልል ዝክረ ህግ ካልወጣ የደንብ መተላለፉ መተግበር እንዳለበት በወንጀል ህጉ 343(2) እና 785[145] መሰረት ሊጠየቅ እንደሚገባ የሚነሳ መከራከሪያና አሰራር በጠባቡም ቢሆን ለደንብ መተላለፍ አለ፡፡ ቢሆንም ግን በፌድራል መንግስቱ ገንዘቦች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ግን በፌድራል ፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013[146] መሰረት ጉዳዩ የፌድራል በመሆኑ፣ በቅጣት መጠናቸው መሰረት የፌድራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ስልጣን በመሆናቸው ጉዳዩን ለማየት ስልጣኑን በውክልና  ለያዘው ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድቤት በመሆኑ[147] ከተፈቀደው በላይ የተያዘው ብር እጅግ አነስተኛ ቢሆንም ጭምር ወደ ደንብ መተላለፍ የሚያስኬድ ምክንያት ወይም አመላካች ህግ አለመኖሩን ወይም ደግሞ ጠባብ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ የገንዘብ ጉዳት መጠኑን አስመልክቶ የወንጀል ህጉ በግልጽ ባያስቀምጥም በአዋጁ 26(1(መ))፣ በወንጀል ህጉ 353(1(ረ))ና በመመሪያው መሰረት አነስተኛ ገንዘብ ጉዳት ላላቸው እንዲጠየቁበት ማስቀመጡን፤ እንዲሁም ደግሞ ከፍ ያለ ጉዳትና የገንዘብ መጠንን የሚመለከት ሲሆን ግን የወንጀል ህጉ አንቀጽ 354፤ የአዋጁ 26(1(መ)) እና መመሪያ ተጠቅሶ እስከ 15 ዓመት ሊጠየቁ እንደሚገባ ማስቀመጡን የሚቀርብ መከራከሪያ ያለ ሲሆን ከቅጣት መጠን አንጻርም በአዋጁ አንቀጽ 26(2(ለ)) ከተቀመጠውም ሆነ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 354 ላይ የተቀመጠው መቀጮው ልዩነት ቢኖረውም ከአስራት ረገድ እስከ 15 ዓመት ጣሪያ አስቀጭነትን የሚያስቀምጥ በመሆኑ ልዩነት አለመኖሩን መረዳት የሚቻል ሲሆን የገንዘብ መጠነኑን ተንተርሶ አክብደና አቅልሎ ክስ የሚቀርብበት እድል በወንጀል ህጉ ሲኖር በአዋጁ ግን የሌለ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

ከላይ እንደተብራራው ጠቅላላ የወንጀል ህግ መርህ[148] ቢኖርም  የኢኮኖሚ ወንጀሎችን በሚመለከት ጠቅላላው ልዩ መርህ ለአዋጆች፣ ደንብና መመሪያዎችም ሲሆን እንደጠቅላላ መርህ የሚሰራው ይህ የኢኮኖሚ ወንጀሎች ልዩ ህግ ነገር ግን ጠቅላላ መርህ በልዩነት በፌድራል ነጋሪት ጋዜጣ ወይም በክልል የህግ ጋዜጦች እስካልወጡ ድረስ  ተፈጻሚነታቸውን

---

[145] *ዝኒ ከማሁ*፣ አንቀጽ 343፤ 785፡፡

[146] *የፌደራል ፍርድቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ*፡ አዋጅ 1234/2013፣ አንቀጽ 4 (11 እና 12)፣ 12(1 እና 3) እና 15(1 እና 3)፡፡

[147] *ዝኒ ከማሁ*፡፡

[148] *የኢፌድሪ ወንጀል ህግ*፡ አዋጅ ቁጥር 414/1996፤ አንቀጽ 1-237፡፡

በመገደቡ ለትርጉም የተጋለጠና ለክርክር በር በመክፈት አግባብነት ያለውን ድንጋጌ አስመልክቶም አጠያያቂና አሻሚ አድርጎታል፡፡ እንዲሁም እናት(የበላይ) ህጋቸውን ማለትም አዋጁንና ደንቡን ጠብቀው መውጣት፤ መብቶችንም በማያጣብቡና በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት መውጣት ስላለበቻው ሲተረጎሙም በማይቃረንና ከወንጀል ረገድ የተከሳሽን መብት በማያጣብብ መልኩ ሊወጡና ይህነን መርህ በመጣስ ከወጡም ይህን አውድ በጠበቀ መልኩ ሊተረጎሙ ይገባል የሚል እምነት አጥኚው አለው፡፡

መሰል አሻሚ ጉዳዮች ባሉበት ሁኔታ የወንጀል ህግ አተረጓጎም መርህን በምንፈትሽበት ጊዜ ወንጀል የሚመነጨው ህጋዊ፣ ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ መሆን እንዳለበት[149]፤ ህገወጥነቱ በግልጽ ድርጊትና ግድፈት አስቀጭነቱ እስካልተወሰነ ድረስ እንደወንጀል ተቆጥሮ መቀጣት እንደሌለበት እና አሻሚ በሚሆን ጊዜ በይመሳሰላል በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር ሊቀጣ እንደማይገባና ህጉ አሻሚ ሆኖ በሚተረጎምበት ጊዜ ህጉ ሊደርስበት ያሰበውን ግብ ለማረጋገጥ እንዲቻል ህግ አውጭው ባቀደው ትርጉምና በህጉ መንፈስ መሰረት ሊተረጎም እንደሚገባ፤[150] በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ክስ ስለድርጊቱና አፈጻጸሙ የሚሰጠው መግለጫ ድርጊቱን ወንጀል ከሚያደርገው ህግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ፤ የህጉን መንፈስና አላማ ያገናዘበ መሆን እንዳለበትና ፍርድቤቶችም በዚሁ አግባብ ውሳኔውን ሊያጤኑት እንደሚገባ በተመሳሳይ ሁኔታ ፌድራል ሰበር አስገዳጅ ትርጉም[151] ተሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ይህነን አስመልክቶ የህጉን ጠቅላላ መርህና የወንጀሉን ባህሪ እንዲሁም የሰበር ሰሚ ውሳኔዎችን ባገናዘበ መልኩ በጊዜያዊነት የአሰራርና የመመሪያ፣ በዘላቂነት የህግና መመሪያ ማሻሻያ በማድረግ ምላሽ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

ሌላው በጥናቱ የተዳሰሰው ጉዳይ በተከሳሾች የሚነሱት የመከላከያ መከራከሪያዎች ማለትም ‹‹ገንዘቡን ወደባንክ ላስገባ ስሄድ ነው እንጅ ለህገወጥ ድርጊት መፈጸም አይደለም፣ ያመረትሁትን እቃ በጅምላ ወይም በችርቻሮ ሽጨ ባንክ ወዳለበት ወስጄ ላስገባ እንጅ ከግብይት አሰራር ውጭ ለመደበቅ/ላስቀምጥ አስቤ አይደለም፣ የቀንድ ከብት ወይም ከአርሶ አደር በለቀማ የምገዛ የእህል ነጋዴ በመሆኔ ልገዛበት ይዤ እየሄድሁ ወይም ሽጨ የያዝሁትና ለግብይት ልጠቀምበት እንጅ ለመደበቅ ወይም ከግብይት ስርዓት ውጭ ለማድርግ ይዤ ስሄድ አልተገኘሁም እና የመሳሰሉት›› ተጠቅሰው በመከላከያነት ሲቀርቡ አስቀድሞ በምርመራ

[149] *ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ* 23(2)፡፡
[150] *የኢፌድሪ ወንጀል ህግ፣ አዋጅ ቁጥር* 414/1996፤ *አንቀጽ* 2(2-4)፡፡
[151] የፌ/ገቢዎች ዓ/ህገ እና እንከበደ ተሰራ (2 ሰዎች)፤ የፌ/ሰ/መ/ቁ 81178፣ በቀን መስከረም 21/2006 ዓ/ም የተወሰነ፤ አመልካች እነጀሚላ መሀመድ እና በተጠሪ የፌ/ዓ/ህግ፤ ፌ/ጠ/ፍ/ሰ/ችሎት ፋ/ቁ 38161፤ በቀን የካቲት 19/2001 ዓ/ም፡፡

ክፍተቶችን መዝጋትና አሳማኝ ከሆኑ የአያስከስስም ውሳኔ መስጠት አሳማኝነት ከሌላቸው ግን የመከራከሪያ አሻሚ በሮችን መርማሪዎች በምርመራዎቻቸውም ሆነ ዓቃቢያነ ህጎች በተጨማሪ ምርመራ ክፍተቱን መዘጋት እንዳለባቸው ግንዛቤ ሊወሰድበት እና እንደ ፍትህ ተቋማትም በዚሁ አግባብ ትርጉም ሊሰጥበት ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ግለሰቦች ያፈሩትን ንብረት እንዳይጠቀሙ ከመገደብ ባለፈ በወንጀል የመቅጣቱ አግባብነት፤ ባለን የባንክ ተደራሽነትና ኋላቀር የግብይት ስርዓት አንጻር  አርሶአደርና የገጠር ነጋዴው ማህበረሰባችን የብር ኖትን በከፍኛ መጠን ይዞ በመሄድ ካልተገበያየ በስተቀር ግብይት ለመፈጸም የሚገጥመውን የእለት ከእለት ችግር፤ ከ80% አካባቢው ያልተማረ ማህበረሰብ ወይም አርሶ አደር በሆነበት የሀገራችን ክፍል ይህን መመሪያ ማውጣቱ ከገንዘብ በኤሌክትሮኒክስ ግብይት መፈጸም ይልቅ ወደ እቃ በቃ ግብይት (Bartter system) እንዳይመልሰውና የግብይት ስርዓቱን ከማዘመን የበለጠ ወደኋላ እንዳይጎትተው ከሚፈጥረው ስጋት፤ ያልተማረው ማህበረሰብ በኤሌክትሮኒክ ግብይት አለማወቅ የተነሳ ለመጭበርበር የሚዳረግበት ሁኔታ መኖሩ፤ ብሩን ወደባንክ ለማስገባትና ለማውጣት ብሎም በተሳለጠ ለመገበያየት የባንኮችን መጨናነቅና የአርሶ አደር ግለሰቦችን ከገጠር ወደ ባንክ ያለበት ከተማ መመላለሻ ወጭ፣ ጊዜና ጉልበት ብክነት መታደግ አንጻር፤ የሀገሪቱ ተጨባጭ የኢኮኖሚ እድገት ሁኔታ አንጻር ውጤታማ የፋይናንስ ስርዓትን ለማስፈን በሚያስችል መልኩ ታይተውና እንዳስፈላጊነቱ በጥናት ዳብረው ዝቅተኛ መጠኑ በከፊልም ቢሆን ከፍ ብሎ ሊሻሻል የሚገባ ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንዲሁም ደግሞ የሀሳብ ክፍላቸውን ግምት ከመውሰድ ጋር በቀጥታ የሚያያዝና ዓ/ህግ ለመክሰስ ይዞ መገኜት ብቻ በቂው በመሆኑ ከዚህ ባለፈ ማጣራቱ ከተለመደው የፖሊስ ምረመራ ስራ ባህል አንጻር የማይደረሰበትና ባብዛኛው የተከሳሽ መከላከያ መከራከሪያዎች የሚቀርቡ ሲሆን ለማስተባበልና ፍርድቤትን ከጥርጣሬ በጸዳ መልኩ ለማስረዳት መመሪያ እንዲሻሻል መጠየቁ በተጨማሪ ጥናት ማሳየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በምርመራ፤ በክስ እና ክርክር ሂደት ግን ልዩ መንገድን ማለትም ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ልዩ እውቀት ክህሎትና ልምድ ያለው ባለሙያ፤ በምርመራ ወቅት የተጠርጣሪን የሀሳብ ክፍል አስቀድሞ ማረጋገጥና አግባነት ያለው ማስረጃ ማቅረብ፣ በክስ ዝግጅት ወቅት ሀሰተኛ የመከላከያ ማስረጃ ሊያቀርብባቸው የሚችሉ መንገዶችን በተቻለ መንገድ አስቀድሞ በምርመራ ማረጋገጥና አግባነት ባለው ማስረጃ ማስደገፍ፣ እና ሌሎችም እንደጉዳዩ ሁኔታ ልዩ የክርክር መንገዶችን መከተል እንደሚያስፈልግ መረዳት ይገባል በሚል አጥኚው ያምናል፡፡

## 4. ማጠቃለያና ምክረ-ሀሳብ

## 4.1. ማጠቃለያ

አሁን ባለው አደረጃጀት የኢኮኖሚ ወንጀሎች የሚባሉት ከንግድ አሰራር ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን፤ ከፍትህ ሚንስትር በውክልና ከተሰጡ የገቢዎችና ጉምሩክ ወንጀሎችን፤ ከሀሰተኛ የገንዘብ ዝውውር ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን፤ ደረቅ (ስንቅ የሌለው) ቼክን የሚመለከቱ ወንጀሎችን፤ የአራጣ ወንጀልን፤ በታወቁ ገንዘቦች፣ የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን፤ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ህጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን እና ተያያዝ ጉዳዮችን፤ ከፀረ-ንግድ ውድድርና ሸማቾች መብት ጥበቃ ጋር የተያያዙ ወንጀሎችንና ተያያዥ ጉዳዮችን፤ በግብርና ታክስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሲሆኑ ልተካተቱ ሌሎችም ግን ያሉ መሆኑ ተረጋግጧል ። በመንግስት የኢኮኖሚና የገንዘብ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች እና በገንዘብ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በወንጀል ህጉ ከአንቀጽ 343-354 እና በአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26 ላይ የተዘረዘሩት ; በመመሪየው የተደረጉ ክልከላዎችን በመተላለፍ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች ተጠያቂነት ግን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች አስመልክቶ መሰረታዊ ልዩነት ያለ ሲሆን የሚከሰሱበት ድንጋጌ በተመሳሳይ ድርጊት ከስረነገር ስልጣን ጋርም ይሁን ከድንጋጌ አንጻር ልይነቱ ጉልህና ሰፊ ነው።

በክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በግል መያዝ ከሚፈቀደው ጥሬ ገንዘብ መጠን በላይ ይዞ መገኘት ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች በአብዛኛው እየተከሰሱ ያሉት  በመመሪያውና በአዋጁ 591/2000 አንቀጽ 26(2(ለ)) ቢሆንም ጥፋተኛ እየተባሉ ያሉት በመመሪያውና በወንጀል ህጉ አንቀጽ 353(1(ረ)) ሲሆን በይግባኝ ስርዓት ሂዶ የተለወጠ ነገር አጥኝው አላገኘም። ህጉ ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ማለትም የመመሪያ ክልከላውን መነሻ በማድረግ እጅግ የተጋነነ 15 ዓመት ጽኑ አስራት፣ መቀጮና ገንዘብ መውረስ ከመሆኑ አንጻር  በዚህ በአዋጁ አንቀጽ 26(2(ለ)) እንዲጠየቁ መደረጉ ባህላዊ የግብይት መስተጋብሩን በከፍተኛ ቅጣት የሚጎዳ በመሆኑ ፍትሀዊና ምክንያታዊ እንዲሁም አሳማኝ አይደለም። በአዋጁ 591/2000 አንቀጽ 26(2(ለ)) ክስ ሊቀርብ የሚገባው በግልጽ ገንዘብን ከሀገር ለማስወጣጥና ለማስገበት መሰል ትልልቅ ጉዳዮች እንጅ ጥሬ ብር ይዞ ለተገኘ በዚህ ድንጋጌ ማስጠየቁ ከአዋጁ አውድና መንፈስ ውጭ ይመስላል። ስለሆነም የመመሪያ ማሻሻያና የህግ ማብራሪያ(ትርጉም) የዋጋ ግሽበቱን፣ የሀገሪቱንና የማህበረሰቡን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ከሚመለከተው የበላይ አካል ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ተደርጎ አንድም የገንዘብ መጠን ወሰኑ ከፍ ብሎ ሊሻሻል ይገባል፤ ይህ ካልሆነም ወጥ የህግ አተረጓጎምን በበላይ ተርጓሚ (የፌድራል ሰበር ሰሚ ችሎት) ወይም በመመሪያውን ያወጣው ህግ አውጭ አካል ማለትም ብሄራዊ ባንክ በኩል  ታይቶ በወ/ህ/ቁ 353(1(ረ)) እና በአዋጁ 591/2000 አንቀጽ 26(1(መ)) አነስተኛና ከፍተኛ መጠን ባላቸው የገነዘብ መጠኖች

ላይ፤ በጣም ከፍተኛና በሆኑት ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 591/2000 አንቀጽ 26(1(መ)) እና በወ/ህ/ቁ 354 መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡

## 4.2. ምክረ-ሀሳብ

ሀ. የኢኮኖሚ ወንጀሎች ባህሪና አተገባበር ላይ ውስንነት ያለ በመሆኑ ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ የህግ ባለሙያዎችና የማህበረሰቡ ግንዛቤ ስልጠናዎች ቢሰጡ፤ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ቢሰራ፤

ለ. በግለሰብ እንዲያዝ ተፈቀደው የጥሬ ገንዘብ መጠን ከሀገሪቱ እድገትና ከማህበረሰቡ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ዝቅተኛ መጠን በመሆኑ ለወደፊቱ የዋጋ ግሽበቱን፤ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት እንዲሁም የማህበረሰቡን የእውቀት ግንዛቤ ግምት ውስጥ ያስገባ ከፍ ወዳለ ገንዘብ መጠን ቢሻሻል፤

ሐ. ከምርመራ እስከ ክስ እንዲሁም እስከ ፍርድቤት ክርክር ያለው ስራ በተገቢው ትኩረት እየተሰራ የተጠርጣሪዎችን የሀሳብ ክፍል በተገቢው አጣርቶ ተጠያቂነቱ አላማውን በሚመጥንና የግለሰቦችን ሀብት የማፍራትና ይዞ የመንቀሳቀስ መብት ባልገደበ መልኩ ቢተገበር፤ የሚል ምክረሀሳብ ያቀርባል፡፡

# በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ በአማራ ክልል

**ዳኘነት ይግዛው ዘለቀ***

**Abstract**

Recovery of asset to the real owner needs special attention to protect fail of state economy and working properly asset recovery leads to those criminal offenders committed a crime for the benefit of economy makes them restraint and lesson from commit other offences. Despite economic crimes come up to increase time to time in the region, failure of giving special attention to asset recovery is cause of the study. In fact, in other countries, there is well experience and enforcement to stolen asset recovery; however, both institutional and legal frameworks of Ethiopia and Amhara region are weak as long as strengthen it. Though the notion of asset recovery was well known in Ethiopia, there had no responsible organ which was practically done. Due to these factors, there is obvious to see economical offenders use legal and institutional gaps to commit a crime and maximum they penalize only sentence without return the property. According to the finding, to confiscate stolen asset recovery there is no strong special law and institution in Amhara region, it tries to use Ethiopia's scattered laws even they did not well practice with their legal gaps. So, since it results asset recovery is not practically perform in the region, the author recommends to the government for giving high attention both special strong institutional establishment and legal frameworks.

**Keywords**: - Asset recovery, confiscation, proceeds of crime, proportionate property

* ፀሐፊው በ2003 ዓ.ም. ከመቐለ ዩኒቨርስቲ ህግ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ዲግሪውን ያገኘ ሲሆን ሁለተኛ ዲግሪውን በ2013 ዓ.ም በመዋዕለ_ነዋይና አስተዳደር ህግ /investment law and governance/ ከደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ አግኝቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአብክመ ፍትህ ቢሮ በክልል ዐቃቤ ሕግነት እየሰራ ይገኛል፡፡ ለማንኛውም አስተያዬት ፀሐፊውን በኢሜል dagninetyigzaw18@gmail.com ማግኘት ይችላሉ፡፡

**አህፅሮተ-ፅሁፍ**

በወንጀል የተገኘን ሀብት በተገቢው መንገድ ወደ ትክክለኛ ባለቤቱ ማስመለስ ልዩ የስራ እንቅስቃሴ የሚያስፈልገውና የሀገርን ኢኮኖሚ ከውድቀት የሚታደግ እንዲሁም ወንጀል ፈፃሚዎች ለኢኮኖሚ ጥቅም ብለው ወንጀል በመፈፀም ያገኙትን ሀብት ተከታትሎ በማስመለስ እንዳይጠቀሙበት ማድረግ ሌላ ተመሳሳይ ወንጀል እንዳይፈፀም በማስጠንቀቅና በመከላከል ረገድ ያለው አስተዋፅኦ ላቅ ያለ ነው፡፡ የኢኮኖሚ ወንጀሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ የመጡ ቢሆንም በዚያው ልክ በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ አለመሆኑ የጥናቱ መነሻ ነው፡፡ በሌሎች ሀገሮች የተሻለ ልምድና አፈፃፀም ያለ ሲሆን በኢትዮጵያም ሆነ በአማራ ክልል ደረጃ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስን በተመለከተ በህግ ማዕቀፍም ይሁን በተቋም ደረጃ የተጠናከረ ባለመሆኑ ልዩ ትኩረት በመስጠት መስራት የሚያስፈልግ መሆኑ ግንዛቤ ያሻል፡፡ በሀገራችን በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ ቀደም ብሎ የነበረ ቢሆንም ስራው ባለቤት ተሰጥቶት በተፈለገው መጠን ሲሰራ አልቆየም፡፡ በዚህም ምክንያት የኢኮኖሚ ወንጀል ፈፃሚዎች ይህን የግንዛቤ፣የህግና የአሰራር ክፍተት በመጠቀም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ከፍተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ሀብት በየጊዜው እየዘረፉ ተከስሰው ጥፋተኛ ከተባሉም እስራት ተወስኖባቸው በወንጀሉ ምክንያት የተወሰደው ንብረት ሳይመለስ ሲቀር ማየት የተለመደ ነው፡፡ በጥናቱም መሰረት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብትን ለማስመለስ በአማራ ክልል የተለየ ህግ የሌለና የሀገሪቱን ሕጎች የሚጠቀም ሲሆን እነዚህ የሀገራችን ህጎችም በተበታተነ መልኩ ቀደም ሲል ጀምሮ በህግ ደረጃ ተደንግገው የሚገኙ ቢሆንም በቂና ራሱን የቻለ ወጥ ህግ ካለመኖሩም በላይ ከነክፍተቱም ቢሆን ያሉት ህጎች በተገቢው ሁኔታ በተግባር ላይ ሲውሉ አይስተዋሉም፤እንዲሁም የተደራጀ ተቋማዊ አወቃቀርና ግንዛቤ የሌለ በመሆኑ በክልሉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብትን ማስመለስ መሰራት ባለበት መጠን ልክ ስራው እንደማይፈፀም ያሳዩ ስለሆነ ራሱን የቻለ የተጠቃለለ ህግና ጠንካራ ተቋም ተዘርግቶ ልዩ ግንዛቤ በመፍጠር መሰራት ያለበት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡


**ቁልፍ-ቃላት**፡- በወንጀል የተገኘ ሀብት፣ የወንጀል ፍሬ፣ ሀብት ማስመለስ፣ ማስወረስ፡፡

# 1. መግቢያ

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት የማስመለስ ተግባራትን በሚመለከት በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትህ ስርዓት አስተዳደር ውስጥ ስራውን ለመስራት በ2011 ዓ.ም በፌደራል ፍትህ ሚኒስተር ስር ሆኖ ራሱን የቻለ የስራ ክፍል ተዋቅሮ በተሻለ ስራ ላይ ያለ ሲሆን በአማራ ክልል ደግሞ በ2015 ዓ.ም በክልሉ ፍትህ ቢሮ በተደረገ ጥናትና የአደረጃጀት ለውጥ መሰረት አዲስ መዋቅር በመዘርጋት ስራውን በይፋ ጀምሮ እያከናወነ የሚገኝ የስራ ክፍል ነው፡፡[1] ከዚህ በፊት በቂ ግንዛቤና ኃላፊነት ተወስዶ በውጤታማነት ሲሰራ ባይቆይም ከሌሎች የስራ ክፍሎች ጋር ተደርቦ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሲከናወን ቆይቷል፡፡

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብትን ማስመለስ የስራ ክፍል በክልሉ ራሱን ችሎ እንዲቋቋም የተደረገበት ዋናው ዓላማም ከጊዜ ወደ ጊዜ የኢኮኖሚ ወንጀሎች እየተበራከቱ መምጣቱ፣መደበኛው የእስራትና የገንዘብ መቀጮ በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ፣በወንጀል የተገኘ ሀብት የማስመለስ ስራ በልዩ ትኩረት በመስራት ህገ መንግስታዊ የንብረት ባለቤትነት መብትን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፣ጥፋተኞቹን እንዲሁም ሌላውን የህብረተሰብ ክፍል ለማስተማር ማለትም ለኢኮኖሚ ጥቅም ተብለው የሚፈፀሙ ወንጀሎች ከወንጀል ቅጣቱ በተጨማሪ በወንጀሉ ምክንያት የተገኘውን ሀብት ራሱን ችሎ በመከታተል ወደ ህጋዊ ባለቤቱ በማስመለስ ወንጀል ፈፃሚዎችን ህጋዊ ያልሆነውን ጥቅም በማሳጣት ወደ ፊት መሰል ወንጀሎችን እንዳይፈፅሙ ለማድረግ ሲሆን እነዚህ ስራዎች ከሌሎች የወንጀል የሥራ ክፍሎች ጋር ተደርቦ ሲሰራ የቆዩ ቢሆንም በተፈለገው ልክ ውጤት ባለማምጣቱ ነው፡፡[2]

የጹሑፉ መነሻ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስ ከተነሳበት ዓላማ እና ግብ አንፃር ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ባለመሆኑና ወንጀል ፈፃሚዎች ወንጀል በመፈጸም የሚያገኙት ገንዘብ ካልተወሰደባቸው እነርሱ ቢታሰሩም ለቤተሰቦቻቸው ወይም የተወሰነ ጊዜ ታስረን ስንወጣ ገንዘቡን እንጠቀማለን የሚል ሀሳብ በማዳበር የኢኮኖሚ ወንጀሎች በዚህ ዘመን በክልሉ እየተበራከቱ በመምጣቱ ነው፡፡ በክልሉ ያለው አሰራርም በወንጀል የተገኘውን ሀብት ማስመለስ ላይ ሳይሆን ወንጀል ፈፃሚዎችን በእስራት ማስቀጣት ላይ ያተኮረ በመሆኑና

[1] አቶ ልየው ፀሐይ፣ በአብክመ ፍትህ ቢሮ በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ (ባህር ዳር፣ 1/11/2015 ዓ.ም) ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፡፡

[2] አቶ ግዛቸው መስፍን፣ በአብክመ ፍትህ ቢሮ የልዩ ልዩ ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር፣ በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ የስራ ክፍል አጥኚ የነበር፣ (ባህርዳር 7/1/2016 ዓ.ም) ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፡፡

*ይህ ደግሞ የክልሉን የኢኮኖሚ ዕድገት ከመግታቱም በላይ ማህበራዊ ቀውስ እየፈጠረ መጥቷል፡፡*

*ስለሆነም ይህ ትክክል ያልሆነ አስተሳሰብና በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብትን በተገቢው ሁኔታ ማስመለስ አለመቻል ምክንያቶች በዚህ ጥናት ምላሽ ያገኙ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በዚህም አግባብ ግኝቶችን መሰረት በማድረግ የስራው ባለቤቶች የሥራ ድርሻ፣ምን ዓይነት ህጎችንና አሰራሮችን በመጠቀም በወንጀል የተገኘ ሀብትን ማስመለስ እንደሚቻል ከማሳየትም በተጨማሪ መንግስት በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ላይ ያሉ ሕጎችንና አደረጃጀቶችን በተገቢው አጠናክሮ ውጤታማ ሊሆን የሚችልበትን የመፍትሄ መንገዶች የሚያመለክት ነው፡፡*

*ጥናቱ አይነታዊ የጥናት ዘዴን ተከትሎ የተከናወነ ሲሆን የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም ቃለ-መጠይቆች፣ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች፣ ምልከታዎች፣ ሪፖርቶች፣ ከርዕሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የተለያዩ ጹሑፎች እና ሌሎችም ህጎች በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡*

## 2. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ምንነት

*በኢትዮጵያ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር* 780/2005 *አንቀፅ* 2/3/ *እና* /4/ *መሰረት የወንጀል ፍሬ/proceeds of crime/ማለት በቀጥታም ሆነ በተዛዋሪ መንገድ ከአመንጭ ወንጀል/predicate offence/ ከማንኛውም የወንጀል ፍሬ ምንጭ ከሆነ የተገኘ ማንኛውም ገንዘብ ወይም ንብረት ማለት ነው ሲል አመንጭ ወንጀልን ደግሞ ማንኛውም ለወንጀል ፍሬ ምንጭ የሆነና ቢያንስ አንድ ዓመት ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል ነው በማለት ይተረጉማል፡፡*[3]

*በዚህ ትርጉም መሰረት ከአንድ ዓመት በታች በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ በሚያስቀጡ ወንጀሎች አማካኝነት በተፈፀመ የወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት አንደ ወንጀል ፍሬ ስለማይቆጠር በፍትሐብሔር ካልሆነ ከወንጀሉ ድርጊት ጋር አብሮ የማይታይ መሆኑን የሚያስገነዝብ ስለሆነ የተከተለው የህግ ስርዓት ሙሉ የማያደርገውና ከሌሎች ዓለማቀፍ ህጎች የተለየ ነው፡፡*

[3] *የኢፌዲሪ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ፣*2005 *ዓ.ም፣ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር* 780/2005፣19*ኛ ዓመት ቁጥር* 25፣ *አንቀፅ* 2(3,4)፣ *አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፡፡*

ኢትዮጵያ ያፀደቀችው United Nation's Convention Against Transnational Organaized Crime የወንጀል ፍሬን እና አመንጭ ወንጀልን ሲተረጉም 'Proceeds of crime shall mean any property derived from or obtained, directly or indirectly, through the commission of an offence and Predicate offence shall mean any offence as a result of which proceeds have been generated that may become the subject of an offence" በማለት ትርጉም ሰጥቷቸዋል፡፡[4] ይህ ትርጉም ከኢትዮጵያው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 780/2005 አንቀፅ 2/3/እና/4/ የሚለየው አመንጭ ወንጀልን ሲገልፅ any offence as a result of which proceeds have been generated that may become the subject of an offence በማለት ሲሆን ለበወንጀል የተገኘ ሀብት ሰፋ ያለ የተሻለ ትርጉም በመስጠት በማንኛውም ዓይነት ወንጀል ለወንጀል ፍሬ ምንጭ የሆነ በቅጣት መጠን ሳይወሰን በተፈፀመ የወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ሀብት መሆኑን ይገልፃል፡፡

ከነዚህ ትርጉሞች መረዳት የሚቻለው በወንጀል የተገኘ ሀብት ማለት በህግ ወንጀል ተብሎ የተደነገገ ድርጊትን በመጣስ ወንጀል ፈፅሞ የተገኘ የሌላ ሰው ሀብት ማለት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ምንነትን በሚመለከት በሌሎች የሀገራችን ሕጎች ወጥ የሆነ ትርጉም ያልተሰጠ ቢሆንም ሕጎቹን እንደየ ባህሪያቸው የሚያስማመው የጋራ ሀሳብ ወንጀል ፈፃሚዎች በተለይም ለገንዘብ ጥቅም በማሰብ ወንጀል ፈፅመው በተለያየ መልኩ ያገኙት የወንጀል ፍሬ ሀብት መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ለዚህም ምሳሌ በሰዉ መነገድና ሰዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል፣ የሙስና ወንጀል ህጎች፣ የጉምሩክ ህጎች፣ የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር ህግ፣ መደበኛው የወንጀል ህግ እና የመሳሰሉት የኢኮኖሚ ጥቅም ለማግኘት ተብሎ የሚፈፀሙ ወንጀሎች በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ይህንኑ ይገልፃሉ፡፡

## 3. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስወረስ ምንነት

በ1996 ዓ.ም ተደንግጎ በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 98[5] እና ተከታዎቹ እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 2/5/(አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 29ን

[4] *United Nations Convention Against Transnational Organized Crime, 2004, article 2/e, h) respectively, United Nations, New York*

[5] *የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ*፣1996 *ዓ.ም*፣*ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ አዋጅ ቁጥር 414/1996፣አንቀፅ 98፣አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፡፡

እንዳሻሻለው) የወንጀል ፍሬ የሆነውን ሀብት ወይም ንብረት ከወንጀል ክሱ ጋር የውርስ አቤቱታ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ወደ ባለቤቱ ማስመለስ እንደሚቻል በግልፅ በመደንገግ[6] ያስቀመጠ በመሆኑ በወንጀል የተገኘ ሀብትን ማስመለስ ማለት በወንጀል ድርጊት ምክንያት የተገኘን የወንጀል ፍሬ ወይም ተመጣጣኝ የወንጀል ፈፃሚው ማንኛውንም ገንዘብ ወይም ንብረት ወደ ትክክለኛ ባለቤቱ እንዲመለስ ማድረግ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ መውረስን African Union Convention on Preventing and Combating Corruption "confiscation means any penalty or measure resulting in a final deprivation of property, proceeds or instrumentalities ordered by a court of law following proceedings in relation to a criminal offence or offences connected with or related to corruption" በማለት በግልፅ ትርጉም ሰጥቶት ይገኛል።[7]

በወንጀል የተገኘን ሀብት ማስመለስ/*stolen asset recovery/* በተለያዩ ህጎች አንድ ወጥ ትርጉም ባይሰጠውም ተቀራራቢ በሆነ ሁኔታ ከዚህ በላይም እንደተገለፀው በወንጀል ድርጊት ምክንያት የተገኘን ሀብት በፍርድ ቤት ወይም ሌላ ስልጣን በተሰጠው አካል ትዕዛዝ ወደ ትክክለኛ ባለቤቱ እንዲመለስ የሚወረስበት/*confiscate/*ሂደት መሆኑን በመደንገግ ያስቀምጣሉ። በወንጀል ድርጊት የተገኘው ሀብት ማስወረስ በፍርድ ቤት የወንጀል ፍሬ/ተመጣጣኝ ሀብት/ መሆኑን ማስወሰን ሲሆን ማስመለስ ግን እስከ መጨረሻው አፈፃፀምን እና ሀብቱን መረከብን ያጠቃልላል።

## 4. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት የሚመለስበት የህግ ማዕቀፍ

በወንጀል ድርጊት አማካኝነት የተገኘን ሀብት ወደ ትክክለኛ ባለቤቱ ለማስመለስ የሚመለከታቸውን ተቋማት በተለያዬ መልኩ በማጠናከር፣ተቀናጅተውና ተባብረው በመስራት ሊወረሱ የሚችሉ ሀብቶችን በመለየት ህግ በሚፈቅደው ስነስርዓት ማስመለስ ይቻላል።

የኢኮኖሚ ወንጀሎች በዋነኛነት የሚፈጸሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በመሆኑ ወንጀሉን ለመፈጸም የሚያነሳሳውና የሚያደፋፍረው ከድርጊቱ በስተጀርባ የሚገኘው ጥቅም ሲሆን ወንጀል ፈፃሚው በእስራት ቢቀጣም በወንጀሉ ያገኘው ጥቅም ከፍተኛ እስከሆነ ድረስ መታሰሩ ብቻ ከወንጀል ድርጊቱ እንዲታቀብ እንዲሁም ሌሎች ሰዎች መታሰሩን አይተው

---

[6] *የኢፌዲሪ የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የስነ ስርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ*፣2007 ዓ.ም፣ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 882/2007፣21ኛ ዓመት ቁጥር 37፣አንቀፅ 2/5/፣አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ።
[7] *African Union Convention on Preventing and Combating Corruption*, Article 1, 2003, Maputo.

ድርጊቱን ከመፈጸም እንዲታቀቡ ስለማያደርጋቸው የወንጀል ፍሬውን የሚመለከት ጠንካራ የህግ ስርዓት ያስፈልጋል፡፡[8]

በኢኮኖሚ ወንጀል የተገኘ ጥቅም ሊወረስ የሚያስችል ተገቢ የህግ ስርዓት ካለ ግን የኢኮኖሚ ወንጀል መፈፀሙ ከተረጋገጠና በወንጀሉ ድርጊት ምክንያት የተገኘው ሀብት በፍርድ ቤት በማስወረስ የሚመለስ ከሆነ ወንጀለኞች ከመቀጣት በስተቀር የሚያተርፉት ነገር ስለማይኖር ሰዎች የኢኮኖሚ ወንጀል እንዳይፈጽሙ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡[9] ስለሆነም ሀብት ለማግኘት የሚፈፀሙ ወንጀሎች ጥቅምና ጉዳቱን በማመዛዘን/cost benefit analysis/ ታሳቢ ተደርጎ የሚፈፀም የወንጀል ድርጊት ስለሆነ ለወንጀል መፈፀምና ለሀገር ኢኮኖሚ ውድቀት ዋነኛ ምክንያት በመሆኑ በጥንቃቄ መታየት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

## 4.1. በወንጀል ድርጊት ምክንያት ሊወረሱ የሚችሉ ሀብቶች

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ተብሎ በወንጀል ፈፃሚዎች*/perperators/* የተወሰዱ ንብረቶች ሲረጋገጡ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ሀብት የማስመለሱ ሁኔታ ከሚወረሰው የንብረት ዓይነት አኳያ የወንጀሉን ፍሬ መውረስ፣ተመጣጣኝ የወንጀል ፍሬና ለወንጀል መፈጸሚያ የዋለ ንብረት ስልጣን ባለው አካል ሊወረስ ይችላል፡፡[10]

### 4.1.1. የወንጀል ፍሬን መውረስ

የወንጀል ፍሬን መውረስ ማለት ወንጀል ፈፃሚው የወንጀል ድርጊት ፈፅሞ በቀጥታ ያገኘውን ገንዘብ/ንብረት መውረስ ሲሆን በቀጥታ የተገኘውን የወንጀል ፍሬ በመጠቀም የተገኘ ሌላ ገቢ፣ተቀላቅሎ ወይም ተለውጦ የተገኘ ፍሬንም ያካትታል፡፡[11]

ይህ ማለት ከወንጀል ፍሬው በተጨማሪ በወንጀል ፍሬው አማካኝነት በማንኛውም መንገድ የተገኘ እንደ ወለድ፣የኪራይ ገቢ፣ትርፍ እና የመሳሰሉት የገቢ ጥቅሞች እንደ ወንጀል ፍሬ ተቆጥሮ ይወረሳሉ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ወንጀል ፈፃሚ ከባንክ ብር ዘርፎ ቤት በመግዛት በቤቱ ኪራይ እየተጠቀመ መሆኑ ቢረጋገጥ የተገኘው ገቢ ከዋናው የወንጀል ፍሬ ቢበልጥም ከነወንጀል ፍሬው ከቤቱ የሚገኘው የኪራይ ገቢ በቀጥታ ከወንጀል ድርጊቱ የተገኙ

---

[8] የፌደራል ፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል መፅሐፍ ፣*የሙስና ሀጎች*፣ (አዲስ አበባ፣2004)፣ *ገፅ* 29

[9] *ዝኒ ከማሁ*፡፡

[10] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የተመዘበረ ሃብት መመርመርና ማስመለስ ግብረ ሃይል፣*የተመዘበረ ንብረት መውረስና በመወረስ ሂደት ላይ የሚገኝ ንብረትን ስለማስተዳደር በኢትዮጵያ፡* የህግ ማዕቀፍና ተቋማዊ አወቃቀርን በተመለከተ የተደረገ ጥናት፣ አዲስ አበባ (2011)፣*ገፅ* 7፡፡

[11] *ዝኒ ከማሁ ገፅ* 8፡፡

የወንጀል ፍሬ ገቢዎች በመሆናቸው ተወርሰው እንደአግባቡ የወንጀል ድርጊቱ ለተፈፀመበት ባንክ ሀብቱ ይመለሳል ማለት ነው። ይህን በማጠናከር የወ/መ/ህ/ቁ 98/2/ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት የወንጀል ድርጊት ወንጀለኛው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ያገኘው ንብረት ይወረሳል በማለት በግልፅ ተደንግጎ ይገኛል።[12]

### 4.1.2. ተመጣጣኝ የወንጀል ፍሬን መውረስ

የወንጀል ፍሬን ተመጣጣኝ መጠን መውረስ ማለት ወንጀል ፈፃሚው ወንጀል ፈጽሞ ያገኘውን ቀጥተኛ የወንጀል ፍሬ ገንዘብ/ንብረት በማሸሸቱ ወይም በማጥፋቱ ማግኘት ባልተቻለ ጊዜ ከወንጀሉ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለውን ተመጣጣኝ የሆነ የወንጀል ፈፃሚውን ንብረት በመውረስ የሶስተኛ ወገን የንብረት መብት እንዲጠበቅ የሚደረግበት የመውረስ አይነት ነው።[13]

ተመጣጣኝ የወንጀል ፍሬን መውረስ ከወንጀል ፍሬ መውረስ የሚለየው በቀጥታ በወንጀሉ ድርጊት የተገኘው ሀብት በማንኛውም ሁኔታ መገኘት በማይችልበት ጊዜ የወንጀል ፍሬውን በተመጣጣኝነት ሊተካ የሚችል የወንጀል ፈፃሚው ህጋዊ ንብረት የሚወረስበት ስርዓት መሆኑ ነው። ለምሳሌ የኢኮኖሚ ወንጀል ፈፅሞ በፈፀመው ወንጀል አማካኝነት ያገኘውን ገንዘብ ቢያጠፈውና ማግኘት ባይቻል የወንጀለኛው ህጋዊ ቤት ቢኖረው በወንጀሉ ምክንያት ላገኘው ንብረት ማካካሻ በማሳገድና የውርስ አቤቱታ በማቅረብ በወንጀል በተገኘው ሀብት መጠን ልክ ሊወረስበት የሚችል መሆኑን ከላይ ከተገለፁት የህግ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል።

### 4.1.3. ለወንጀል መፈፀሚያ የዋለ ንብረትን መውረስ

ይህ የመውረስ ዓይነት ወንጀል ፈፃሚው ወንጀሉን በመፈጸም ሂደት ውስጥ የተጠቀመበትን ንብረት/መሳሪያ በወንጀል የቆሸሸ በመሆኑ የሚወረስበት ሂደት ነው።[14] በዚህ የመውረስ ሂደት ወንጀል ፈፃሚው ያገኘው ሀብት ባይኖርም የወንጀል ድርጊቱን ለመፈፀም የተጠቀመውን መሳሪያ ሌላ ወንጀል እንዳይፈፅምበትና ንብረቱንም በመውረስ መቅጣትና ማስተማር ስለሚያስፈልግ በቀጥታ የሚወረስበት ሁኔታ ነው።

## 4.2. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት የሚመለስበት የህግ ስርዓት

ከሚወረሰው በወንጀል የተገኘ ንብረት አንፃር ከላይ ባየነው ሁኔታ የሚተገበር ሲሆን የማስወረሱ ህጋዊ ስነ ስርዓት ደግሞ በጥፋተኝነት ላይ የተመሰረተ መውረስ፣በጥፋተኝነት

---

[12] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 5 እንደተጠቀሰው።

[13] *ዝኒ ከማሁ*።

[14] *ዝኒ ከማሁ*።

ላይ ያልተመሰረተ መውረስ፣ በፍትሐብሔር መውረስ እና በአስተዳደራዊ መውረስ በሚሉ አራት የህግ ስነ ስርዓቶች ሊከናወን ይችላል፡፡[15]

### 4.2.1. በጥፋተኝነት ላይ የተመሰረተ መውረስ

በዚህ በወንጀል የተገኘ ንብረት የመውረስ ዓይነት የወንጀል ፍሬ የሆነውን ሀብት/ተመጣጣኙን/ ለመውረስ በወንጀሉ የተከሰሰው ሰው በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡[16]

በወንጀል የተጠረጠረው ግለሰብ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ከተባለ በዚያው የወንጀል መዝገብ ላይ የወንጀሉን ጉዳይ ላየው ችሎት አስቀድሞ ከክሱ ጋር ካልቀረበ የውርስ አቤቱታ በማቅረብ በዚሁ የወንጀል ድርጊት ምክንያት ያገኘው የወንጀል ፍሬ፣ተቀላቅሎ/ተለውጦ የተገኘው ገንዘብ ወይም ንብረት እንዲሁም ከወንጀሉ ፍሬ የተገኘውን ማንኛውንም ገቢና ጥቅም እንዲወረስ የሚወሰንበት ሲሆን የወንጀል ፍሬው በማይገኝበት ጊዜ ካገኘው የወንጀል ፍሬና በወንጀል ፍሬው ሊገኝ ይችል ከነበረው ገቢ ጋር ተመጣጣኝ የሆነው የወንጀል ፈፃሚው ህጋዊ ንብረት የሚወረስበትና ጉዳት ለደረሰበት ህጋዊ ባለቤቱ የሚመለስበት የህግ ስርዓት ነው፡፡[17]

ስለዚህ በዚህ መንገድ የሚካሄድ በወንጀል የተገኘ ሀብት የማስመለስ የህግ ስርዓት በማንኛውም ሁኔታ ወንጀል ፈፃሚው በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ መባልና የንብረት የውርስ አቤቱታውም በዚያው የወንጀል መዝገብና ችሎት በመቅረብ መወረስ የሚቻልበት የህግ ስርዓት ነው፡፡

### 4.2.2. በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ መውረስ

ይህ የመውረስ ሂደት መሰረት የሚያደርገው በወንጀል የተከሰሰው ወይም የተጠረጠረው ሰው በፍርድ ውሳኔ ጥፋተኛ መባልን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ራሱን በቻለ አካሄድ የሚከናወን ሆኖ የመውረስ ክስ የሚቀርበው በወንጀሉ ፍሬ ላይ መሰረት በማድረግ ሲሆን የተጠረጠረው ግለሰብ በወንጀሉ ጥፋተኛ ባይባልም ንብረቱ የወንጀል ፍሬ ነው ተብሎ በሚታመንበት ጊዜ እና በተጠርጣሪው ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ በተለያየ መልኩ ማስጠት ሳይቻል ሲቀር ማለትም ተከሳሽ ቢሞት፣ባይታወቅ፣ ቢጠፋ፣በወንጀል ያለመከሰስ መብት ያለው ቢሆን እና የመሳሰሉት

---

15 *በአብክመ ፍትህ ቢሮ በወንጀል የተገኘ ንብረት ምርመራና ማስመለስ የአሰራር ማንዋል*፣ ባህርዳር(2015)፣ገፅ 22-28፡፡

16 በግርጌ ማስታሻ ቁጥር 8 እንደተጠቀሰው ገፅ 9፡፡

17 *ዝኒ ከማሁ*፡፡

በሚያጋጥሙ ጊዜ የሚወሰድ አማራጭ በወንጀል የተገኘን ሀብት ለማስመለስ የሚጠቅም ህጋዊ መንገድ ነው፡፡[18]

በኢትዮጵያ ደረጃ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 780/2005 አንቀፅ 31/3/[19] እና በሰው የመነገድና ሰውን በህገ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመክላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ዓ.ም አንቀፅ 21/1/ለ/ ብቻ ይህን አይነት ህጋዊ የመውረስ ዘዴ ይፈቅዳሉ፡፡[20] ይሁን እንጅ በኢትዮጵያ ብዙ ህጎች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብትን መወረስ የሚያስፈልግ መሆኑን የሚያስቀምጡ ቢሆንም በዋናነት በተለያዩ ምክንያት ወንጀለኞች በሚያመልጡበት ጊዜ በወንጀል የተገኘ ሀብትን ለማስመለስ የሚጠቅመውን በጥፋተኝነት ላይ ያልተመሰረተ የመውረስን የህግ ስርዓት ያካተቱ አይደሉም፡፡

### 4.2.3. በፍትሐብሔር መውረስ

የወንጀል ድርጊት ፈፃሚው በተለያዩ ምክንያት ክሱ እንዲቋረጥለት ቢደረግ ወይም በማንኛውም መንገድ የጥፋተኝነት ውሳኔ ባይሰጥ በወንጀሉ ድርጊት ምክንያት የተገኘውን የወንጀል ፍሬ ወይም በወንጀሉ ምክንያት ከደረሰው ጉዳት/ጥቅም/ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ ለማካካስ በፍትሐብሔር ክስ መስርቶ የንብረት መብትን ማስጠበቅ እንደሚቻል ይገልፃል፡፡[21]

ይህ የማስወረስ ህጋዊ መንገድ መደበኛ የሆነውን የፍትሐብሔር ክስ የሚመለከት ሲሆን የህግ ስርዓቱም እንደማንኛውም ፍትሐብሔራዊ ክስ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህጉን ተከትሎ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሰው የደረሰበት የንብረት ጉዳት እንዲመለስለት ወይም እንዲካስለት የሚቀርብ የማስወረስ የህግ  ስነስርዓት ዘዴ ነው፡፡

ለዚህም በቂ ማሳያ የሚሆነው የኢፌዲሪ የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የስነ ስርዓትና የማስረጃ ህግ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ 882/2007 አንቀፅ 2/7/ በወንጀል ፈፃሚው ላይ የተጀመረው የሙስና ወንጀል ምርመራ/ክስ/ ቢቋረጥ ወይም በማንኛውም መንገድ የጥፋተኝነት ውሳኔ ባይሰጥ በወንጀሉ የተገኘውን የወንጀል ፍሬ /አላግባብ ከተገኘው ጥቅም/ ጋር ተመጣጣኝ

---

[18] *ዝኒ ከማሁ*፡፡

[19] በግርጌ ማስታወሻ 1 እንደተጠቀሰው አንቀፅ 31/3/፡፡

[20] *በሰው የመነገድና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከል ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ*፣2012 ዓ.ም፣ *ፌድራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ አዋጅ ቁጥር 1178/2012 ዓ.ም፣26ኛ ዓመት ቁጥር 31፣አንቀፅ 21/1/ለ/፣አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፡፡

[21] በግርጌ ማስታወሻ 8 እንደተጠቀሰው *ገፅ* 25፡፡

የሆነ ሀብት ለመካስ አግባብ ያለው አካል  በፍትሐብሔር ክስ ሊመሰርት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡[22]

እንዲሁም የኢትዮጵያ የወንጀልኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ አንቀፅ 154-559 ድረስ ያሉት ድንጋጌዎች በግልፅ በወንጀል ድርጊት የደረሰን ጉዳት ከወንጀሉ ክስ ጋር ወይም ለብቻው የፍትሐብሔር ክስ በመመስረት ማስመለስ የሚቻል መሆኑን የሚያሣይ ሲሆን[23] የተሻሻለው የኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ልዩ የስነስርዓትና ማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 32 በሙስና ወንጀል የተገኘ ንብረት አግባብ ያለው አካል ወይም ጉዳት የደረሰበት ሰው ከሶ ማስመለስ እንደሚችል ለማመላከት ሲገልፅ የአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ወይም የሌላ ግለሰብን ንብረት ወይም ገንዘብ ከሆነ ይኸው የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ወይም ግለሰብ በሙስና የተገኘውን ንብረት ወይም ገንዘብ እንዲመለስ በፍትሐብሔር ክስ እንዲመሰርት አግባብ ያለው አካል ሊያሳውቅ ይችላል በማለት በወንጀል የተገኘን ሀብት በፍትሐብሔር ክስ በመመስረት ማስመለስ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡[24]

### 4.2.4. በአስተዳደራዊ ስርዐት መውረስ

ይህ የመውረስ ዘዴ በፍርድ ቤት ክርክር የሚደረግበት ሳይሆን ህግ በሚፈቅደው አግባብ ስልጣን በተሰጠው አካል በአስተዳደራዊ መንገድ የሚወረስ ሲሆን ወደ ህዝብና መንግስት ንብረትነት/ሀብትነት/ የሚመለስበት መንገድ ነው፡፡[25]

ለምሳሌ በኢትዮጵያ ደረጃ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀፅ 147 በኮንትሮባንድ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን በጉምሩክ ባለስልጣን በአስተዳደራዊ መንገድ ስለሚወረሱበት ሁኔታ በግለፅ ይደነግጋል[26] ማለትም በኮንትሮባንድ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡና የሚወጡ ዕቀዎችና ማጓጓዣዎች በፍ/ቤት ክስ ቀርቦ ሳይሆን በቀጥታ በባለስልጣኑ አስተዳደራዊ ውሳኔ እንዲወረሱ የሚደረጉ ናቸው ማለት ነው፡፡

እንዲሁም የኢትዮጵያ የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1177/2012 አንቀፅ 21/5/ እና /6/ የጦር መሳሪያ ቁጥጥር ባለስልጣኑ በቀጥታ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ

---

[22] በግርጌ ማስታወሻ 4 እንደተጠቀሰው አንቀፅ 2/7/፡፡

[23] *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት አዋጅ*፣ 1954 ዓ.ም፣ *ነጋሪት ጋዜጣ*፣ አዋጅ ቁጥር 1/1954 ዓ.ም፣ 31ኛ ዓመት ቁጥር1፣አንቀፅ 154-159፣(አዲስ አበባ፣ኢትየጵያ)

[24] *የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ ህግ አዋጅ*፣1997 ዓ.ም፣ *ፌድራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ አዋጅ ቁጥር 434/1997 ዓ.ም፣ 11ኛ ዓመት ቁጥር 19፣አንቀፅ 32፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፡፡

[25] በግርጌ ማስታወሻ 12 እንደተጠቀሰው አንቀፅ 39

[26] *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የጉምሩክ አዋጅ*፣2006 ዓ.ም፣ *የፌድራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣አዋጅ ቁጥር 859/2006፣ 20ኛ ዓመት ቀጥር 82፣አንቀፅ 147፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፡፡

ለሰላምና ደህንነት ስጋት ነው ያለውንና ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ሆኖ ያገኘውን መውረስ እንደሚችል ስልጣን ሰጥቶት ይገኛል፡፡[27]

## 5. የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ

በእኛ በሀገር ደረጃም ሆነ በክልሎች በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስ አስፈላጊነቱና ልምዱ የዳበረ ባለመሆኖ ሌሎች ሀገራት የተከተሉትን የህግ ስርዓትና ያመጣውን ውጤት በማየት የሚጠቅመውን መውሰድ ተገቢ በመሆኑ ተሞክሮ የሚወሰድባቸው በርከት ያሉ ሀገራት ያሉ ቢሆንም ከአፍሪካና ከአውሮፓ የተሻለ ልምድ ያላቸውን ሁለት ሀገሮችን ለአብነት ለማየት ተችሏል፡፡

### 5.1. ደቡብ አፍሪካ

የደቡብ አፍሪካ መንግስት ከአፓርታይድ ቅኝ አገዛዝ መላቀቅ በኂላ የተደራጀ የወንጀል ተግባርን ለመቆጣጠር የሚያግዙ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ያከናወነ ሲሆን እነዚህን ውጤታማ ስራዎች የፈፀሙት በዘርፉ ልዩ የሙያ ብቃት እና ክህሎት ያለው የህግ አስከባሪ ባለሙያ በማፍራትና በተደራጀ ወንጀል የኢኮኖሚ ጥቅምን መሰረት ያደረገ ወንጀል ላይ ሀብትን በመከታተል */following the money/*እና በወንጀል ተግባር የተገኘ ሃብትን በማስመለስ*/confiscation on proceeds of crime/*በተመለከተ አዲስ ዘዴ በመተግበር ነው፡፡[28]

በዚህም መሰረት ደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያውን በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሃብት ስለመውረስ የሚደነግግ ህግ እ.አ.አ በ1996 አውጥታ የነበረ ቢሆንም በማሻሻል በ1998 ዓ.ም የተደራጀ የወንጀል ተግባርን ለመከላከል */Prevention of Organized Criminal Act/* አውጥታለች፡፡[29]

መጀመሪያ አካባቢ ስራው ውጤታማ አልነበረም ለዚህም ምክንያቱ በህገ-ወጥ ድርጊት ሃብት የሚያካብቱ ሰዎች ሳይኖሩ ቀርተው ወይም አመንጪውን ወንጀል */predicate offence/* በተመለከተ በዐቃቤ ህግ ክስ ሳይመሰረትባቸው ቀርቶ ሳይሆን ጉዳዩን በሚፈለገው ደረጃ ለመቆጣጠር እና ለማስፈጸም የሚያበቃ የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እና ተቋማዊ አደረጃጀት ያልነበረ በመሆኑ ይህን የተገነዘበው የሀገሪቱ የዐቃቤ ህግ መስሪያ ቤትም ለህግ አውጭው

---

[27] *የጦር መሳሪያ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ* ፣2012 ዓ.ም፣ የፌድራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 1177/2012፣ 26ኛ ዓመት ቁጥር 28፣አንቀፅ 21/5፣6/፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፡፡
[28] በግርጌ ማስታወሻ 8 እንደተጠቀሰው ገፅ 14፡፡
[29] *ዝኒ ከማሁ*፡፡

ክፍል ስለ መውረስ ዝርዝር ችግሮችን ሊፈታ የሚችል ህግ እንደሚያስፈልግ ባቀረበው አስተያየት መሰረት ተቀባይነት አግኝቶ እ.አ.አ በ1998 ህጉ ተሻሽሎ ሊወጣ ችሏል፡፡[30]

የህጉ መውጣት ብቻ ሳይሆን በህገ ወጥ ተግባር የተገኘ ሃብትን ማስመለስ ከሚፈልገው ልዩ ትኩረት አንጻር ተቋማዊ አወቃቀሩም በዚያው ልክ ሊስተካከል እንደሚገባና ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ግን ህጉም እንዲያሳካ የታለመለትን ግብ ሊያሳካ እንደማይችል ስለታመነበት የተደራጀ የወንጀል ተግባርን ለመከላከል የወጣውን ህግ በተሻለ ጥንካሬ ለማስፈጸም የንብረት ማስወረስ ስራ ብቻ የሚሰራ ክፍል */Asset Forfeiture Unit/* እ.አ.አ 1999 በዐቃቤ ህግ መስሪያ ቤት ስር ተደራጅቶ ውጤታማ በሆነ መልኩ እየሰራ ይገኛል፡፡[31]

## 5.2. እንግሊዝ

የንብረት ማስመለስና መውረስ ህግ በዩናይትድ ኪንግደም ለመጀመሪያ ጊዜ በተግባር መዋል የጀመረው የአደንዛዥ እፆች ዝውውር መከላከል ህግ ከወጣበት*/Drug Trafficking Offence Act/* እ.ኤ.አ ከ1986 ጀምሮ ሲሆን ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የተለያዩ ህጎችን በማውጣትና ያሉትንም በማሻሻል ዛሬ ላይ የተመዘበረ ሃብትን በማስመለስ በኩል ለሌሎች ሀገሮች ምሳሌ ሊሆን የሚችል የህግ ስርዓት ለመዘርጋት የቻለች ሀገር ናት፡፡[32]

በ1988 እ.ኤ.አ የወጣው የወንጀል ፍትህ ህግ*/Criminal Justice Act/*እንዲሁም የወንጀል ፍሬ ህግ*/Proceeds of Crime Act*-2002/የሚወረሰው የወንጀል ፍሬ ከእፅ ከሚገኝ ገንዘብ ባሻገር በሌሎች የገንዘብ ጥቅም በሚያስገኙ ወንጀሎች ላይም ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረጉ በወንጀል የተገኘ ሀብትን ከማስመለሱም በተጨማሪ የተደራጁ ወንጀሎችን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ ሚና የነበረው ነው፡፡[33]

በወንጀል የተገኘ ሃብት ማስመለስን በተመለከተ በአሁኑ ሰዓት በእንግሊዝ ትኩረት የተሰጠውና በተግባር ላይ ያለው ህግ የወንጀል ፍሬ ህግ*/Proceeds of Crime Act-POCA 2002 as amended by the 2017 Criminal Finance Act/* ሲሆን የተለያዩ ተቋማት ከምርመራ ጀምሮ ንብረት እስከ ማስመለስና ማስተዳደር ድረስ በሰፊው የሚሳተፉበት አስፈላጊ የሀገሪቱ የህግ ስርዓት ነው፡፡[34]

---

30 *ዝኒ ከማሁ*፡፡
31 *ዝኒ ከማሁ ገፅ* 15፡፡
32 *ዝኒ ከማሁ ገፅ* 23-24፡፡
33 *ዝኒ ከማሁ ገጽ* 24፡፡
34 *ዝኒ ከማሁ*፡፡

ከሁለቱም በጉዳዩ የዳበረ ልምድ ካላቸው ሀገራት መረዳት እንደቻልነው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስ የሚቻለው ጠንካራ ተቋምና የህግ ስርዓት የሚያስፈልገው መሆኑንና የተለየ ትኩረት የሚሻ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

## 6. በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስ በኢትዮጵያ

በማንኛውም ወንጀል ለደረሰ ጉዳት/ለተገኘ ጥቅም/ በማካካሻነት ውርስን ተፈፃሚ ለማድረግ ከወንጀል ምርመራው ጀምሮ የወንጀል ፍሬውን/ተመጣጣኝ/ንብረቶችን በማፈላለግ ከወንጀል ድርጊቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት በመመርመር ለስራው አስፈላጊነታቸውን በመመዘንና በወንጀል የተገኘ ንብረት/ተመጣጠኙ/ሀብት መሆኑ ሲረጋገጥ እንዳይባክን አድረጎ የመጠቀም መብትን በማሳገድ ማስተዳደር፣ ከወንጀል ክሱ ጋር ማስተሳሰር እና በክሱ ሊጠቀሱ የሚገባቸውን ፍሬ ነገሮች ማካተትና የተመዘበረውን ሀብት እንዲወረስ በማድረግ ማስመለስ ያስፈልጋል።[35]

በሕጋዊ መንገድ ሀብት የማፍራትና በባለቤትነት የተያዘ ንብረት በሌሎች ህጎችም ጥበቃ የተሰጠው ቢሆንም በኢትዮጵያ ህገ መንግስት የንብረት መብት በሀገሪቱ ህገ መንግስታዊ መብት መሆኑን በግልፅ የደነገገና ዋስትና የተሰጠው መሰረታዊ መብት እንደሆነ ያረጋግጣል።[36]

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብትን ለማስወረስ በሚፈፀመው ሂደት ጊዜ ስለሚወስድ ንብረቱን በማስተዳደር በኩል የሚደረገው ጥረት ጥንቃቄ የተሞላበት መሆን እንዳለበት ምሁራን እንዲህ በማለት ይገልፃሉ *While the case for confiscation is pending, the court may order provisional measures like seizure or freezing of the property in the meantime we need to ensure the safety and value of the asset until final decision on confiscation and even after confiscation order because of the procedure may potentially takes a period of years.*[37]

በወንጀል ምርመራ ወቅትም የተገኘ ጥቅም፣ዓይነትና የጉዳት መጠን በማስረጃ በማጥራት በሚቀርበው የወንጀል ክሰና የመውረስ አቤቱታ ላይ ለሚቀርብለት ፍርድ ቤት

---

[35] ፍትሕ ሚኒስተር፣ *የሙስና ወንጀል እና ልዩ የስነ ስርዓት ህግ ማስገንዘቢያ መፅሐፍ*፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፣2015 ዓ.ም፣ ገፅ 130።

[36] *የኢትየጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አዋጅ*፣1987 ዓ.ም፣የፌድራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 1/1987፣1ኛ ዓመት ቁጥር 1፣ አንቀፅ 40፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ።

[37] Biniyam Shiferaw, *AML/CFT Consultant, Stolen Asset Recovering Proceeds of Crime and Money Laundering-Tracing, Seizure, Freezing, Confiscation and Asset Management Training Material,* (Ethiopia, 2022).

ለውሳኔ አሰጣጥ ያመች ዘንድ የወንጀል ፍሬና ተያያዥነት ያለው እንዲሁም የወንጀል መፈፀሚያ የዋለ ንብረት ስለመሆኑ እንዲረጋገጥና የመወረስ ውሳኔ እንዲያርፍበት በግልፅ ዳኝነት መጠየቅ ይገባል፡፡[38]

ስለሆነም በወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረትን ለማስመለስ እና ተገቢ ስራ ለመስራት ከሀብት ምርመራ ጀምሮ መከታተልና ትኩረት መስጠት ስለሚያስፈልግ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት ከፖሊስ የወንጀል ምርመራ ክፍል ጋር በቅንጅትና በትብብር በቅርበት መስራት ያስፈልጋል፡፡[39]

በኢትዮጵያ ደረጃ ከሌሎች የስራ ክፍሎችና ሕጎች ጋር ተደርበው በስሱ ሲሰሩ ከመቆየታቸው ውጭ የተለየ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ለማስመለስ የተመሰረተ ተቋም እና ህግ ያልነበረ ሲሆን ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ግን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ስር በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት ጀነራል በመቋቋም ስራውን እያከናወነ የሚገኝና የበለጠ ለማጠናከር ራሱን የቻለ ህግ ለማውጣት በሂደት ላይ ያለ መሆኑን የፌድራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ የሆኑት አቶ ብሩክ አያሌው ገልፀዋል፡፡[40] በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ በሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ስር በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ በቡድን ደረጃ በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የተመሰረተና ትኩረት ያልተሰጠው በመሆኑ ውጤታማ አለመሆኑን ነገር ግን በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ከፍተኛ ስራ የሚያስፈልገው ስለሆነ ራሱን ችሎ በዳይሬክቶሬት ደረጃ ተቋቁሞ መሰራት የሚገባው ነው ሲሉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች የክልል ዐቃቤ ህግ የሆኑት አቶ ግርማ ሙልጌታ አጥብቀው ይገልፃሉ፡፡[41]

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ ስር በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት በ2015 ዓ.ም መጀመሪያዎቹ ወራት ጀምሮ ራሱን ችሎ ስራዎችን እያከናወነ የሚገኝ መሆኑን ፀሐፊው የዚሁ ዳይሬክቶሬት ባለሙያ ሆኖ በመስራት ላይ ያለ በመሆኑ ማረጋገጥ ችሏል፡፡ ስለሆነም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከፌደራል ፍትህ ሚኒስቴር፣ ከአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ኦሮሚያ ክልል ፍትህ ቢሮ ውጭ ሌሎች ክልሎች በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ራሱን የቻለ የስራ ክፍል የሌላቸው መሆኑን በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

---

[38] ዝኒ ከማሁ፡፡

[39] ዝኒ ከማሁ፡፡

[40] አቶ ብሩክ አያሌው፣ የፌድራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ፣ (አዲስ አበባ፣ 28/3/2016 ዓ.ም) ጋር የተደረገ ውይይት

[41] አቶ ግርማ ሙልጌታ፣ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ የክልል ዐቃቤ ሕግ፣ (አዲስ አበባ፣ 25/03/2016 ዓ.ም) ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

በህግ ደረጃም ቢሆን ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ የፌደራል ወንጀል ህጎች በተመሳሳይ ለክልሎችም ስለሚያገለግሉ ከሌሎች ህጎች ጋር በመቀላቀል እንጅ አሁን ላይ ራሱን የቻለ በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ የሚመለከት ህግ በሀገሪቱም ሆነ በክልሎች የለም፡፡

በፖሊሲ ደረጃም ቢሆን ራሱን የቻለ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስ ፖሊሲ የሌለ ሲሆን በ2014 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ የስነምግባርና የሙስና መከላከል ፖሊሲ በተወሰነ ደረጃ ስለ ህዝብና መንግስት ሀብት ደህንነት ሲገልፅ ሙስና በሁሉም ዘርፍ የሚከሰት ወንጀል ቢሆንም ካላቸዉ አጠቃላይ የተጋላጭነት ባህሪያትና አሰራር አንጻር የመንግስት ግዥ፣መሬት አስተዳደር፣ታላላቅ የመንግስት ፕሮጀክቶች፣ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር፣ የገቢ አሰባሰብና አስተዳደር፣የጉምሩክ አሰራር፣የኤሌክትሪክ አገልግሎት፣የፖሊስ/የትራፊክ ፖሊስ አሰራር፣ የፍርድቤቶች አሰራር፣የመንግስታዊ የልማት ድርጅቶች አሰራር እና የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም/ማዕድን ልማት/የበለጠ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ እና የተፅዕኖ ደረጃቸዉ በአንጻሩ ከፍተኛ የሆኑ ዘርፎች መሆናቸውን በማስቀመጥ በሃገራችን እነዚህን አካባቢዎች የበለጠ ትኩረት በመስጠት በአግባቡ መለየትና በቀጣይ ሙስናን በመከላከል ያለዉን ዉስን ሃብት ዉጤታማ በሆነ መልኩ ለመጠቀም የሚረዳ ይሆናል በማለት ያስቀምጣል፡፡[42]

ራሱን የቻለ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስ ህግ ባይኖርም ከሌሎች ህጎች ጋር ተቀላቅለው የሚገኙት በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስን የሚመለከቱ ህጎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉ መጥተዋል፡፡ ለምሳሌ የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/1997 አንቀፅ 9/1/ በወንጀል የተገኘ ሀብት በመሆኑ ሊታገድና ሊመለስ የሚችለው በተከሳሽ ስም ብቻ ያለ ሀብት ስለመሆኑ ሲደነግግ[43] የተሻሻለው የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና ማስረጃ ህግ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 882/2007 አንቀፅ 2/5/ ላይ በወንጀል የተገኘ ሀብትን ለማስመለስ በተከሳሽ ስም ብቻ ያለ ሀብት ሳይሆን በተከሳሽ የትዳር ጓደኛና ከ18 ዓመት በታች በሆኑ ልጆቹ ስም ያለ ንብረት እንደ ሁኔታው ለበወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለሰ እንደሚውል የደነገገ ሲሆን እንዲሁም ይህ አዋጅ በመግቢያው ላይ አዋጁ እንዲሻሻል ያስፈለገበትን ምክንያት ሲገልፅ በሙስና የተገኘ ሀብት/ተመጣጣኙን የማገድና የማስመለስ ስራ ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በማለት ያስቀመጠ በመሆኑ ለበወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ የተሻለ ትኩረት መሰጠቱንና ህጎች እየተሻሻሉ መምጣታቸውን ያሳያል፡፡[44]

[42] *የኢትዮጵያ የስነምግባርና የሙስና መከላከል ፖሊሲ*፣2014 ዓ.ም፣ቁጥር 4.7.፣አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፡፡
[43] በግርጌ ማስታወሻ 21 እንደተጠቀሰው አንቀፅ 9/1/፡፡
[44] በግርጌ ማስታዎሻ 4 እንደተገለፀው አንቀፅ 2/5/፡፡

የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 7 ላይ በተለያዩ ምክንያት ወንጀል ፈፃሚው በፈፀመው ወንጀል አለመጠየቅ የፍትሐብሔር ወይም አስተዳደራዊ ኃላፊነት ተጠያቂነትን እንደማያስቀር ይደነግጋል፡፡[45] ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው በኢትዮጵያ የሙስና ህግ በወንጀል የተገኘ ሀብትን ለማስመለስ የተለያዩ ማለትም በወንጀል፣በፍትሐብሔር እና በአስተዳደራዊ አማራጭ ሕጋዊ መንገዶችን በመጠቀም በወንጀል የተገኘን ንብረት ወደ ትክክለኛ ባለቤቱ ለማስመለስ ሰፊ ዕድል የሰጠና የተሻሻለ መሆኑን ያስረዳል፡፡

በወንጀል የተገኘ ሀብትን በቀላሉ ለማስመለስ የመንግስት ቁርጠኛ የሆነ ፖለቲካዊ ፍላጎት መኖር፣ ከመጠን ያለፈ የባንክ ህጎች ሚስጥር ጠባቂነት መሻሻልን፣የስነ ስርዓትና የማስረጃ ህጎች የተሟሉና ግልፅ ሆነው መቀረፅን እንደሚጠይቁ የህግ ባለሙያው በጥናታቸው ማጠቃለያ ላይ ያስቀምጣሉ፡፡[46]

በተጨባጭ እንደተዳሰሰው ከነክፍተቱም ቢሆን በወንጀል የተገኘ ሀብት ባለው ህግ በተገቢው መንገድ እንደማይተገበር የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌደራል ፍርድ ቤት ደረጃ የውክልና ስልጣኑ ባየው በወ/መ/ቁ. 27810 እና 28147 በማያመች ሁኔታ የመንግስትን ስራ መምራት የሙስና ወንጀል ክስ ሲቀርብ የመወረስ አቤቱታው አብሮ የቀረበ ቢሆንም በተከሳሾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ በመስጠት የእስራትና የገንዘብ መቀጮ ሲያሳርፍ የመወረስ አቤቱታውን በተመለከተ በመጀመሪያው መዝገብ ላይ ምንም ሣይል ያለፈ ሲሆን በሁለተኛው መዝገብ ላይ ደግሞ በፍትሐብሔር ችሎት በኩል ክርክር ተደርጎ ውሳኔ ይሰጥበት በማለት ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም በይግባኝም የተስተካከለበት ሁኔታ ያለ መሆኑን አያሳይም፡፡[47]

በአማራ ክልል በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ስራው ህጉ በሚፈቅደው አግባብ እየተከናወነ አለመቆየቱን በአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/መ/ቁ 02-27390 በቀረበ ክስና ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡[48] በዚህ መዝገብ ላይ ተከሳሽ በፈፀመችው ሀሰተኛ ሰነድ መገልገል የሙስና ወንጀል ስተከሰስ አብሮ የወንጀል ፍሬ የሆነውን የመንግስት የኢንቨስትመንት ቦታ እንዲወረስ የመውረስ አቤቱታ ለፍ/ቤቱ መቅረብ የነበረበት ባለመቅረቡ እንደገና ከወንጀሉ ውሳኔ በኋላ የመውረስ አቤቱታ ለብቻው ቀርቦ የኢንቨስትመንት ቦታው ለመንግስት የተመለሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

---

[45] *የሙስና ወንጀሎች አዋጅ*፣2007 ዓ.ም፣ፌድራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ አዋጅ ቁጥር 881/2007፣ 21ኛ ዓመት ቁጥር 36፣ አንቀፅ7፣አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፡፡

[46] *ማመኔ እንዳለ*, በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ መምህር፣ *Stolen Asset Recovery in Ethiopia: Critical Legal Issues and Challenges*, (ባህር ዳር፣2012) 5፡፡

[47] የአብክመ ፍትህ ቢሮ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት እና እነ ፈንታየ ገበየሁ [2015 ዓ.ም]፣ አብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የወ/መ/ቁ.27810 እና 28147፡፡

[48] አብክመ ፍትህ ቢሮ እና ሽማጫሽ አየለ፣አብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት [2015 ዓ.ም]፣ ወ/መ/ቀ 27390፡፡

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ለማስመለስ የወንጀል ክሱ ለቀረበለት የወንጀል ችሎት በማቅረብ ሳይሆን ራሱን ችሎ በሚቀርብ የፍትሐብሔር ክስ ለፍትሐብሔር ችሎት ነው በማለት ለሚነሱ መከራከሪያዎች ከተደነገጉ ህጎች በተጨማሪ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 24 ሰ/መ/ቁ 137908 ላይ የወንጀል ፍሬ የሆነ ንብረት በፍትሐብሔር ሳይሆን በወንጀል በተያዘ መዝገብ ላይ መወረስ/*confiscation*/ ማለቅ እንዳለበት አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቶ ይገኛል፡፡[49]

## 7. በወንጀል የተገኘ ሀብትን ለማስመለስ በአማራ ክልል ያለው ሁኔታ

ከአሁን በፊት ወንጀል ፈፃሚዎችን በእስራት ከማስቀጣት በዘለለ በወንጀል ድርጊት የተገኘውን ሀብት ማስመለስ ላይ ትኩረት ያልነበረው በባለድርሻ አካላት በኩል የግንዛቤ ማነስ፣ራሱን የቻለ በባለቤትነት ይዞ የሚሰራ የስራ ክፍልና በቂ የህግ ማዕቀፍ አለመኖር፣ ክስ ሲዘጋጅ በወንጀል የተገኘው ሀብት በተሟላ አኳኋን ክስ ቀርቦበት የክሱ አካል ሆኖ የመወረስ አቤቱታ ለፍርድ ቤት የመቅረብ ውስንነት፣ከአመንጭ ወንጀል ጋር ተያይዞ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ወደ ባለቤቱ ሊመለሱ የሚችሉ ንበረቶችን የመመርመር፣የማጣራትና የማሳገድ ስራ ያለመሰራት፣ ኤግዚቢቶችን በተገቢው መንገድ ለፍ/ቤት ያለማቅረብና የቀረቡትም ቢሆን በፍ/ቤት ውሳኔ ካገኙ በኋላ ወደ ንብረቱ ባለቤት ገቢ ያለመሆን እና በወንጀል የተገኘን ሀብት ማስመለስ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ላይ ውስንነቶች በሰፊው እንደነበሩ ይገልፃሉ፡፡[50]

በአማራ ክልል የህግ ማዕቀፍና የተቋማዊ አደረጃጀቱ ክፍተት እንዳለ ሆኖ በተግባር ያለው የተቀላቀለ አሰራር ትኩረት የሚያደርገው ወንጀል ፈፃሚዎችን ለፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ጥፋተኛ በማስባል በእስራትና በተወሰነ ገንዘብ ማስቀጣት ላይ እንጅ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስ ላይ ትኩረት ተሰጥቶት ሲሰራ አይስተዋልም፡፡[51]

በክልሉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብትን ማስመለስ በተመለከተ የተለዩ ህግ ባይኖርም ከሌሎች ህጎች ጋር እንደ ህጉ ባህሪ ተቀላቅሎ የሚገኝ ሲሆን ከሙስና ወንጀሎች አንፃር የክልሉን የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ[52] ብቻ ከማውጣት ያለፈ የተለዩ የህግ ማዕቀፍ የሌለና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር

[49] የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ዐቃቤ ህግ እና ወ/ሮ ፀሐይ አሰፋ [2010 ዓ.ም]፣ ፌድራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 137908፣ [2013 ዓ.ም] የፌድራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ቅፅ 24፡፡
[50] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1 እንደተጠቀሰው
[51] አቶ ሽድጋፍ ኃይሌ፣ የአብክመ ፍትህ ቢሮ በሰብአዊ መብት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ክልላዊ የፍልሰት ትብብር ጥምረት ቡድን መሪ ፣ (ባህር ዳር፣ 08/03/2016 ዓ.ም) ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ፡፡
[52] *የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ*፣2008፣ዝክረ-ህግ ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 237/2008፣21ኛ ዓመት ቁጥር 8፣ባህርዳር-ኢትዮጵያ፡፡

187/2003 የመንግስት ሰራተኞችን ሀብት ከመመዝገብ ባለፈ የራሱ የሆነ በወንጀል የተገኘ ሀብትን ለማስመለስ የሚያስፈፅም የህግ ክፍል የሌለው ቢሆንም ሀብትን ማሳወቅና ማስመዝገብ የመንግስት አሰራርን በግልፅነትና በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ከማድረጉም በላይ የስራ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይቀላቀሉ በየራሳቸው መንገድ የሚመሩበትን ግልፅ ስርዓት መዘርጋት ሊፈጥር የሚችለውን የጥቅም ግጭት በማስወገድ ሊመዘበር የሚችልን የህዝብ ሀብት በመከላከልና በወንጀል ድርጊት የተገኘን ሀብት ለማስመለስ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያትታል፡፡[53]

በአማራ ክልል በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት በክልሉ ፍትህ ቢሮ ስር  በ2015 ዓ.ም እንደተቋቋመ ወደ ስራ በመግባት ስራዎችን ሲያከናውን ምን ያህል ትኩረት የሚያስፈልገው መሆኑን በክልሉ በአዊ ብሔረሰብ ዞን፣በምስራቅ ጎጃም ዞን እና በምዕራብ ጎጃም ዞን ፍትህ መምሪያዎች በ2015 ዓ.ም በተደረገ የስራ ድጋፍ በቁጥር በወ/የተ/ሀ/ማዳ 07/2015 በቀን 20/06/2015 ዓ.ም በቀረበ ሪፖርት መሰረት በአዊ ብሔረሰብ ዞን ፍትህ መምሪያ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች የስራ ሂደት ላይ ከ2012-2015 ዓ.ም ግማሽ ዓመት ድረስ ውሳኔ ያገኙ የሙስና ወንጀል መዝገቦች ሲታዩ 16/አስራ ስድስት/ መዝገቦች ላይ 4,503,145.60 (አራት ሚሊዮን አምስት መቶ ሶስት ሺ አንድ መቶ አርባ አምስት ብር ከስልሳ ሳንቲም) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ያልተመለሰ መሆኑን፣ምስራቅ ጎጃም ዞን ፍትህ መምሪያ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች የስራ ሂደት 45/አርባ አምስት/ መዝገቦች ላይ 2,147,263.29 (ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ሰባት ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ሶስት ብር ከሃያ ዘጠኝ ሳንቲም) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ያልተመለሰ መሆኑን እና በምዕራብ ጎጃም ዞን ፍትህ መምሪያ የሙስና ወንጀል ጉዳዮች የስራ ሂደት 18/አስራ ስምንት/ ውሳኔ ያገኙ መዝገቦች ላይ ሲታይ  3,189,865.50 (ሶስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ያልተመለሰ መሆኑን በማረጋገጥ ለየዞን ፍትህ መምሪያዎቹ ተገቢውን የህግና የአሰራር ስርዓት በመከተል በወንጀል ድርጊት የተገኘው ሀብት እንዲመለስ በማለት የተሰጠበት የስራ አቅጣጫ ሪፖርት ያመለክታል፡፡[54] ከዚህ የስራ ክንውን ምልከታ መገንዘብ የሚቻለው ልዩ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብትን የሚመለከት ተቋምና ህግ ባለመኖሩ ባለው ህግና መዋቅር ወንጀል ፈጻሚዎች

---

[53] የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሀብት ማሳወቂያና ማስመዝገቢያ አዋጅ፣2003 ዓ.ም፣ዝክረ-ህግ ጋዜጣ፣አዋጅ ቁጥር 187/2003፣16ኛ ዓመት ቁጥር 25፣ አዲስ አበባ-ኢትዮጵያ፡፡

[54] በአብክመ ፍትህ ቢሮ በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ ዳይሬክቶሬት፣ የዞኖች የስራ ድጋፍ ሪፖርት፣ 2015 ዓ.ም (ያልታተመ)፣ ገፅ 1-7፡፡

ላይ ክስ መስርቶ ከማስቀጣት ያለፈ በተለያየ ወንጀል በተለይም በሙስና ወንጀል ምክንያት በወንጀል ፈፃሚዎች የሚወሰድ ሀብት እንደማይመለስ በግልፅ የሚያመለክት ነው፡፡

እንዲሁም ከፀረ-ሙስና ልዩ የስነስርዓትና የማስረጃ ህጉ አዋጅ ቁጥር 434/97 አንቀፅ 29 ተከሳሽ ጥፋተኛ የሆነ እንደሆን በወንጀል ድርጊቱ የተገኘው ንብረት እንዲወረስ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይሰጣል ከሚለው[55]ድንጋጌ ወጭ በሆነ መልኩ በባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በከባድ ዕምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል በደረሰው ጉዳት ልክ ከሳሽ ከዋናው የወንጀል ክስ ጋር ለወንጀሉ ችሎት በደረሰው የመንግስት ንብረት ጉዳት መጠን ተከሳሽ እንድትከፍል በማለት የመውረስ አቤቱታ አብሮ ያቀረበ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ግን ተከሳሽን በወንጀሉ ብቻ ጥፋተኛ ብሎ የእስራት ቅጣት ውሳኔ በማሳረፍ የመውረስ አቤቱታውን በተመለከተ በፍትሐብሔር በመክሰስ አስመልሱ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡[56]

አሁን ላይ የተጠናከረ ባይሆንም በክልሉ ፍትህ ቢሮ ስር ራሱን የቻለ በወንጀል ድርጊት የተገኘ የሀብት ማስመለስ የስራ ክፍል ተሰጥቶት እየሰራ ያለና ይበልጥ እንዲጠናከር ስራው በአዲስ ከመደራጀቱ አንፃር ዐቃቤ ህግ፣ፍርድ ቤት፣ፖሊስ እና ሌሎችም ተቋማት ተቀናጅተውና ተናበው በመስራት የወንጀል ምርመራዎች ሲጣሩ ጎን ለጎን በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት /ንብረት/ ማጣራትና ማሳገድ በሚገባው ልክ አብሮ መሰራትና ማስወረስ ይገባል ብለዋል፡፡[57]

የወንጀል ፍሬው መገኘት ካልተቻለ በተገቢው ሁኔታ ተከታትሎ ተመጣጣኝ የወንጀል አድራጊዎች ሀብት ማሳገድ የሚገባ ቢሆንም አላግባብና ተመጣጣኝ ያልሆነ የግለሰቦች ንብረት እንዳይታገድ ጥንቃቄ ማድረግና በወንጀል የተገኘ ሀብት ምክንያት የታገዱ ንብረቶች እንዳይባክኑ ንብረት አስተዳዳሪ በፍርድ ቤት ማሾም እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ፡፡[58]

## 8. ማጠቃለያ

ማንኛውም ሰው ሀብትና ንብረት በህጋዊ መንገድ ማፍራትና በባለቤትነት ለያዘው ሀብቱም ጥበቃ እንደሚደረግለት በተለያዩ ህጎች ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጅ ይህን ወደ ጎን በመተው የተለያዩ ወንጀል ፈፃሚዎች የራሳቸው ያልሆነውን ሀብትና ንብረት በወንጀል ድርጊት አማካኝነት ወደ ራሳቸው ሲወስዱ ይስተዋላል፡፡ በመሆኑም ይህ በወንጀል ድርጊት የተገኘው ሀብት ወደ እውነተኛ ባለቤቱ መመለስ እና ወንጀል ፈፃሚዎች በወንጀሉ ብቻ መቅጣት ሳይሆን በወንጀል ድርጊት የተገኘውን ሀብት በማስመለስ ህጋዊ ያልሆነ ጥቅም እንዳያገኙ ማድረግ

[55] በግርጌ ማስታወሻ 21 እንደተጠቀሰው አንቀፅ 29፡፡

[56] ምዕራብ ጎጃም ዞን ፍትህ መምሪያ የባህርዳር ቋሚ ምድብ እና አሰገደች ፈጠነ [2015 ዓ.ም]፣ የባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 14809፡፡

[57] የግርጌ ማስታወሻ 47፡፡

[58] ዝኒ ከማሁ፡፡

ተገቢ በመሆኑ የህግ ስርዓት ተበጅቶለትና ራሱን የቻለ የስራ ክፍል ተቋቁሞለት በልዩ ሁኔታ ሊሰራ የሚገበው ፋይዳ ያለው ጉዳይ ነው፡፡

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ነው ተብሎ የሚመለሰውም የወንጀሉ ፍሬ፣የወንጀሉ ፍሬ ካልተገኘ ተመጣጣኝ የሆነ የወንጀል ፈፃሚው ሕጋዊ ሀብትና ወንጀሉን ለመፈፀም የተጠቀመው መሳሪያ ሲሆኑ እነዚህን ወደ ትክክለኛ ባለቤቱ መመለስ ያለባቸውን በወንጀል ድርጊት የተገኙ ሀብቶች በጥፋተኝነት ላይ በመመስረት፣ያለ ጥፋተኝነት ላይ በመመስረት እና በፍታብሔር የመወረስ አቤቱታ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ማስመለስ የሚቻል ሲሆን እንዲሁም በአስተዳደራዊ የመውረስ ህጋዊ መንገድ ውሳኔ ያገኙ ንብረቶችን ተከታትሎ ማስፈፀም የሚቻል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስ በአማራ ክልል በዚህ ጽሑፍ እንደተዳሰሰው የተጠናከረ ተቋማዊ መዋቅር እና ራሱን የቻለ የህግ ማዕቀፍ የሌለው እንዲሁም ባለው የተቋም አደረጃጀትና በተበታተነ መልኩ በሚገኘው የህግ ስርዓትም ቢሆን ፍርድ ቤቶችና ሌሎች የፍትህ አካላት በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስን በተመለከተ ትኩረት በመስጠት በሚገባው ልክ ስራው እንደማይከናወን ከጥናቱ መረዳት ተችሏል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተወሰነ መጠንም ቢሆን በሀገራችንና በአማራ ክልል በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ለማስመለስ ሙከራ እየተደረገና ህጎችም በተወሰነ መጠን እየተሻሻሉ ቢሆንም ከጉዳዩ ውስብስብነት፣አስፈላጊነትና ለሀገር ካለው ከፍ ያለ ፋይዳ አንፃር የተለየ ትግበራ እና ትኩረት ያልተሰጠው፣ስራው የተሻለ ክህሎትና ዕውቀት እንደመፈለጉ መጠን በዚያ ልክ እየተከናወነ ያልሆነ ጉዳይ መሆኑን ያሳያል፡፡

ስለሆነም የክልሉ መንግስት ከፌደራል መንግስት ጋር በመሆን በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስን በተመለከተ ስራው በተፈለገው ልክ ውጤታማ እንዲሆን ራሱን የቻለ የፖሊሲ አቅጣጫና የህግ ማዕቀፍ/policy and legal frameworks/ ማለትም በአዋጅ፣ደንብ እና መመሪያ በግልፅ ደንግጎ ሊያዘጋጅ የሚገባ ሲሆን ራሱን የቻለ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ሀብት ማስመለስን የሚመለከቱ ተቋማዊ አደረጃጀቶች/institutional frameworks/ አጠናክሮ ማዋቀር የሚገባው ነው፡፡

እንዲሁም በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስ በፅንሰ-ሀሳብ ደረጃ መታወቅ ከጀመረ ቆየት ያለ ቢሆንም በሀገራችን በተለይም በክልላችን ወደ ተግባር የተገባው በቅረቡ ስለሆነ የወንጀል አፈፃፀሙ ውስብስብና በጥናት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሥራው የተለየ የክህሎት፣የአመለካከት፣የእውቀት፣የስነ-ምግባር እና የልምድ አቅም የሚጠይቅ ከመሆኑ አንፃር ለስራው ባለቤቶች አስፈላጊ ስልጠናዎች ሊሰጡ ይገባል፡፡ በተለይ ደግሞ በአብዛኛው በሀገር አቀፍም ሆነ በክልል ደረጃ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የኢኮኖሚ ጥቅም ለማግኘት በመሆኑና

ይህ የወንጀል ተግባር ደግሞ የህዝብን ህልውና የሚፈታተን ስለሆነ መንግስት ቁርጠኛ የሆነ የፖለቲካ ፍላጎትና ውሳኔ */committed political will and decision/* በመያዝ እና ከቀዳሚ አጀንዳዎች ውስጥ በዋናነት በማካተት*/prioritize mainstreaming in the current regional issues/* በማድረግ በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስን በልዩ ትኩረትና በሰፊው ሊሰራበት ይገባል፡፡

# የንግድ-ነክ እርቅ ስነ-ስርዓት በኢትዮጵያ፡ የአዋጅ ቁጥር 1237/2013 ዳሰሳ

ምህረቱ ይዘንጋው ድንቁ*

## መግቢያ

በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ውስጥ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች ተቀባይነት ያላቸው ሲሆን በልዩ ልዩ የህግ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ በዋናነት አማራጭ ሙግት መፍቻ መንገዶች የምንላቸው ድርድር /Negotiation/፣ እርቅ /Conciliation/ እና የግልግል ዳኝነት /Arbitration/ ናቸው፡፡[1]

ድርድር የሚባለው ግለሰቦች አለመግባባታቸውን በራሳቸው ስምምነት የሚፈቱበት አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገድ ነው፡፡[2] እርቅ ግለሰቦች በሶስተኛ ወገን አስማሚነት አለመግባባታቸውን የሚፈቱበት መንገድ ሲሆን ጉዳዩን ለመፍታት ሦስተኛ ወገን አስፈላጊ ቢሆንም በራሱ ውሳኔ የማይሰጥና አስገዳጅ ውሳኔ የመስጠት ሃላፊነት የሌለው ነው፡፡[3] በግልግል ዳኝነት አለመግባበት ለመፍታት ለጉዳዩ ገለልተኛ የሆነ ሦስተኛ ወገን ማስረጃ የማጣራት እና ልዩ ልዩ አካሄዶችን ተከትሎ ውሳኔ የሚሰጥበት ሲሆን በሦስተኛው ወገን የሚሰጠው ውሳኔ አስገዳጅነት ውጤት ይኖረዋል፡፡[4]

በኢትዮጵያ በ1952 በወጣው የፍትሐ ብሔር ህግ እርቅ[5] እና የግልግል ዳኝነት (በዘመድ ዳኛ የመጨረስ ስምምነት[6]) አሰራር የነበራቸው ሲሆን በ1958 በወጣው የፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ህግ መሰረት ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት የጀመሩትን ክርክር በእርቅ ፍጻሜ መስጠት ይችላሉ፤ከዚህ በተጨማሪም ህጉ በሚፈቅድበት ጊዜ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በግልግል ዳኝነት ለመጨረስ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡[7]

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከዚህ በኋላ ኢፌዲሪ ህገ መንግስት መሰረት የግል እና የቤተሰብ ህግን በተመለከተ በተከራካሪዎች መልካም ፈቃድ

---

* ፀኃፊው በህግ የመጀመሪያ ድግሪያቸውን ከጅማ ዩኒቨርሲቲ ያገኙ ሲሆን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በBusiness and Investment Laws ከደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አግኝተዋል፤ አሁን ላይ በአማራ ክልል ፍትሕ ቢሮ የወረዳ ዐቃቤ ሕግ ናቸው፡፡ ፀኃፊው ለዚህ ጽሁፍ አስተያየት የሰጧቸውን ሰዎች ለማመስገን ይፈልጋሉ፤ ለአስተያየት በ mihretuyizengaw@gmail.com መገኘት ይችላሉ፡፡

[1] Shipi M. Gowok፣ Alternative Dispute Resolution in Ethiopia - A Legal Framework 2 ‹‹ https://www.ajol.info/index.php/afrrev/article/view/41054 ›› ለመጨረሻ ጊዜ የተገበኘው ጥቅምት 30 2017 ዓ.ም

[2] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 3

[3] ዝኒ ከማሁ

[4] ዝኒ ከማሁ

[5] የኢትዮጵያ ፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 165/1952፣ ቁጥር 3318-3324

[6] ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 3325- 3346

[7] የፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 52/1958፣ ቁጥር 274

በሀይማኖቶች ወይም በባህላዊ ህጎች መሰረት መዳኘት ይቻላል[426]። ስለዚህ ህገ መንግስቱም አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶችን ድጋፍ የሰጣቸው መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል።

በኢትዮጵያ ወቅቱን የሚጠይቀውን፣ አለምአቀፍ ስምምነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ፣ የዳበሩ ስርዓቶችን እና መርሆችን ለማካተት እንዲሁም ግልግል ዳኝነት እና እርቅ ለባለጉዳዮች ያለው ነጻነት ብሎም ለፍትህ ስርዓቱ አጋዥ ስለሆኑ ከዚህ ቀደም የነበሩትን ህጎች ማሻሻል በማስፈለጉ አዲስ የግልግል ዳኝነት እና እርቅ አሰራር ስርዓትን በአዋጅ ቁጥር 1237/2013[427] ለመደንገግ ተችሏል።

በዚህ ጽሁፍም ከአዋጁ ክፍል የእርቅ አሰራር ስርዓትን በተመለከተ ምልከታ የሚደረግ ይሆናል። በጽሁፉ ቀጣይ ክፍልም ስለእርቅ አጀማመር፣ እርቅ ስምምነት፣ የአስታራቂዎች አመራረጥ እና ሚና፣ የእርቅ ሂደትን ስለማቋረጥ፣ እርቅን ስለመቃወም እና መሰል ጉዳዮችን በጽሁፉ ዋና ክፍል ይዳሳሰል። በመጨረሻም በክፍል ሦስት ደግሞ የጽሁፉ ማጠቃለያ የሚቀርበበት ይሆናል።

# 2. የንግድ ነክ እርቅ ስነ ስርዓት በኢትዮጵያ፡ የአዋጅ ቁጥር 1237/2013 ዳሰሳ

## 2.1. የአዋጁ አላማዎች

የግልግል ዳኝነት እና የእርቅ ስነ ስርዓት አዋጅ መውጣት ዋና ዋና አላማዎችን ከአዋጁ መግቢያ መረዳት እንደሚቻለው የሚከተሉት ናቸው።[428]

1. አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶችን በማስፋት ፍትህ የማግኘት መብትን ለማስፋት
2. አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶችን መጠቀም በተለይም ለኢንቨስትመንት እና ንግድ ነክ[429] አለመግባቶችን ለመፍታት ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑ
3. በግልግል ዳኝነት እና እርቅ ስርዓት ተሳታፊ ወገኖችን ወጭ፣ጊዜ መቀነስ፣ምስጢር በመጠበቅ የሚችል መሆኑ
4. ቀላል እና ለተዋዋይ ወገኖች ነጻነት ያለው ለማድረግ
5. በዘርፉ ልዩ ሙያ ያላቸውን አካላት ለማሳተፍ የሚቻልበት ለማድረግ

---

[426] የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት፣አዋጅ ቁጥር 1/1987፣አንቀጽ 34 (5)
[427] የግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አሠራር ሥርዓት አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 1237/2013፣ አንቀጽ 1
[428] ዝኒ ከማሁ፣ መግቢያ
[429] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 2 (7)፡- ንግድ ነክ ማለት የንግድ ባህሪ ካላቸው ከውል ወይም ከውል ውጭ ባሉ ግንኙነቶች ሁሉ የሚመነጩ ሆነው፣ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ ወይም ለመለዋወጥ የሚደረግ የንግድ ግንኙነት፣ ለማከፋፈል የሚደረግ ስምምነት፣ የንግድ ወኪልነትን፣ ኪራይን፣ የግንባታ ሥራን፣ የማማከር ሥራን፣ የምህንዴስና ሥራን፣ ለንግድ ጉዳይ የሚደረጉ የፈቃድ ጉዳዮች፣ የኢንቨስትመንት፣ የፋይናንስ ሥራ፣ የባንክ ሥራ፣ ኢንሹራንስ ፣የማዕድን ሥራዎች፣ በዚህ አዋጅ ከተከለከሉት ውጭ ያሉ የእሽሙር እና ሌሎች ንግድ ማህበራት ጉዳዮች፣ በአየር፣ በባህር ወይም በየብስ የሚደረጉ የሰው እና ዕቃ የማጓጓዝ ሥራዎች እና የመሳሰለትን ያካትታል።

6. በግልግል ዳኝነት እና እርቅ ስርዓት የሚታዩ እና የማይታዩ ጉዳዮችን ለመለየት፣ ጉዳዩ የሚመራበት፣ የሚወሰንበት እናየሚፈጸምበት አጠቃላይ የህግ ማዕቀፍ ለመስጠት
7. ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ማመቻቸት
8. የግልግል ዳኝነት እና የእርቅ ስርዓትን በተመለከተ በአለም አቀፍ ደረጃ የዳበሩ መርሆችን እና ልምዶችን ተሳቢ በማድረግ ነባር ህጎችን ለማሻሻል ናቸው፡፡

ከላይ በተጠቀሱት አላማዎች መሰረት በኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በልዩ ልዩ ህጎች የነበሩትን የግልግል ዳኝነት እና የእርቅ አሰራር ስርዓት በማሻሻል አሁን ላይ ወቅቱ የሚጠይቀውን የህግ ማዕቀፍ በተለይም ንግድ ነክ የሆኑ ጉዳይ ብቻውን ችሎ እንዲመራ በማሰብ ይህ የአሰራር ስርዓት አዋጅ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጽሁፍ ከአዋጁ መሰረታዊ ውስጥ እርቅ ስርዓትን በተመለከተ በሚከተለው ክፍል ዳሰሳ ይቀርባል፡፡

## 2.2. የንግድ ነክ እርቅ ስነ ስርዓት ዋና ዋና ጉዳዮች

### 2.2.1. የእርቅ አጻጻፍ ፎርም

እርቅ ማለት ተዋዋይ ወገኖች በሚመርጡት ሶስተኛ ወገን አጋዥነት ከውል ወይም ከውል ውጪ በሚመነጭ ሕጋዊ ውጤት ባለው ጉዳይ ላይ በክርክር ሂደት ወይም ወደፊት ሊፈጠር የሚችልን አለመግባባት ለመፍታት የሚያከናውኑት ሂደት[430]ሲሆን ይህንም ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባታቸውን በእርቅ ለመፍታት መስማማታቸውን በጽሁፍ ወይም በማናቸውም መንገድ ሲገለጹ ስምምነቱ ውጤት የሚኖረው ግን በተዋዋይ ወገኖች ብቻ ነው፡፡[431]

ተዋዋይ ወገኖች በጽሁፍ የሚያደርጉት ስምምነት በአንደኛው ወገን በፍርድ ቤት ለሚቀርብ ክስ የመጀመሪያ መቃወሚያ ሲሆን ፍርድ ቤቶችም ስምምነት የተደረሰበትን ጉዳይ ማየት አይችሉም፡፡[432] ነገር ግን ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የተደረገው የእርቅ ስምምነት የማይጸና ስለመሆኑ ውሳኔ ከሰጠ ወይም እርቁን ለማድረግ ተዋዋይ ወገኖች ያስቀመጡት ጊዜ ያለፈ መሆኑ ከተረጋገጠ ወይም እርቁን ለመጀመር የማያስችሉ በቂ ምክንያት መኖሩን ፍርድ ቤቱ ካመነ ክሱን ከመስማት አይከለከልም እንዲሁም ጉዳያቸውን በእርቅ እስከሚጨርሱ ድረስ የስምምነታቸውን ጉዳይ ለማየት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት የመጠባበቂያ እርምጃ እንዲሰጥ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡[433]

### 2.2.2. የእርቅ አጀማመር እና የአስታራቂዎች ሚና

እንታረቅ ባይ ወገን ለእርቁ መነሻ የሆነውን ጉዳይ ጠቅሶ ከሌላኛው ወገን ምላሽ የሚጠብቅበትን ቀን በመወሰን የእርቅ ሃሳቡን በቃል ወይም በጽሁፍ ሲያሳውቅ ሌላኛው ወገን ደግሞ

[430] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 2 (9)
[431] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 54
[432] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 55 (1)
[433] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 55 (2-3)

በተጠየቀው ቀን ውስጥ የእርቅ ሀሳቡን መቀበሉን የገለጸ እንደሆነ የእርቅ ሂደት እንደተጀመረ ይቆጠራል፡፡[434] ሆኖም እንታረቅ ተባዩ እንታረቅ ማስታወቂያው በደረሰው በሰላሳ ቀናት ወይም ማስታወቂያው ላይ የተገጸው ጊዜ ሳያበቃ ምላሽ ካልሰጠ የእንታረቅ ሃሳቡን አለመቀበሉን ወይም እንዳልፈለገ በመቁጠር እንታረቅ ባዩ የእርቅ ሀሳቡን እንዳነሳ ለሌላኛው ወገን ማሳወቅ አለበት፡፡[435]

አዋጁ በቀረበው የእርቅ ሀሳብ ላይ መልስ የሚሰጥበት መንገድ ያልገለጸ በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችን ማገናዘብ እንዳለብን ጸኃፊው ያምናል፡፡ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1681 ስለውል አቀራረብ እና አቀባበል ፈቃድን በጽሁፍ፣ በቃል ወይም በተለምዶ ጠቅላላ ምልክቶች ወይም ለውሉ መነሻ ከሆነው ምክንያት የተነሳ ግዴታ ለመግባት መፍቀዱን በማያጠራጥር ሁኔታ ማሳወቅ ይቻላል ነገር ግን ውል አቅራቢው የአቀባበሉን ሁኔታ ወስኖ ማቅረብ እንደሚችል ደንግጓል፡፡ በመሆኑም የእርቅ ስምምነት የቀረበለት ተዋዋይ ወገን በአዋጁ የተለየ አቀባበል ስርዓት ያልተቀመጠለት ስለሆነ ከጠቅላለው የውል ህግ ጋር በማገናዘብ አቀባበሉን በተመለከተ በአቅራቢው ካልተገለጸ በስተቀር መቀበሉን በማያጠራጥር መልኩ ማሳወቅ ይችላል፡፡

ተዋዋይ ወገኖች በተለይ ሁኔታ ተስማምተው አስታራቂዎች ሁለት ወይም ከዚያ በላይ እንዲሆኑ ካልወሰኑ በቀር በዚህ አዋጅ መሰረት የሚካሄድ እርቅ በአንድ አስታራቂ የሚመራ ሲሆን በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት መሰረት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ አስታራቂዎች ከሆኑ በጋራ መስራት አለባቸው፡፡[436]

ተዋዋይ ወገኖች የተለየ ስነ ስርዓት እንዲኖር ካልተስማሙ በስተቀር በአስታራቂ ብዛት እና ማንነት ላይ ለመስመማት ጥረት ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሆኖ ተዋዋይ ወገኖች አስታራቂ ሆኖ ለመስራት ምቹ የሆነ ሰው እንዲጠቁማቸው አንድን ተቋም ወይም ግለሰብን እገዛ መጠየቅ ይችላሉ፡፡[437] ከተስማሚ ወገን አስታራቂን ለመጠቆም ወይም ለመሰየም ጥያቄ የቀረበለት ተቋም ወይም ግለሰብ ስለ አስታራቂው ነጻነት፣ ገለልተኝነት እና ዜግነት በሚገባ ግምት ውስጥ አስገብቶ መጠቆም ወይም መሰየም ያለበት ሲሆን አስታራቂው ለአስታራቂነት ሲመረጥ ወይም ከተሰየመበት ጊዜ ጀምሮ በማስታረቁ ሂደት ሊያጋጥሙት የሚችሉ በነጻነቱ፣ በገለልተኛነቱ ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ይፈጥራሉ ብሎ የሚያስባቸውን ማንኛውንም ጉዳዮች ለተዋዋይ ወገኖች ሳይዘገይ ማሳወቅ አለበት፡፡[438]

---

[434] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 56 (1-2)
[435] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 56 (3)
[436] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 57
[437] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 58 (1-2)
[438] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 58 (3-4)

በዚህ ጉዳይ ላይ መረዳት የሚቻለው ተዋዋይ ወገኖች የአስታራቂን ቁጥር እና ማንነት ለመወሰን ነጻነት ያላቸው መሆኑን የምንገነዘብ ሲሆን ቁጥራቸውን በተመለከተ በአዋጁ እንደ ግልግል ዳኝነት የዳኞች ቁጥር ጎደሎ መሆን አለበት[439] ወይስ ሙሉ ቁጥር መሆን ይችላል በሚል ማስቀመጥ ሲገባው ለተዋዋይ ወገኖች ሙሉ መብት ሰጥቷል፡፡

አስታራቂው እንደተሰየመ ተዋዋይ ወገኖች ስለ እርቁ ጉዳይ አጠቃላይ ሁኔታ እና የእርቁን ፍሬ ነገር በጽሁፍ እንዲያሳውቁት ይጠይቃል፤ እያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን የሚያቀርበው ተጨማሪ ማስረጃ ለሌላው ወገን ቅጅው እንዲደርስ የሚደረግ ሲሆን ተዋዋይ ወገኖች ተጨማሪ ማስረጃ እንዲያቀርቡ እና እንዲያሥረዱ ሲጠየቁ ማቅረብ አለባቸው፡፡[440] ሆኖም ተዋዋይ ወገኖች በተለየ ሁኔታ ያደረጉት ስምምነት ከሌለ በስተቀር እርቅ በሌሎች መሰረታዊም ሆነ በስነስርዓታዊ ህጎች መሰረት እንዲመራ አይገደድም፡፡[441]

በእርቅ ሂደት ውስጥ አስታራቂዎች ራሱን የቻለ ሚና ያለው ሲሆን አስታራቂዎች ነጻ እና ገለልተኛ፣ ምክንያታዊ እና ፍትሐዊ መርሆችን መነሻ በማድረግ የተዋዋይ ወገኖችን መብት እና ግዴታ፣ ልማዳዊ አሰራር፣ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የነበረን የስራ ወይም የንግድ ግንኙነት እና አለመግባባቱ የመነጨበትን አካባቢያዊ ሁኔታዎች በበቂ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት እርቁን መምራት አለባቸው፡፡[442] በዚህም የነገሩን አካባቢያዊ ሁኔታ ለመረዳት ተዋዋይ ወገኖችን በቃል መስማት፣ የተዋዋይ ወገኖችን ፍላጎት እና አለመግባባቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍታት አስፈላጊነት ግምት ውስጥ አስገብቶ አመች መስሎ በታየው መንገድ እርቁን የሚመራ ሲሆን በማንኛውም የእርቅ ደረጃ ላይ የእርቅ ሃሳብ ማቅረብ ይችላል ሆኖም በጽሁፍ እንዲሆን እና ምክንያቱን እንዲገልጽ አይገደድም፡፡[443] አስታራቂ ሚናውን በተገቢው መንገድ ይወጣ ዘንድ በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ ሲያገኝ አግባብነት ካለው ተቋም ወይም ግለሰብ አስተዳደራዊ ድጋፍ ለመጠየቅ ይችላል፤ ይህን የድጋፍ ጥያቄ ተዋዋይ ወገኖችም በመጠየቅ ለእርቁ ሂደት መሳካት አስተዳደራዊ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ፡፡ [444]

### 2.2.3. የአስታራቂ እና የተዋዋይ ወገኖች ግንኙነት

አስታራቂ ሆኖ የተሰየመ አካል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በተናጥልም ሆነ በጋራ በጽሁፍም ሆነ በቃል ግንኙነት ማድረግ ይችላል፡፡[445] ስለሆነም አስታራቂው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር የሚፈጥረው ግንኙነት ነጻ እና ገለልተኛ ሆኖ መስራትን የሚጎዳ

---

[439] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 11
[440] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 59
[441] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 60
[442] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 61 (1-2)
[443] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 61 (3-4)
[444] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 62
[445] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 63 (1)

እንዳይሆን አዋጁ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማለት ግንኙነቱን ለማጥበብ ለማጥበብ ተሞከሯል፡፡ በተዋዋይ ወገኖች የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር አስታራቂው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በመመካከር እና የእርቁን አካባቢያዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሚገናኙበትን ቦታ ይወስናል፡፡[446]

የእርቅ ስርዓቱ ምስጢራዊነት ተገቢ በመሆኑ እርቁን ለማስፈጸም መግለጹ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር የእርቅ ስምምነት በምስጢር መጠበቅ ያለበት ቢሆንም አስታራቂው ከአንደኛው ወገን አለመግባባቱን በተመለከተ ያገኘውን መረጃ ለሌላው ተዋዋይ ወገን ከመግለጽ አይከለከልም ፤ነገር ግን ለአስታራቂው መረጃ የሰጠው ወገን መረጃው በምስጢር እንዲያዝለት በተጠየቀ ጊዜ መረጃውን ለመግለጽ የተከለከለ ነው፡፡[447]

ተዋዋይ ወገኖች ለእርቁ መሳካት ከአስታራቂው ጋር በቅን ልቦና የመተባበር፣ በአስታራቂው ሲጠየቁም ሰነዶችን እና ማስረጃዎችን የመስጠትና በውይይት ጊዜም በመገኘት ትብብር ማድረግና በቀና መስራት አለባቸው፡፡[448] በዚህም ተዋዋይ ወገኖች በራሳቸው አነሳሽነት ወይም ከአስታራቂው በሚቀርብላቸው ጥያቄ መሰረት አለመግባባቱን ለመፍታት የሚያስችል አስታራቂ ሃሳብ በማቅረብ ለእርቁ መሳካት የበኩላቸውን ሚና መወጣት አለባቸው፡፡[449] አስታራቂው ተዋዋይ ወገኖች ጉዳያቸውን በእርቅ እንዲጨርሱ ሚና ያለው ቢሆንም በተዋዋይ ወገኖች የሚደረግ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በእርቅ በያዘው ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ወይም የፍርድ ሂደት ላይ የግልግል ዳኛ፣ ጠበቃ ወይም ወኪል ሆኖ መስራት እንዲሁም በግልግል ዳኝነት ወይም በፍርድ ሂደት ውስጥ ምስክር ሆኖ መቅረብ አይችልም፡፡[450]
ከዚህ በተጨማሪም ተዋዋይ ወገኖች ጉዳያቸውን በእርቅ ለመፍታት በማሰብ የተሰጠ ሀሳብ ወይም አስተያየት፣ እምነት ቃል፣ እርቁን ለመቀበል የተሰጠ ፈቃደኝነት በግልግል ዳኝነት ወይም በፍርድ ሂደት ውስጥ በማስረጃነት ሊቀርብ አይችልም፡፡[451]

### 2.2.4. የእርቅ ስምምነት እና ውጤት

አስታራቂው በተዋዋይ ወገኖች ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል ሀሳብ መኖሩን ሲያምን ተዋዋይ ወገኖች እንዲያዩት በማድረግ እና ተዋዋይ ወገኖች ሀሳብ ካላቸው እንዲያቀርቡ በማድረግ የመግባቢያ ሰነዱን ሊያሥተካክል ይችላል፡፡[452] ተዋዋይ ወገኖች የእርቅ ስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት በተዘጋጀው ሰነድ ላይ መፈራረም ይችላሉ ሆኖም አስታራቂው በተዋዋይ

---

[446] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 63 (2)
[447] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 64
[448] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 65
[449] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 66
[450] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 74
[451] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 75
[452] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 67 (1)

ወገኖች ጥያቄ ከቀረበለት የእርቅ ስምምነቱን እራሱ ሊያዘጋጅ ወይም ተዋዋይ ወገኖች የሚያዘጋጁት ከሆነም ሊያግዝ ይችላል፡፡[453]

ተዋዋይ ወገኖች በስምምነታቸው ውስጥ መብት መተውን በተመለከተ የሚያደርጉት ስምምነት ውጤቱ በሌላኛው ወገን መብት መኖሩ መግለጽ ብቻ ነው፤ ስለዚህ የተተወ መብትን ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ የፎርም እና የችሎታ ግዴታዎች መጠበቅ አለባቸው፡፡[454] አስታራቂው የእርቅ ስምምነት ሰነዱን በማረጋገጥ ቅጅውን ለእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን መስጠት አለበት፡፡[455] በዚህ ላይ ልናጤነው የሚገባ ጉዳይ የእርቅ ስምምነት ውስጥ የመብት መተው ካለ እርቅ ስምምነቱ ከሌላው አስፈላጊ ጉዳይ በተጨማሪ ህጉ የሚጠይቀውን የፎርም ስርዓት እና የተዋዋይ ወገኖች ችሎታ ማሟላት እንዳለበት ነው፡፡

ተዋዋይ ወገኖች በእርቅ ስምምነት መድረሳቸው በእርቅ ስምምነት የተደረሰበት ጉዳይ በእነሱ መካከል ይግባኝ ሳይኖረው የመጨረሻ ሆኖ እንደተፈረደ ይሆናል፤ የአፈጻጸም ክስ የሚቀርበውም ጉዳዩ ለስምምነት ባይቀርብ ኖሮ ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እና ስምምነት የተደረሰበት ቦታ ላለው ፍርድ ቤት ነው፡፡[456]

### 2.2.5. የእርቅ ስምምነት ስለማቋረጥ እና ስለመቃወም

የእርቅ ሂደት የሚቋረጠው አስታራቂው ከተዋዋይ ወገኖች ጋር በመመካከር እርቁን መቀጠል አላስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን ሲያሣውቅ፣ ተዋዋይ ወገኖች በጋራ ስምምነት እርቁ መቋረጡን ለአስታራቂው በጽሁፍ ሲገልጹ፣ አንዱ ተዋዋይ ወገን ለሌላኛው ተዋዋይ ወገንና ለአስተራቂው እርቁ መቋረጡን በጽሁፍ ሲገልጽ ወይም የእርቅ ስምምነቱ ሲደረግ ነው፡፡[457]

ተዋዋይ ወገኖች በእርቅ የተያዘ ጉዳያቸውን ለፍርድ ቤት ወይም ለግልግል ዳኝነት ማቅረብ የሚችሉት በውል በተመለከተው ጊዜ ውስጥ አስታራቂው ተግባሩን ካልፈጸመ ወይም በውሉ ላይ ጊዜው ያልተገለጸ ሲሆን አስታራቂው ከተመረጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር መፈጸም ካልቻለ ወይም አስታራቂው እርቅ ስላለመደረጉ በጽሁፍ መግለጫ ሲሰጥ ብቻ ነው፡፡[458] ሆኖም ተዋዋይ ወገኖች መብታቸውን ለመጠበቅ ሲባል ፍርድ ቤት የመጠበቂያ እርምጃ ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው አቤቱታ ማቅረብ ያልተከለከለ ሲሆን አቤቱታ የሚቀረበውም እርቁ እየተካሄደ ባለበት አካባቢ የሚገኝ እና ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን ላለው ፍር ቤት ነው፡፡[459]

---

[453] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 67 (2)
[454] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 67 (3)
[455] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 67 (4)
[456] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 68
[457] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 69
[458] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 70 (1)
[459] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 70 (2)

በመሰረታዊነት ተዋዋይ ወገኖች የእርቅ ስምምነትን የመቃወም መብት አላቸው ነገር ግን ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ያደረጉባቸውን መብቶች በተመለከተ በተዋዋይ ወገኖች ወይም በአንደኛው ወገን በተደረገው ስህተት ምክንያት የእርቅ ስምምነትን ለመቃወም አይችሉም፡፡[460]

ስምምነት የተደረሰበት ጉዳይ እንዲፈጸም አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ለመቃወም የሚቻለው የተገለጹትም እርቅ ለመድረግ የተደረገው ስምምነት ፈራሽ ወይም የማይጸና ሲሆን፣ የተደረሰው የእርቅ ስምምነት ግልጸኝነት የጎደለው ሲሆን፣ የተደረገው ስምምነት ለመልካም ባህሪ ተቃራኒ ወይም የህዝብ ሰላም እና ፖሊሲ የሚጻረር ሲሆን ወይም ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ ስምምነቱን ለማድረግ ችሎታ የሌለው እንደሆነ በማስረዳት መቃወም ይቻላል፡፡[461]

ከዚህ በተጨማሪም በውሉ ላይ መሰረታዊ ስህተትን መሰረት በማድረግ የእርቅ ስምምነትን መቃወም የሚቻል ሲሆን ነገርግን ይህ ሊሆን የሚችለው ለመፈጸም ግዴታ የገቡበት ሰነድ በራሱ ፈራሽ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡[462] ተዋዋይ ወገኖች ወይም ከተዋዋይ ወገኖች የአንዱ ፈቃድ የተገኘው ሀሰተኝነቱ በታወቀ ሰነድ መሰረት እንደሆነ ስምምነቱን ለማፍረስ ይቻላል ሆኖም በውሉ ጊዜ ተዋዋይ ወገኞች ሰነዱ ፈራሽ ወይም ሀሰተኛ እንደሚሆን አስበው የተስማማሙ እንደሆነ ስምምነቱ እንደጸና የሚቀር ይሆናል፡፡[463]

### 2.2.6. የእርቅ ሂደት ወጭ እና ክፍያ

በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ከሌለ በስተቀር ለአስተራቂው በእርቁ ምክንያት ያወጣውን ወጭ ከሚከፈል ክፍያ በስተቀር የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ የለውም፤ ስለዚህ የእርቁ ሂደት ሲቋረጥ ያወጣውን ወጭ በመወሰን ለተዋዋይ ወገኖች በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡[464] በእርቅ ሂደት ውስጥ ወጭ የሚባሉት በተዋዋይ ወገኖች እና በአስታራቂው ስምምነት የተጠሩ ምስክሮች የሚከፈል ክፍያ፣ በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ በአስታራቂው ጠያቂነት በሙያተኛ ለተሰጠ ሙያዊ አስተያየት ወይም ምክር የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ፣ በአዋጁ መሰረት ለተሠጡ አገልግሎቶች የሚከፈሉ ክፍያዎች እና ሌሎች ከእርቅ ሂደት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ወጭዎችና ክፍያዎችን ያካትታል፡፡[465] ስለሆነም ተዋዋይ ወገኖች በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር ወጭ እና ክፍያዎች በተዋዋይ ወገኖች በጋራ የሚሸፈን ይሆናል፡፡ ተዋዋይ ወገኖች የእርቅ ስምምነት ያደረጉት ከክስ በኋላ ከሆነ ለዳኝነት የከፈሉት ክፍያ እንደ

[460] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 71 (1)
[461] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 71 (2)
[462] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 71 (3)
[463] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 71 (4-5)
[464] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 73 (1-2)
[465] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 73 (3)

አግባብነቱ ተመላሽ ይሆናል፤ በዚህ ገዳይ ለሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ እንዲወጣ ስልጣን ተሰጥቷል፡፡[466]

## 2.3. የአዋጁ ክፍተት እና የመፍትሄ ሃሳቦች

ከላይ ከአዋጁ ክፍል ውስጥ የእርቅ አሰራር ስርዓትን በተመለከተ ከእርቅ አጀማመር እስከ አፈጻጸም ለመመልከት የተሞከረ ሲሆን ከዚህ በታች ደግሞ በዚሁ ዙሪያ በሚመለከት በጸኃፊው እይታ የአዋጁ ክፍተቶችን እና የመፍትሄ ሃሳቦችን እንደሚከተለው ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

### 2.3.1. የፍርድ ቤት ጣልቃ ገብነትን በተመለከተ

በአዋጁ ክፍል አንድ ከጠቅላላ ድንጋጌዎች ውስጥ አንቀጽ 5 ላይ የፍርድ ቤቶች ጣልቃ ገብነትን በተመከለተ ፍርድ ቤቶች በአዋጁ ከተሰጣቸው ስልጣን ውጭ በግልግል ዳኝነት በሚታዩ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ እንደማይገቡ ሲደነግግ እርቅን በተመለከተ ግን በዝምታ አልፎታል፤ አንድም በአዋጁ ክፍል ሁለት ስለ ግልግል ዳኝነት በሚመለከተው መግለጽ እየተቻለ በጠቅላላ ድንጋጌ ስር መገለጹ ሁለትም እርቅን በተመለከተ በክፍል ሦስት በእርቅ ሂደት ላይ ስለ ፍርድ ቤት ጣልቃ ገብነት በዝምታ መታለፉ ጸኃፊው የአዋጁ ክፍተት መሆኑን ተረድቷል፡፡ ስለሆነም በመርህ ደረጃ በፍትሐ ብሔር ጉዳይ ያልተከለከለ ተግባር እንደተፈቀደ ስለሚቆጠር ፍርድ ቤቶች በእርቅ ሂደት ውስጥ ጣልቃ ገብነታቸው እንዳልተከለከለ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የፍርድ ቤቶች ጣልቃ ገብነት የእርቅ ስርዓትን ነጻነት ስለሚነፍግ ስለሚችል አዋጁ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ግልጽ የሆነ ድንጋጌ ሊኖረው ይገባል፡፡

### 2.3.2. ለእርቅ የማይቀርቡ ጉዳዮችን በተመለከተ

በአዋጁ አንቀጽ 7 መሰረት ልዩ ልዩ ጉዳዮች ለግልግል ዳኝነት እንደማይቀርቡ ክልከላ ተደርጓል፡፡ ይህን አንቀጽ ስንመለከት በዋናነት ለመንግስት ጥቅም፣ የህዝብ ሞራል፣ ከጉዳዩ ውስብስነት አንጻር እና መሰል ምክንያት ተደርጎ ጉዳዮች ለግልግል ዳኝነት ዝግ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ እርቅን በተመለከተ ግን በዝምታ ማለፉ ማንኛውም ጉዳይ ለእርቅ መቅረብ ይችላል የሚልን እሳቤ ሊያመጣ የሚችል ቢሆንም አዋጁ የስርዓት አዋጅ በመሆኑ በሌሎች መሰረታዊ ህጎች ለእርቅ የማይቀርቡ በሚል ክልከላ ከተደረገ ግን ጉዳዩን ለእርቅ ማቅረብ እንደማይቻል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የሕንድ የግልግል ዳኝነት እና የእርቅ ህግ ለእርቅ የማይቀርቡ ጉዳዮችን በተመለከተ በሌሎች ህጎች በተለየ ሁኔታ ካልተከለከለ በስተቀር ተዋዋይ ወገኖች አለመግባባታቸው በእርቅ መፍታት ይችላሉ በማለት ተደንግጓል፡፡[467] ስለዚህ የኢትዮጵያ የግልግል ዳኝነት እና የእርቅ ስርዓት አዋጅም ለእርቅ የማይቀርቡ ጉዳዮችን

---

[466] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 76
[467] Arbitration and Conciliation Act of India, (enacted 1996 )፣ አንቀጽ 61

በተመለከተ እንደ ግልግል ዳኘነት በግልጽ ማስቀመጥ ነበረበት እንጂ በዝምታ ማለፍ አልነበረትም፡፡

## 2.3.3. የአስታራቂ ቁጥርን በተመለከተ

አዋጁ የግልግል ዳኘነት ዳኞችን በተመለከተ ተዋዋይ ወገኖች ቁጥራችውን መወሰን እንዲችሉ ፍቃድ በመስጠት ነገርግን ቁጥራቸው ጎደሎ ቁጥር መሆን እንዳለባቸው እና ተዋዋይ ወገኖች ካልተስማሙ ግን ሦስት መሆን አለባቸው በሚል በአስገዳጅነት አስቀምጧል፡፡[468] አስተራቂን በተመለከተ እርቅ የሚመራው በአንድ አስታራቂ ሲሆን ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ከፈጠሩ ግን ሁለት እና ከዛ በላይ መሆን እንደሚችሉ አዋጁ ያሥቀምጣል፡፡[469] በዚህ ጉዳይ ላይ የሕንድ የግልግል ዳኘነት እና የእርቅ ህግ የእርቅ ሂደት የሚመራው በአንድ አስታራቂ ሲሆን የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ካለ ግን ሁለት ወይም ሦስት መሆን አለበት፤ አስታራቂዎች ከአንድ በላይ በሆኑ ጊዜ ስራቸውን በጋራ የሚወጡ ይሆናል በማለት ይገልጻል፡፡[470]

ከዚህ በተጨማሪም የተባባሩት መንግስታት ድርጅት የአለም አቀፍ ንግድ ህግ ኮሚሽን የእርቅ ደንብ / *United Nations Commission On International Trade Law Conciliation Rules* (*UNCITRAL*) በአንቀጽ 3 የአስታራቂ ብዛትን በተመለከተ አስታራቂ አንድ መሆን እንዳለበት ነገርግን የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ካለ ሁለት ወይም ሦስት መሆን ያለባቸው ሲሆን አስታራቂዎች ከአንድ በላይ በሚሆኑበት ጊዜ ስራቸውን በጋራ መስራት ጠቅላላ ደንብ ይሆናል በማለት ያስቀምጣል፡፡[471]

ስለሆነም የኢትዮጵያ የግልግል ዳኘነት እና የእርቅ አሰራር ስርዓት አዋጅ የአስታራቂ ቁጥርን በተመለከተ በአንድ አስታራቂ እንዲመራ በመርህ ደረጃ ካስመጠ በኃላ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ግን ሁለትና ከዚያ በላይ አስታራቂ ማድረግ ይችላሉ በማለት የገለጸ ሲሆን ከላይ በምሳሌ የተጠቀሱት የሀገር ህግ እና አለም አቀፍ መርህ ላይ ስንመለከት እርቅ በአንድ አስታራቂ ይመራል ነገር ግን ተዋዋይ ወገኖች ከተስማሙ ሁለት ወይም ሦስት መሆን ይችላሉ በማለት ያስቀምጣል፡፡ ስለዚህ አዋጁ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት መሰረት አስታራቂዎች ሁለትና ከዚያ በላይ መሆን ይችላሉ በማለት መግለጹ የአለም አቀፍ መርህ ሁለት ወይም ሦስት ስለሚል የተለየ በመሆኑ፤ አዋጁ ከታወጀበት አላማ አንዱ ከሆነው አለም አቀፋዊ መርሆችን ለማካተት ልዩነት ያለው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

---

[468] *የግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አሠራር ሥርዓት አዋጅ፣የግርጌ ማስታወሻ* 9፣*አንቀጽ* 11

[469] *ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ* 57

[470] *ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ* 63

[471] United Nation General Assembley Reosultion No.35/52, on December 04 1980፣ United Nations Commission On International Trade Law Conciliation Rule፣ አንቀጽ 3

### 2.3.4. የእርቅ ስምምነትን በተመለከተ

አዋጁ የግልግል ዳኝነት ስምምነትን[472] በትርጓሜ አንቀጽ በግልጽ ትርጉም የሰጠ ሲሆን እርቅ ስምምነትን በተመለከተ ግን በግልጽ የሠጠው ትርጉም የለም፡፡ ስለሆነም በእርቅ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያለውን የእርቅ ስምምነት ትርጉም አለመስጠቱ እርቅ ስምምነት አለ ወይስ የለም የሚለውን ለመለየት እና ትርጉም ለመስጠት የሚያሥቸግር ስለሚሆን አዋጁ በትርጓሜም ሆነ በሌላ መንገድ ለጉዳዩ ምላሽ መስጠት ነበረበት፡፡

### 2.3.5. የእርቅ ስምምነት ፎርምን በተመለከተ

አለመግባባትን በእርቅ ለመፍታት ተዋዋይ ወገኖች ስምምነታቸውን በጽሁፍ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ መግለጽ ይችላሉ በማለት የእርቅ ስምምነትን ፎርም ለተዋዋይ ወገኖች ምርጫ ሰጥቷል፡፡[473] በሌላ በኩል በፍርድ ቤት መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችለው በጽሁፍ የተደረገ እርቅ ስምምነት ብቻ መሆኑን አዋጁ ይገልጻል፡፡[474] አዋጁ ለተዋዋይ ወገኖች እርቅ ስምምነታቸውን በፈለጉት መንገድ ማድረግ የሚችሉ መሆኑን መብት ከሰጠ በኂላ በጽሁፍ የተደረገን እርቅ ስምምነት ብቻ ለመቃወሚያነት ማቅረብ እንደሚቻል መግለጹ የተዋዋይ ወገኖችን መብት ያጠባል፤ ከዚህ በተጨማሪም እርቅ ስምምነት መኖሩን እንዲያስረዱ በማድረግ ለፍርድ ቤት ክርክር መቃወሚያ ማድረግ ሲቻል ተዋዋይ ወገኖች በፈለጉት ፎርም እርቅ ስምምነት እንዲያደርጉ ከተፈቀደ በኂላ በፎርም ጉዳይ ለመቃወሚያ መስፈርት ማድረጉ ተመጋጋቢነት የሌለው ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ግለሰቦች ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ ስምምነት ካደረጉ በኃላ የእርቁ ጉዳይ ከማለቁ በፊት ፍርድ ቤት ክስ ቢያቀርቡ በተከራካሪ ወገኖች በኩል የመጀመሪያ መቃወሚያ ሊቀርብ የሚችል መሆኑን ከፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 244/2/ረ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 161062 በሰጠው ውሳኔ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በሽማግሌ እንዲታይ ወደውና ፈቅደው ከተስማሙ በኂላ ሽማግሌዎች የሰጡት ውሳኔ ባለበት ሁኔታ እርቅን በይግባኝ ማስተካከል በሚፈቅደው የህግ ማዕቀፍ ማስተካከል ከሚገባ በቀር እርቁን በመተው አዲስ ክስ ማቅረብ በመጀመሪያ መቃወሚያ ሊዘጋ የሚገባ አለአግባብ ክስ ነው በማለት አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡[475]

---

[472] የግልግል ዳኝነት እና የዕርቅ አሠራር ሥርዓት አዋጅ፣የግርጌ ማስታወሻ 9፣ አንቀጽ 2 (1) **የግልግል ዳኝነት ስምምነት** ማለት ከውል ወይም ከውል ውጭ ባለ ሕጋዊ ግንኙነት ሊፈጠር የሚችልን ወይም የተፈጠረን አለመግባባት በሙሉ ወይም በከፊል በግልግል ዳኝነት ለመፍታት የሚፀም ስምምነት ነው፡፡

[473] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 54

[474] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 55 (1)

[475] በአመልካች አቶ መሀዲ ሽረፋ እና በተጠሪ ሻፊ ሽረፋ (2011) የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 161062፣ (2013) 24 የኢትዮጵያ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ 7

ስለዚህ የእርቅ ስምምነትን አቅራቢው ወገን እርቅ ስምምነት መኖሩን እስካስረዳ ድረስ በሌሎች ጉዳዮች በጽሁፍም ሆነ በቃል የተደረገ ስምምነት ፍርድ ቤቶች ሊቀበሉት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ሆኖም አዋጁ እርቅ ስምምነት ፎርምን በተመለከተ ተዋዋይ ወገኖች በፈቀዱት መንገድ ማድረግ እንደሚችሉ በአዋጁ ከተገለጸ በእርቅ ስምምነት ላይ ስለሚደረግ መቃመወም በሌሎች ስነ ስርዓት ህጎች እንዲሸፈን ማድረግ ይገባ ነበር፡፡

### 2.3.6. የመሸጋገሪያ ድንጋጌን በተመለከተ

የአዋጁ መሸጋገሪያ ድንጋጌ የሚገልጸው ስለግልግል ዳኝነት ብቻ መሆኑ በእርቅ ሂደት ላይ የነበሩ ጉዳዮች በምን መልኩ መቀጠል እና መቋጨት እንዳለባቸው መግለጽ የሚገባው ነበር፡፡[476] ስለዚህ መሸጋጋሪያ ድንጋጌው ለሁሉም ጉዳዮች መሆን ሲገባው ስለ ግልግል ዳኝነት ብቻ መደረጉ የአዋጁ ክፍተት ስለሆነ ሊስተካከል ይገባል፡፡

## 3. የማጠቃለያ ሀሳብ

በኢትዮጵያ የሕግ ስርዓት ውስጥ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች በህግ ማዕቀፍ ሆነው አገልግሎት እየተሠጡ ይገኛሉ፡፡ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶችም በዋናነት ስምምነት፣ እርቅ እና የግልግል ዳኝነት ናቸው፡፡ በዋናነት ከፍርድ ቤት ውጭ አለመግባባትን መፍታት ከፍርድ ቤት ክርክር ልዩ የሚያደርገው የባለጉዳዩን ስምምነት የሚጠይቁ በመሆናቸው ነው፡፡

አሁን ላይ በኢትዮጵያ ንግድ ነክ የግልግል ዳኝነት እና እርቅ ስርዓት የሚመራው በአዋጅ ቁጥር 1237/2013 ሲሆን ግለሰቦች የሚያጋጥማቸውን አለመግባባት በእርቅ መፍታት ሲፈልጉ የእርቅ ስምምነታቸውን በጽሁፍም ሆነ በማንኛውም መንገድ ማድረግ ይችላሉ፡፡ እርቅ ለመጀመር እንታረቅ ባይ በሚመቸው መልኩ ሲጠይቅ ተቀባይም መቀበሉን ሊገልጽ በሚችል መንገድ ከገለጸ እርቅ ስምምነት የሚደረግ ሲሆን በስምምነታቸው የአስታራቂ ብዛትና ማንነት ይወሰናል፡፡

የእርቅ ስምምነት በሚተረጎምበት ጊዜ በጠባቡ መተርጎም ይኖርበታል እንዲሁም የእርቅ ስርዓት በሌሎች ህጎች እንዲመራ አይገደድም፡፡ ተዋዋይ ወገኖች የእርቅ ስምምነት ላይ ከደረሱ ይግባኝ ሳይኖረው እንደተፈረደ ፍርድ ተቆጥሮ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ክስ ይቀርባል፡፡ የእርቅ ስምምነት በልዩ ልዩ ምክንያት ማቋረጥ የሚቻል ሲሆን የእርቅ ስምምነት የተደረሰበትን መቃወም የሚቻለው መብቱን የሚጠይቀው ወገን የሚጠይቅበትን ምክንያት በአግባቡ ማስረዳት ሲችል ነው፡፡ በእርቅ ሂደት ውስጥ አስታራቂ የነበረ ሰው በተያዘው ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ወይም በፍርድ ሂደት የግልግል ዳኛ፣ጠበቃ ወይም ወኪል ሆኖ መስራት አይችልም፡፡ በእርቅ ሂደት ውስጥ የተነገሩ ወይም የቀረቡ መረጃዎችና

---

[476] ዝኒ ከማሁ፣ አንቀጽ 77

ማስረጃዎች በግልግል ዳኝነት ወይም በፍርድ ሂደት ለማስረጃነት አይቀርቡም፤ በሌላ በኩል ወጭን በተመለከተ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ካልተወሰነ በስተቀር በተዋዋይ ወገኖች በጋራ የሚሸፈን ይሆናል፡፡

ከላይ በጽሁፉ የአዋጁ ክፍተት ተብሎ ለማመላከት የተሞከረው እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጁ መውጣቱ ንግድ ነክ እርቅን ለማከናወን እፎይታ የሚሰጥ አዋጅ መሆኑን የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

**Author's Guidelines**

The Law School of Debre Markos University publishes a peer-reviewed journal of law, Chokie Journal of Law. The Journal is published annually, every October. The purpose of the journal is to publish the results of original scientific researches on a wide range of issues of law such as the history of legislation and state institutions, philosophy and sociology of law. This brief guideline is prepared based on the Journal's Policy with a view to inform potential contributors.

## 1. Content of the Journal

The Journal publishes:

**1.1.Feature Articles**: which are a thorough, original and high-quality academic analysis. These are scholarly writings on any law or law related topic that meet the rigors of academic writing. The Journal shall feature at least three articles in each issue.

**1.2.Case Comments**: which are manuscripts in which authors critically comment on relevant cases decided by domestic and international courts as well as international tribunals and other quasi-judicial body.

**1.3.Legislative Reviews**: which are manuscripts presenting the salient features of a new or revised legislation in Ethiopia or comparative analysis of related laws.

**1.4.Book Reviews**: which are manuscripts that provide a summary and critic of a book on Ethiopian laws or other topics and themes related to law.

**1.5.Reflections/Notes**: which are manuscripts in which authors put forward their personal thoughts and insights on a pressing issue of law with a view to stimulating a discussion and/or debate.

**1.6.Review Article**: an article that generally summarizes the current state of understanding on a given topic. It surveys scholarly researches already conducted in an area, and it should give an overview of current thinking on the theme.

**1.7.Letter /Letter to the Editor/**: refers to written submissions to the Editor-in-Chief making comments on an article published in previously published issues of the same journal.

## 2. Language of Publication

**2.1.**Contributions can appear in the Journal in Amharic or English language. Contribution in Amharic language shall have English Abstract

**2.2.**Contributions shall be published in the language their author has originally authored them in.

**2.3.**All contributions, whether in Amharic or English should be submitted using "Template for Chokie JoL".

## 3. Exclusivity of Contributions

All contributions that appear in the Journal should be unpublished original works of the author.

## 4. Copyright

**4.1.**The Publisher (School of Law of Debre Markos University) retains copyright over the articles published in the Journal. However, authors may be granted the right to republish their articles if the Board is notified of such use and that it carries the appropriate copyright notice.

**4.2.**The author of a published manuscript is entitled to receive electronic copy of his contribution and one complimentary copy of the issue in which his contribution appears, free of charge.

## 5. Process of Submission

**5.1.**Contributions may be submitted as an attached MS Word document, to the Editor-in-Chief via the via the email chokiejol@dmu.edu.et

**5.2.**Authors should submit a separate cover letter using the "**Cover Letter for Chokie JoL**" format.

## 6. Size of Contributions

The size of contributions shall be as follows, excluding footnotes:

**6.1.**Articles (5000 to 12000 words)

**6.2.**Review Articles (5000 to 10000 words)

**6.3.**Legislative reviews (1000 to 3000 words)

**6.4.**Case Comments (1000 to 4000 words)

**6.5.**Book/Article reviews (1000 to 3000 words)

**6.6.**Notes (2000 to 4000 words)

**6.7.**Letter to the Editor (1000 to 2000 words)

## 7. Content and Presentation Style of manuscripts

**7.1.**Feature articles, review articles, and notes/reflections should be using "**Template for Chokie JoL**" and have the following structure:

i. Title

The article title appears center justified at the top of the first page. The title font is 16 pt, bold. The rule for capitalizing the title is; all words should be capitalized. Do not begin titles with articles (e.g., a, an, the) or prepositions (e.g., on, by, etc.).

ii. Author's name

The list of author/s/ immediately follows the title. The font is 12 pt bold and the author(s)' names are left justified.

iii. Author's affiliations and biographies (see 7.6)

iv. Abstract

With single-paragraph, the abstract should be a summary of the paper and not an introduction. Because the abstract may be used in abstracting and indexing databases, it should be self-contained (i.e., no numerical references) and substantive in nature, presenting concisely the objectives, methodology used, results obtained, and implication/recommendation. The abstract should be an objective representation of the article and it must not contain results that are not presented and substantiated in the main text and should not exaggerate the main conclusions. Complete sentences, active verbs, and the third person should be used. The tense should be in simple past. No literature should be cited. Abstract should not exceed 300 words.

v. Key words/terms

List three to five pertinent keywords/ terms specific to the article yet reasonably common within the subject discipline. The key words should indicate the content of the manuscript but without merely replicating its title or textual sub-headings. These words should be separated with semicolons.

vi. Introduction

The introduction part should provide adequate background that puts the manuscript into context. This is to allow readers to understand the purpose and significance of the study. Authors should avoid a detailed literature survey or a summary of the results. Hence, it has to define the problem addressed and why it is important. It should also include a brief review of the key literature. It should also note any relevant controversies or disagreements in the field. Finally, it needs to conclude with a brief statement of the overall aim of the work and the organizational structure of the paper.

vii. Body

The body should contain discussions, analyses, arguments, etc. and may be divided into sections, and subsections depending on the author's approach to the subject matter. The body of the paper consists of numbered sections that present the main findings. The rules for capitalizing for sentences are; only the first word, proper nouns, and acronyms should be capitalized. At the first occurrence of an acronym, spell it out followed by the acronym in parentheses, e.g., United Nations High Commissioner for Refugees (UNHCR).

Paragraphs that immediately follow a section heading are leading paragraphs and should not be indented, according to standard publishing style. The same goes for leading paragraphs of subsections and sub-subsections. First lines of subsequent paragraphs should be 1.5 inch left indented. Sections should be numbered sequentially. Spaces should be added before and after each section, sub-sections and sub-subsections. There should not be extra spacing between paragraphs.

viii. Conclusion

Conclusion reflects the author's synoptic opinion on the subject matter, and may include suggestions, proposals, affirmation, recommendations, etc.

ix. Appendices

Brief appendices may be included when necessary, such as copy of letters or decisions. The format for appendices is similar with Heading 1 except they will not be numbered.

x. Disclosures

Conflicts of interest should be declared under a separate header after conclusion. If the authors have no competing interests to declare, then a statement should be included declaring no conflicts of interest. The format for the disclosure is similar with Heading 1. The disclosure section does not have a section number.

xi. Acknowledgments

Acknowledgments and funding information (if necessary) should be added after the disclosure of conflict of interest. The acknowledgments of people, grants, funds, etc. should be brief. You must ensure that anyone named in the acknowledgments agrees to being so named. Include grant numbers and the full name of the funding body. The format for acknowledgement is similar with Heading 1. The acknowledgments section does not have a section number.

**7.2.Case comments**: Case comments to be submitted to the Journal should bestructured as follows:

i. Main subject heading;

ii. Case name and citation;

iii. Text: (1) the facts, (2) the decision, and (3) the commentary on the case; and Summary remark.

**7.3.Legislative reviews**: Legislative reviews to be submitted to the Journal should be structured as follows:

i. Main subject heading;

ii. Name of the legislation and citation;

iii. Body: (1) Background on the subject matter, (2) the objective of the legislation, (3) introduction to main parts of the legislation, (4) the commentary on the legislation; and its implication

**7.4.Book reviews**: book reviews should have the following elements:

i. A Header, that should include: (1) author(s)/editor(s) name, (2) title of book, (3) year of publication, (4) edition (if second or subsequent), (5) publisher and place of publication, (6) number of pages, (7) format (hardback, if available in e-copy), (8) ISBN, and (9) price (if available);

ii. A summary of the intended audience and purpose of the book and how it contributes to the field of scholarship;

iii. A description of the way the author approaches his or her topic, the rigor of the research and scholarship, the logic of the argument, and the readability of the prose;

iv. A comparison with earlier or similar books (if any) in the field to place the book in the existing literature;

v. An evaluation of the book's merits, usefulness, and special contributions, along with constructive comments on its limitations; and indication of who would find the book useful and its implication for research, policy, practice, or theory.

**7.5.Letters**: The letter to the editor should convey its message in a short and definitive fashion. The comments should be objective and constructive.

**7.6.**Author’s affiliation and biographies: For all kinds of contributions, the author’s affiliation shall be indicated in a footnote marked by an asterisk and not by an Arabic number. Affiliations and biographies should be inserted as footnotes. They should be approximately 75 words or fewer. Similar with other footnotes, the font is 10 pt and single space. Superscript letters (a, b, c, etc.) should be used to associate multiple authors with their respective affiliations. The corresponding author should be identified with an asterisk, and that person's email address and phone number should be provided in addition to the

affiliation. Authors shall refer to themselves, if at all, in the third person pronoun throughout the text.

# 8. Page Setup and Fonts

Top, bottom, left, and right margins should be 1 inch. Use Times New Roman font throughout the manuscript, in the sizes and styles shown in Table 1.

**Table 1:** Recommended fonts and sizes.

| **Style name** | **Brief description** |
|---|---|
| **Article Title** | **16 pt, bold, uppercase, center** |
| **Author Names** | **12 pt, bold** |
| Footnotes and Author Affiliations | 10 pt |
| Abstract | 12 pt |
| Keywords | 12 pt |
| **Heading 1** | **16pt, bold** |
| **Heading 2** | **14 pt, bold** |
| **Heading 3** | **13 pt, bold** |
| **Heading 4** | **12 pt, bold** |
| Body Text | 12 pt |
| Figure caption | 10 pt |
| Table caption | 10 pt |

# 9. Requirements as to Reference/ Citation Rule

**9.1.** Chokie Journal of Law follows footnote citation style.

**9.2.** The style of referencing for any contribution to Chokie Journal of Law shall be based on citation rule annexed at the end of this policy, which is the customized version of the OSCOLA Citation Rules (Annex 1).

**9.3.** Where the customized version falls short of completeness for a specific citation, Authors should resort to the latest editions of the OSCOLA Citation Rules.

# Annex 1-Citation Rule- Customized version of OSCOLA Citation Rules

- ✓ Chokie Journal of Law has adopted *the Oxford Standard for Citation of Legal Authorities* (OSCOLA) 4th Edition, 2012 with some modifications.
- ✓ OSCOLA can be accessed following the link; https://www.law.ox.ac.uk/sites/files/oxlaw/oscola_4th_edn_hart_2012.pdf
- ✓ The editors reserve the right to change manuscripts to make them conform with the house style, to improve accuracy, and to eliminate mistakes and ambiguity.

**1. Basic guidelines**

**1.1.Italicization**

When the manuscript is written in English, non-English words must be *italicized.* When the manuscript is written in Amharic, non-Amharic words must be *italicized*

### 1.2.Emphasis

Use *italics* for emphasis.

### 1.3.Quotations

Quotations of more than three lines should be double indented paragraph without quotation marks. Quotations of less than three lines should be in a single quotation mark and not indented from the text. Use square bracket [ ] to note any change in the quoted material, Ellipsis … to indicate omitted material, and [sic] to indicate mistake in the original quote. Begin with an Ellipsis … when a quotation starts mid-sentence. Any comments on the quotation should be in the text or in a footnote. The superscript footnote marker comes last, after both the punctuation and the closing quotation mark. Indicate any use of emphasis in a parenthetical clause after superscript footnote marker by use of (emphasis added).If you omit citations or footnotes from a quotation, put (citation(s) omitted) or (footnote(s) omitted) after the superscript footnote marker.

### 1.4.Footnotes

References in footnotes should generally contain sufficient information about the source material. Footnotes should in accordance with the original language of the source document referred to. The footnote marker should appear after the relevant punctuation in the text (if any) and normally at the end of a sentence. It may sometimes be necessary, for the sake of clarity, to put the footnote after the word or phrase to which it relates. Footnotes should be consecutively numbered and be set out at the foot of each page. Close footnotes with a full stop (or question or exclamation mark.

## 2. Specific Citation Rules

### 2.1. Primary Sources

#### 2.1.1. Legal Instruments

Cite a domestic laws including *italicized* title followed by type and number of legislation, the specific provision using Art., Sec. or Parag.

*Federal Courts Proclamation,* Proclamation No. 25/1996, Art 3.

*Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia,* Proclamation No. 1/1995, Art. 29.

*Criminal Procedure Code of Ethiopia,* Proclamation No. 185/1961, Art. 31.

*Amharic National Regional State The Urban landholding Registration and Information Offices Establishment and Determination of Their Powers and Duties,* Council of Regional

Government Regulation No. 137/2015, Art. 2.

- Cite legal instruments from other jurisdictions as they are cited in their own jurisdiction.

Accident Compensation Act 1972 (NZ)

#### 2.1.2. Cases

- For cases, the general citation rule is:

*The parties na*me [year of the decision] The Court and file number, [Year of publication in the law report] volume/issue and the Law Report and first page of the relevant case.

*Azeb Tamiru v Dejene Zewde* [2009] Ethiopian Federal Supreme Court Cassation Bench 104621, [2010] 21 Decisions of Ethiopian Federal Supreme Court Cassation Bench 47.

- The above example indicates a case between Azeb Tamiru and Dejene Zewde decided by Ethiopian Federal Supreme Court Cassation Bench on 2009 EC with a file number 104621, and that the report can be found on volume 21 of Decisions of Ethiopian Federal Supreme Court Cassation Bench starting from page 47.
- When pinpointing, give the exact paragraph/page number in square brackets at the end of the citation.

  *E.g. Azeb Tamiru v Dejene Zewde* [2009] Ethiopian Federal Supreme Court Cassation Bench 104621, [2010] 21 Decisions of Ethiopian Federal Supreme Court Cassation Bench 47 [49].

- If the case is not reported in the Law Reports, provide all neutral citations as follows.

*E.g. Alemu Fisseha v Bahiru Belay* [2007] Federal High Court Lideta Bench 12890.

- Where a case name is given in the text, it is not necessary to repeat it in the footnote, instead provide other details.
- Cite overseas cases as they are cited in their own jurisdiction with similar information like domestic cases are included. E.g. *Roe v Wade* 410 US 113, 163-64 (1973).
- If the name of the case cited does not itself indicate the jurisdiction and the court of decision, and the jurisdiction and court are not obvious from the context of your work, you should indicate these in parentheses at the end of the reference.

#### 2.1.3. International Treaties

- When citing the instrument for the first time, the *italicized* name of the treaty shall be followed by the date of adoption and entry into force in bracket. Then short form of the treaty followed by the specific provision/section/paragraph shall be provided as seen below.

- *International Covenant on Civil and Political Rights*, (adopted 16 December 1966, entered into force 23 March 1976), ICCPR, Art. 10.

## 2.2.Secondary Sources

### 2.2.1. Books

**2.2.1.1.**Sole authored books

- Use italics for the title, and put the publication information in roman within parentheses. Author, *Title in Italics* (series title, edition publisher, place date) page. E.g. John Baker, *An Introduction to English Legal History* (4th edn Butterworths, London 2002) 419–421.
- Where a book has a title and subtitle not separated with punctuation, insert a colon. E.g. Joseph Raz, *Ethics in the Public Domain: Essays in the Morality of Law and Politics* (Oxford University Press, Oxford 1995) 297.
- Where there are up to three authors, cite the name of all authors.
  E.g. Gwyne Davis, Nick Wikeley and Richard Young, *Child Support in Action* (Hart Publishing, Oxford 1998) 48.
- Where there are more than three authors, cite the first author followed by 'and others'.
  E..g. Roy Goode and others, *Transnational Commercial Law: International Instruments and Commentary* (Oxford University Press, Oxford 2004) 6.
- Names of Ethiopian authors should appear as follows: Author's given (first) name and his/her father's name without changing the order. Subsequent, references should be limited to given names. E.g. Assefa Fiseha, *Federalism and the Accommodation of Diversity in Ethiopia: A Comparative Study* (2nd edn Wolf Legal Publishers, Nijmegen 2007) 235.

**2.2.1.2.**Edited and Translated Books

- The rules are the same as sole authored books, except for the insertion of '(ed)' or '(tr)'. Where there are two editors insert '(eds)' or '(trs)'. E.g.1. Peter Birks and Grant McLeod (trs), *The Institutes of Justinian* (Duckworth, London 1987) 14-15. E.g.2. Gareth Jones (ed), *Goff and Jones: The Law of Restitution* (6th edn Sweet & Maxwell, London 2004) 152.
  E.g.3. Konrad Zweigertand Hein Kötz, *An Introduction to Comparative Law* (Tony Weir tr 3rd edn Oxford University Press, Oxford 1998) 286–287.

**2.2.1.3.**Contributions to books

- Cite essays and chapters in edited books as:

The contributing author/s Name, ‘Title of the Chapter’ in Author, *Title of the book in Italics* (series title, edition publisher, place date) page. E.g.1. Ian Brownlie, ‘The Relation of Law and Power’ in Bin Cheng and ED Brown (eds), *Contemporary Problems in International Law: Essays in Honour of Georg Schwarzenberger on his Eightieth Birthday* (Stevens and Sons, London 1988) 233.

**2.2.2. Articles**

**2.2.2.1.**Hard Copy Published Articles

- The style for articles generally follows the style for books except peculiarities provided as follows.

Name of the author, ‘Title of the Article’ [year of publication] volume number or issue abbreviation/name of the journal the first page of the article, pinpoint page cited.

E.g. Andrew Ashworth, ‘Social Control and “Anti-Social Behavior”: The Subversion of Human
Rights’ [2004] 120 LQR 263, 276.

E.g. Minasse Haile, ‘The New Ethiopian Constitution: Its Impact upon Unity, Human Rights and Development’ [1996] 20 Suffolk Transnat’l L. Rev 1, 6.

**2.2.2.2.**Electronic Journals

- For journals that are only published electronically, give publication details as for hard copy published journals, but also provide the website address and most recent date of access within angled brackets as <web address> | date accessed with no full stop at the end.
- Include page number if there is any. E.g. Carolyn Penfold, ‘Nazis, Porn and Politics: Asserting Control over Internet Content’ [2001] 2 JILT<http://www2.warwick.ac.uk/fac/soc/law/elj/jilt/2001_2/penfold> accessed 27 April 2005

- Where the author is not identified, cite the body that produced the document; if no such body can be identified, insert two joined dashes (like this: ——).

**2.2.3. Other Secondary Sources**

**2.2.3.1.**Theses

- When citing unpublished theses, give the author, the title and then in brackets the type of thesis, university and year of completion with no full stop. E.g. Javan Herberg, ‘Injunctive Relief for Wrongful Termination of Employment’ (LL.M thesis, University of Oxford 1989) 34

**2.2.3.2.**Interviews

- When citing an interview, you conducted yourself, give the name, position and institution (as relevant) of the interviewee, and the location and full date of the interview.
  E.g. Interview with Irene Kull, Assistant Dean, Faculty of Law, Tartu University (Tartu, Estonia, 4 August 2003)
- If someone else conducted the interview, the interviewer's name should appear at the beginning of the citation.

**2.2.3.3.**Websites and blogs

- When citing websites and blogs, use the following citation style. Name of the writer, 'Title of the text' (Name of the Website, Date) <the link> date of access. E.g.1. Sarah Cole, 'Virtual Friend Fires Employee' (Naked Law, 1 May 2009) <www nakedlaw com/2009/05/index html> accessed 19 November 2009

**2.2.3.4.**Newspaper/Magazine Articles

- When citing newspaper articles:

Name of the author, 'The Title' The Newspaper (Place of publication, Date) page
E.g 1. Jane Crof, 'Supreme Court Warns on Quality' Financial Times (London, 1 July 2010) 3 Ian Loader, 'The Great Victim of this Get Tough Hyperactivity is Labour' The Guardian (London, 19 June 2008) <www guardian co uk/commentisfree/2008/jun/19/justice ukcrime> accessed 19 November 2009

**2.2.3.5.**Speeches

- If the speech is unpublished: E.g. Vladimir Putin, Address on Security Council meeting (Moscow, 13 Mach 2022)
- If the speech is taken from published document:
- Vladimir Putin, Address on Security Council meeting (Moscow, 13 Mach 2022) in Russia Today (Moscow, 13 Mach 2022) 3

**2.3.Bibliography**

- Items in bibliographies take the same form as all other citations but with no specific page/section/provision.

**3. Short Forms for subsequent citations**

- If you want to cite the same exact source in the footnote immediately following the full citation, you can generally use 'ibid'.
- If you are citing the same, work but with different page or provision, add the page number/provision that is different from previous citation.E.g. ibid 345.
- If there is more than one citation in the preceding footnote, use ibid only if you are

referring again to all the citations in that footnote. Otherwise, use the citation rule for other subsequent citations as provided below.

- In subsequent (not immediate) citations of a source, identify the source and provide a cross citation in brackets to the footnote in which the full citation can be found. Assefa (n 12) 34.
- The above example refers to page 34 of Assefa's work as initially cited under footnote number 12 of your paper.
- If you have previously cited several works by the same author, the name and the title of the work (or a short form of the title) should be given to differentiate from other works. E.g. Assefa 'Federalism and Development' (n 15) 22.
- For subsequent citations of a case, you can abbreviate the names of the parties after the first citation. E.g. *Azeb Tamiru v DejeneZewde* (n 1).
- For subsequent citations of legislations, you shall use the full form. E.g. *Criminal Procedure Code of Ethiopia,* Proclamation No. 185/1961, Art. 31.
- Subsequent citations of treaties, you shall use full name of the treaty unless abbreviations or other short forms are available.

E.g African Union Constitutive Act, Art. 3

E.g ICCPR Art. 6.

- Never italicize or capitalize for ibid or n.
- Do not use supra, infra, ante, id, op cit, loccit, contra.

**ADDRESS**

**Chokie Journal of Law, School of Law, Debre Markos University**

**P.O. Box- 269**

**E-mail- chokiejol@dmu.edu.et**

**Tel- +251910211910**

**Debre Markos, Ethiopia**